አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ
የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ- ግብር

# በደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ የእረኞች ቃል ግጥም ክዋኔና የይዘት ትንተና

በ

አልማዝ ዘውዱ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሰኔ/2004ዓ.ም
አዲስ አበባ

# በደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ የእረኞች ቃል ግጥም

# ክዋኔና የይዘት ትንተና

አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ
የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነጹሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ- ግብር

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ለኢትዮጵያ ሥነጽሁፍና ፎክሎር የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

አልማዝ ዘውዱ

ሰኔ/2004ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ- ግብር

# በደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ የእረኞች ቃል ግጥም ክዋኔና የይዘት ትንተና

በ

አልማዝ ዘውዱ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ስም ዘሪሁን አስፋው ------------------ ፊርማ ---------------

ፈታኝ ስም ፊርማ

የውስጥ ፈታኝ -------------------- ---------------

የውጭ ፈታኝ -------------------- ---------------

ሰኔ/2004ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ


ምስጋና ........ I
አጠቃሎ ........ II
1. መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.2. የምርምር ጥያቄዎች ........ 2
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 2
1.4. የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መንገዶች ........ 3
1.5. የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.6. ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው ........ 5
1.6.1. ያጋጠሙ ችግሮች ........ 5
1.6.2. የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 6
1.7. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 6
2. ክለሳ ድርሳን ........ 7
2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 8
2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ........ 9
2.2.1. እረኝነት ምንድን ነው? ........ 9
2.2.2. የቃል ግጥም ምንነት እና ፋይዳ ........ 9
2.2.3. ቃል ግጥም ቃላዊ የሚያሰኙት ........ 11
2.2.4. የቃል ግጥም ባህሪ ........ 13
2.2.5. ክዋኔና የክዋኔ አላባውያን ........ 14
3. የጥናቱ አካባቢ ዳራ ........ 17
3.1. የካርታ የአማራ ክልል፣ የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞንና የለጋምቦ ወረዳ ካርታ ........ 18
3.2. የለጋምቦ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ ........ 20
3.3. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ማህበራዊ ህይወት ........ 20
3.4. የኢኮኖሚ መሰረት ........ 22
3.5. የይላዳ ባህላዊ የትግል ስነ-ስረዓት ........ 22
3.6. የለጋምቦ ወረዳ አስተዳደራዊ ታሪክ ........ 24
4. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃልግጥም አደራረስ፣አከዋወንና ተስተላልፎ ........ 26


ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY
4.1. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም አደራረስ ........ 26
4.2. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም ክዋኔ........ 28
4.2.1. በተናጠል የሚከወኑ የእረኞች ቃል ግጥም ........ 29
4.2.2. በጥንድ (በቅብብሎሽ) የሚከወኑ የእረኞች ቃል ግጥም ........ 30
4.2.3. በቡድን የሚከወኑ የእረኞች ቃል ግጥም........ 30
4.3. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም ተስተላልፎ ........ 31
5. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም ይዘት ትንተና........ 33
5.1. ትችታዊ የቃል ግጥሞች ........ 34
5.2. ማንነትን የሚገልፁ የቃል ግጥሞች........ 39
5.3. ትንቢታዊ የቃል ግጥሞች........ 44
5.4. ምክር ለጋሽ የቃል ግጥሞች ........ 49
5.5. ሥድባዊ የቃል ግጥሞች ........ 53
5.6. ማሞገሻ የቃል ግጥሞች........ 55
5.7. የፍቅር መግለጫ ቃል ግጥሞች........ 58
6. ማጠቃለያና ይሁንታ........ 61
ዋቢ መፃህፍት........ 63
አባሪ አንድ፡- የግጥም ስብስብ
አባሪ 2:- ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች
አባሪ 3:- የፎቶ መግለጫ

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ሳይሰለቹ ጥናቴን በማረምና በማስተካከል ሙያዊ እገዛቸው ላልተለየኝ መምህሬና አማካርዮ ዘሪሁን አስፋው (ረዳት ፕሮፌሰር) ምስጋናዬ  የከበረ ነው፡፡ በመቀጠልም ጥናቱን ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ አድርጎልኛልና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

ይህ ጥናት የተሳካ እንዲሆን መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ መረጃ አቀባዮቼ በሙሉ፣ እና በማስተካከል ታላቅ አስተዋጾ ላደረጉልኝ የክፍል ጓደኞቼ ለተመስገን ታደሰና ትግስት አለማየሁ እንዲሁም ስለሺ አባተና የጥናቱን ረቂቅ ለተየበችልኝ ለማህሌት ዘውዱ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ እረኞች የሚከውኗቸው ቃል ግጥሞች ላይ የተደረገ ነው፡፡ ከአሁን በፊት በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ዲግሪ በእረኞች ቃል ግጥም ክዋኔ እና ይዘት ትንተና ላይ በቂና አጥጋቢ ጥናት አልተደረገም፡፡ ይህ ጥናት ያንን ክፍተት ለመሙላት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ዓላማው የቃል ግጥሞቹን ክዋኔ ምን እንደሚመስል መግለጽና የይዘት ትንተና ማድረግ ነው፡፡

ጥናቱ ክዋኔ ተኮር ንድፍ ሃሳብን መሰረት ያደረገ ሲሆን የጥናቱ አቀራረብም በገላጭ ተንታኝ ዘዴ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ለጥናቱ ግብዓት የሆኑ መረጃዎችም ከካልአይና ቀዳማይ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎች መሰብሰብ የተጀመረው ከካልአይ የመረጃ ምንጮች ነው፡፡ እነዚህም ከቤተ መጻህፍት ፣ከተለያዩ ቢሮዎች ውስጥ ከተገኙ ጽሁፋዊ ሰነዶች እና ስለ አካባቢው ሁኔታ ከሚያውቁ ሰዎች የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ቀዳማይ መረጃዎች ደግሞ ምልከታንና ቃለ-መጠይቅን በመጠቀም ከመስክ የተሰበሰቡ ሲሆን መቅረፀ-ድምጽ፣ ፎቶና ቪዲዮ ካሜራ እንዲሁም የማስታወሻ ደብተሮች በአጋዥ መሳሪያነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ከመረጃ ትንተናው ማየት እንደሚቻለው የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም አደራረስና ተስተላልፎ ከቤተሰብና ከጓደኞቻቸው የሰሙትን በመሸምደድ ወይም በአካባቢ ከሚያዩት ነገር በመነሳት ፈጥረውና ለአውዱ እንዲስማማ አድርገው ይደርሱታል፡፡ በሚያዜሟቸውና በሚከውኗቸው ቃል ግጥሞች ላይ የቃል፣ የሀረግና የስንኝ ለውጥ በማድረግ እንደገና እንደሚደርሷቸውና እንደሚያስተላልፏቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ እረኞች የሚደርሷቸውን የቃል ግጥሞች በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን እንደሚከውኗቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

እረኞች በተለያዩ አጋጣሚዎች ባነሷቸው ቃል ግጥሞቹ ትችትዊ፣ ትንቢታዊ፣ ስድባዊ፣ ማሞገሻ፣ ማንነት ገላጭ ፣ምክር ለጋሽና ፍቅር መግለጫ ይዘት ያላቸውን ቃል ግጥሞች ማንሳታቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ እረኞች ቃል ግጥሞቹን ለተለያዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች መግለጫነት ከመጠቀም ባለፈ ለትንቢት መንገሪያነት ይጠቀሙባቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ እረኞች በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ "ትንቢት ተናጋሪ" እየተቆጠሩ "እረኛ ምን አለ?" በሚል ትልቅ ክብር ይሰጣቸዋል፡፡ የእረኞች የ"ትንቢት ተናጋሪነት" ሚና ሴቶችን እንደማያካትት በጥናቱ ለማየት ተችሏል፡፡ እረኞች አብዛኛውን ጊዜ ቃል ግጥሞችን የሚደረድሩት በእረኝነት ስፍራ ከብቶችን ውሃ ሲያጠጡ በተለይም ጠዋትና ማታ አካባቢ እንደሆነ በጥናቱ ማወቅ ተችሏል፡፡

# 1. መግቢያ

ይህ ጥናት በደቡብ ወሎ ዞን የለጋምቦ ወረዳ እረኞች በሚያዜሟቸውና በሚከውኗቸው ቃል ግጥሞች ላይ ያተኮረ ነው። በአካባቢው ከአሁን በፊት በዚህ ርዕስ ጥናት አልተደረገም። በመሆኑም እረኞች በቃል ግጥማቸው ምን መልዕክትን እንዴት እንደሚያስተላልፉ ዳሷል።

ጥናቱን ለማሳካት በልጅነት፣በወጣትነት፣በጎልማሳነትና በእርጅና እድሜ ላይ ያሉ እረኞችን በመረጃ አቀባይነት ተጠቅሜያለው። እነዚህ መረጃ አቀባዮች በጥናቱ ላይ ያላቸውን ጉልህ ድርሻ እውቅና ለመስጠትም ሙሉ ስማቸው፣እድሜያቸው፣ስራቸው፣የመኖሪያ ቀበሌያቸው፣ መረጃ የሰጡበት ቀንና ቦታ እንዲሁም ስለ መረጃ አቀባዮቹ አጠቃላይ መግለጫ የሚሰጡ ተጨማሪ ማብራሪያዎች መረጃ በሰጡበት በታ ላይ በፋት ኖት ተብራርቷል።

ከነዚህ መረጃ አቀባዮች የምልከታና ቃለ መጠይቅ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴን በመጠቀም በመቅረፀ ድምጽ፣በፎቶ ካሜራ፣ በቪዲዮ ካሜራና በማስታዎሻ ደብተር መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። እነዚህንም ዘዴዎች በመጠቀም የተገኙትን መረጃዎች ክዋኔን ማእከል ያደረገ *(performance centered approach)* ዘዴን መሠረት በማድረግ የእረኞች ቃል ግጥም ላይ ያሉትን ክዋኔዎች፣ አውድ፣ መልእክት፣ ከዋኝ፣ መቼት፣ አቀራረብ፣ ወዘተ... ምን እንደሚመስሉ ተንትኛለሁ።

ጥናቱ የለጋምቦ ወረዳ እረኞችን በቃል ግጥማቸው አማካኝነት ከማስተዋወቁም በላይ ወደፊት በዚህ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ለሚያጠኑ አጥኝዎች እንደ መረጃ ምንጭ ሆኖ ያግዛል የሚል እምነት አለኝ።

## 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ከልጅነቴ ጀምሮ እሰማቸው የነበሩ የእረኛ ቃል ግጥሞች ምንም እንኳ የያዙት መልእክት በወቅቱ ባይገባኝም የፎክሎር ትምህርት ስማር ባገኘሁት ግንዛቤ እንዴት ከውነው መልእክት እንደሚያስተላልፉ ለማወቅ ጉጉት ስላደረብኝ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአካባቢው ከአሁን በፊት የእረኞች ቃል ግጥምን በተመለከተ በበቂ ሁኔታ ጥናት ባለመደረጉ ነገሩን ይበልጥ ለመመርመር እንድነሳሳ አድርጎኛል፡፡

## 1.2. የምርምር ጥያቄዎች

- እረኞች ቃል ግጥምን ይፈጥራሉ ወይስ አሻሽለው ያቀርባሉ? ክዋኔአቸውስ ምን ይመስላል?
- በቃል ግጥሞቹ ምን መልክቶች ይተላለፋሉ?
- እረኞች ቃል ግጥሞቹን የሚያዜሙበት የተለየ ቦታና ጊዜ አላቸው?
- እረኞች ቃል ግጥሞቹን ለምን ፋይዳ ይገለገሉባቸዋል?
- እረኞች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው አጠቃይ ገፅታ ምንድን ነው?

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች በመመለስ ጥናቱ የሚከተሉትን አላማዎች ያካል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም ክዋኔና ይዘት ላይ ገለጻና ትንተና ማድረግ ነው፡፡ የጥናቱ ንዑሳን አላማዎችም፡-

- እረኞች ቃል ግጥምን ይፈጥሩ ወይም የነበረውን አሻሽለው ያቀርቡ እንደሆነ መመልከትና መግለፅ፡-
- የለጋምቦ ወረዳ እረኞች በቃል ግጥማቸው ምን ምን ጉዳዮችን እንደሚያነሱ በመመርመር ተነትኖ ማሳየት፡-
- ቃል ግጥሞቹን መቼ፣ የት፣እንዴትና ለምን እንደሚያዜሟቸውና እንደሚከውኗቸው ማመላከት፡-
- እረኞች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ቦታ ምን እንደሚመስል መመርመር፡-

## 1.4. የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መንገዶች

ለዚህ ጥናት ተገቢ የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል። መረጃ መሰብሰብ የተጀመረውም ከካልዓይ ምንጮች ነው። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ከቤተ መጻህፍት ፣ ከተለያዩ ቢሮዎች ውስጥ ከተገኙ ጽሁፋዊ ሰነዶች እና ስለ አካባቢው ሁኔታ ከሚያውቁ ሰዎች ነው። በዚህም መሰረት ስለ ጥናቱ አካባቢና ህዝብ ሁለንተናዊ መልክ የሚያትቱ ጽሁፋዊና ቃላዊ መረጃዎች፣ ጥናቱን ለመተንተን እና ለማደራጀት የሚረዱ ንድፈ ሀሳቦች ከተለያዩ መጽሀፍት ተሰብስበዋል።

ቀዳማይ ምንጮች ቃል ግጥሞቹ የተከወኑባቸውን አውዶች፣ በአውድ የተሳተፉ መረጃ አቀባዮችን፣ለፎክሎር ቅንጣቶቹ መከወን ሰበብ የሆኑትን አጋጣሚዎች ይመለከታሉ Goldstein (1964, 80-82)። ስለሆነም በዚህ ጥናት መረጃ የሰጡ ግለሰቦች፣ ቃል ግጥሞቹን ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀት እና ለመተንተን ያስቻሉ አጋጣሚዎች በሙሉ እንደ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ናቸው። በመሆኑም መረጃዎችን ከቀዳማይ ምንጮች ለመሰብሰብ ሁለት ጊዜ የመስክ ጉዞ ተደርጓል:: የመጀመርያው ከየካቲት 1 እስከ 23/2004 ዓ.ም ሲሆን ሁለተኛው የመስክ ጉዞ ደግሞ ከሚያዚያ 4- 13/2004ዓ.ም የተደረገ ነው።

መረጃዎችንም ለመሰብሰብ ከመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች መካከል ምልከታና ያልተዋቀሩ ቃለ መጠይቅ አገልግሎት ላይ ውለዋል። ቃል ግጥሞችን ከመከሰቻ አውዳቸው ለመሰብሰብ በተፈጥሮአዊና አርቲፊሻል መቼት ተሳትፋዊና ተሳትፋዊ ያልሆነ ምልከታን ተጠቅሚያለሁ።

በዚህ ጥናትም ቃለ- መጠይቅን መጠቀሜ በምልከታ ወቅት ግልጽ ያልሆኑ ቃላትና እንቅስቃሴዎችን ለመረዳት፣ የአካባቢውን ዘዬዎች እና ታሪካዊ ሁነቶችን ትርጓሜ ለመረዳት አስችሎኛል። ቃል መጠይቁ ባልተዋቀረ መልኩ የተከናው መረጃ አቀባዮች ሳይጨነቁና ዘና ብለው በለመዱት ወጋዊ የአነጋገር መንገድ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ያልተቆራረጠና ሰፊ መረጃን ማግኘት ያስችላል ከሚል እሳቤ ነው። ይህም በትግበራ ወቅት የታለመለትን ግብ መቷል።

በአንድ የመስክ ስራ ምልከታና ቃለመጠይቅን በጋራ መጠቀም መረጃን በበቂ ሁኔታ ለመሰብሰብ፣ የመረጃ ክፍተትን ለመሙላት እና የተለያዩ አመለካከቶችን እና ፍልስፍናዎችን በቀላሉ ለመረዳት ይረዳል Goldstein (1964,78) ፈቃደ (1993፣93)። ቃል ግጥሞችን በሚገኙበት አውድ መሰብሰብ የቃል ግጥሞቹን የክዋኔ ሂደት፣ የከዋኞቹን አጠቃላይ

እንቅስቃሴና ሚና እንዲሁም የርስ በርስ መስተጋብር ባካተተ ሁኔታ ለመሰብሰብ አስችሎኛል፡፡ ይህም መረጃዎችን በጥሩ ሁኔታ ተረድቶ ለመግለጽና ለመተንተን የተሻለ ሁኔታን ፈጥሮልኛል፡፡ እንደ Goldstein (1964,104) አገላለጽ በቃለ መጠይቅ የሚገኙ መረጃዎች የመረጃ ሰጭዎችን አመለካከት፣ ስሜትና ፍላጎት እንዲሁም ገለጻና ማብራሪያ ያካተተ ነው፡፡

እንደ Goldstein (1964, 44--48); ፈቃደ (1993፣133-135) አገላለጽ የቴክኖሎጂ መሳርያዎችን ተጠቅሞ መረጃዎችን ከአውዳቸው ለመሰብሰብ መሞከር በጽሁፍ ቀርጾ ለማስቀረት አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔቶችን (ቅርጽ፣ ቀለም፣ ንድፍ፣ ዜማ፣ ቅላጼ፣ እንቅስቃሴውን እንዲሁም የመሳሰሉ የፎክሎር ቅንጣት መልኮችን) አካቶ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንደሚያስችል ይመክራሉ[1]፡፡ እኔም የነዚህን ምሁራን ተመክሮ በመመስረት መረጃዎችን በቴፕ ሪከርደር፣ በፎቶና ቪዲዮ ካሜራ እንዲሁም በማስታወሻ ደብተሮች በመከተብ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ጥናቱ ታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴን መሰረት አድርጎ የተከናወነ ነው፡፡ በመሆኑም በለጋምቦ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ሰላሳ አምስት ቀበሌዎች ለጥናት የተመረጡት ስድስቱ ናቸው፡፡

በጥናቱም በተመረጡት ስድስት ቀበሌዎች የሚኖሩ በተለያዩ የእድሜ ደረጃዎች ላይ ያሉ ሃያ ስድስት መረጃ አቀባዮች ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን በመስጠት ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከነዚህም መካከል አስሩ አውራ መረጃ አቀባይዮች ሲሆኑ ቀረዎቹ ረዳቶች መረጃ አቀባዮች ነበሩ፡፡ አውራ መረጃ አቀባዮቹ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ባላቸው ሰፊ እውቀት እና ሊሰጡ በሚችሉት መረጃ በመመስረት የተመረጡ ናቸው፡፡

ከነዚህ መረጃ አቀባዮች በክዋኔ ወቅት እና ክዋኔ ውጭ በቃለ መጠይቅ ሶስት መቶ ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የተነሳውን ነገረ ጉዳይ የበለጠ ይገልፃሉ የተባሉ ሃምሳ ሶስት ቃል ግጥሞች ተመርጠው ገለፃ እና ትንታኔ ተደርጎባቸዋል፡፡

እነዚህንም ዘዴዎች በመጠቀም የተገኙትን መረጃዎች ክዋኔን ማእከል ያደረገ *(performance centered approach)* ዘዴን በመጠቀም እተነትናለሁ፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ የእረኞች

[1] *በዚህ ጥናት ከአጥኚዋ እድሜ በላይ የሆኑ የመረጃ አቀባዮች በሙሉ እንዲሁም የውጭም ሆኑ የሃገር ውስጥ ጽሐፍትና ተመራማሪዎች በ"እንቱታ" ተገልፀዋል፡፡ ምክንያቱም ጸታቸውን ከስማቸው ለይቶ ለመረዳት አስቸጋሪ በመሆኑ እና "እንቱታው" ሁሉንም ጾታዎች በማያሻማ መንገድ ያካትታል ብዬ በማመን ነው፡፡ ከአጥኚዋ እድሜ በታች የሆኑ መረጃ አቀባዮች "ገልጿል፣ገልጻለች፤እንደገለጸው፣እንደገለጸችው" በማለት ተጠቅሜያለሁ፡፡*

ቃል ግጥም ላይ ያሉትን ክዋኔዎች፣ አውድ፣ መልእክት፣ ከዋኝ፣ አቀራረብ፣ ወዘተ… ምን እንደሚመስሉ እየተነተንኩ አሳያለሁ።

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ለጋምቦ ወረዳ ከሚገኙ ሰላሳ አምስት ቀበሌዎች ውስጥ ጊንባ፣ ቱሉ አውልያ፣ መቀርጨሚያ፣ ጭሩ፣ ይላዳ እና ገነቴ በተባሉ ስድስት ቀበሌዎች ላይ ያተኮረ ነው። ሁሉንም ቀበሌዎች ማካተት ያልተቻለበት ምክንያት ለጥናት የተመረጡት ቦታዎች በቂ መረጃ ይገኝባቸዋል ተብሎ ስለታመነና[2] ካለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት አንጻር ነው። ጥናቱ በልጅነት፣ በወጣትነት እና በእርጅና እድሜ ክልል ላይ ያሉ እረኞችን ያጠቃልላል። ምክንያቱም በአካባቢው እረኞች በአብዛኛው በእነዚህ እድሜ ክልሎች ውስጥ ስለሚገኙ ነው። በዚህ መሰረት ጥናቱ የዘፈን፣የፋከራ፣የቀረርቶ እና ሌሎችም እረኞች በቃል የሚያዜሟቸው የቃል ግጥሞችን ያካተተ ነው።

## 1.6. ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው

ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ብዙ ችግሮች አጋጥመውኛል። ሆኖም አብዛኞዎቹ ችግሮች በብዙ አጥኚዎች ዘንድ የተለመዱ በመሆናቸው ሁሉንም አልዘረዝርም። እዚህ የማነሳው ለቀጣይ ተመራማሪ ትምህርት ይሆናሉ ያልኳቸውን ጥቂት የመስክ ችግሮች እና ችግሮቹን ለመፍታት የወሰድኳቸውን መፍትሄዎች ብቻ ነው።

### 1.6.1. ያጋጠሙ ችግሮች

የመጀመሪያው ችግር ከአካባቢው የአየር ንብረት ጋር ተያይዞ የመጣ ነው። አካባቢው እጅግ በጣም ቅዝቃዜ እና ውርጭ የበዛበት ከመሆኑ የተነሳ መረጃዎችን በመቅረፀ ድምፅ ፣ በቪድዮ እና ፎቶ ካሜራ ስሰበስብ መረጃው ጥራት እንዳይኖረው እና በነፋስ የታጀበ ድምፅ እንዲሆን አድርጎታል።

ሁለተኛው ችግር መረጃዎችን በአንድ ቦታ ካለማግኘት ጋር ተያይዞ የመጣ ነው። አብዛኛው የለጋምቦ አካባቢ እረኞች ጊምባ ሜዳ በተባለ ቦታ ላይ ከብት ይጠብቁ ነበር። በወቅቱ ለጥናት

---

[2] መረጃ ይገኝባቸዋል ተብሎ ስለታመነ ሲባል የወረዳው ምክር ቤት እንዲሁም ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ በሰጠኝ ጥቆማ መሰረት ለጥናት የተመረጡት 6 ቀበሌዎች በወረዳው ከሚገኙ 35 ቀበሌዎች ዙሪያ ስለሚገኙ የሌሎቹንም ቦታዎች አጠቃላይ ገጽታ ያሳያሉ በሚል ነው። በተጨማሪም እኔም በጥናቱ ለመዳሰስ እንደሞከርኩት በእነዚህ ቦታዎች በቂ መረጃ አገኝቻለሁ።

የተመረጠው ቦታ የበልግ እህል የሚዘራበት ወቅት ቢሆንም ዝናብ ባለመጣሉ ምክንያት ይጠብቁበት የነበረው ቦታ ላይ ለከብቶች የሚሆን ሳር ስላልነበር በየአካባቢያቸው ተበታትነው መረጃውን ከአንድ ቦታ ማግኘት አልቻልኩም ።

ሶስተኛው ችግር ከመረጃ ሰጭዎችና መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጋር ተያይዞ የመጣ ነው። ይህም ቃል ግጥሞችን በምሰበስብበት ወቅት በመረጃ አቀባዮቹ ዘንድ ሁለት ችግር ገጥሞኛል። የመጀመሪያው ከአሁን በፊት መረጃ ሰጥተን የኛን መረጃ ወስደው የኛነቱን ሳይገልጹ የሸጡ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ምንም አላደረጉልን በማለት መረጃን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ነው። ሁለተኛው ከዋኞቹ ሲከውኑ መቅረፀ ድምጹን እና ፎቶ ካሜራውን ለመጠቀም ስሞክር በትክክል ከመከወንና ለቃል ግጥሞቹ ማብራሪያ ከመስጠት ይቆጠባሉ። መሳሪያዎቹን በማልጠቀምበት ጊዜ በርካታ ቃል ግጥሞችን ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ በነፃነት ይከውናሉ። ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ድምጻቸውንም ሆነ ምስላቸውን እንዳልወስድ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ሁኔታ አጋጥሞኛል።

## 1.6.2. የተወሰዱ መፍትሄዎች

ለመጀመሪያው ችግር እንደ መፍተሄ የወሰድኩት መርጃዎችን በድምፅ ከመቅረፅ በተጨማሪ በማስታዎወሻ መያዝ እና ንፋስ የማይበዛበት አካባቢን በመምረጥ የቃለ መጠይቅ ስራውን አካሂጃለሁ ።

ለሁለተኛው ችግር እረኞች በሚገኙበት ቦታ በመዘዋወር መሰብሰብን እና የተጠኚ ቦታዎችን ቁጥር ከአንድ ወደ ስድስት ማብዛትን እንደ መፍትሄ ተጠቅሜ በቂ መረጃዎችን ለማግኘት ችያለሁ።

ለሶስተኛው ችግር ቀድሞ የተቀረፁ መረጃዎችን ማሰማት፣ የስራውን ተግባር በግልፅ ማስረዳት እና በምስል እና ድምፅ መቅረጫዎች ምትክ የማስታዎሻ ደብተሮችን መጠቀም እንደ መፍትሄ ተጠቅሚያለሁ።

## 1.7. የጥናቱ ጠቀሜታ

- ✓ ቃል ግጥሞች በየጊዜው የመለዋወጥና የመቀያየር ብሎም የመደጋገም ባህሪይ ስለሚታይባቸው ወደፊት ለሚመጡ ተመራማሪዎች አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር እያነፃፀሩ ለማጥናት እገዛ ያደርጋል፡፡
- ✓ የማህበረሰቡ አንድ ክፍል የሆኑትን የለጋምቦ ወረዳ እረኞች የህይወት ፍልስፍና ያስተዋውቃል፡፡
- ✓ እስከአሁን ድረስ እኔ ባደረኩት ፍተሻ መሰረት የለጋምቦ ወረዳ የእረኞችን ቃል ግጥም ክዋኔና ይዘት ትንተናን አስመልክቶ በወጉ የተጠና ጥናት አላጋጠመኝም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ወደፊት በዚህ ዙሪያ ለሚያጠኑ ሰዎች መነሻ ይሆናል የሚል ግምት አለኝ፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል ሁለት መሰረታዊ ነጥቦች ይነሳሉ። አንደኛ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በማድረግ ከዚህ ስራ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጥናታዊ ስራዎች ያላቸው ዝምድናና ልዩነት ማሳየት። ሁለተኛ ከእረኞች ቃል ግጥም ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፅንሰ ሃሳቦች - የእረኝነት ምንነት፣ የቃል ግጥም ምንነት እና ፋይዳ፣ ቃላዊነት እና መመደቢያ ዘዴዎች እንዲሁም ለዚህ ስራ በንድፈ ሃሳብ ማሳያነት የተመረጠው ክዋኔ ተኮር ንድፈ-ሃሳብ ምንነት በፅንሰ ሃሳቦች ደረጃ ይቃኛሉ።

### 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት በፊት ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል በጊምባ እረኞች ቃል ግጥም ላይ "ሽር ፈለቀ" በተባለ ተማሪ በ1982 የቀረበ ጥናት መኖሩን ተነግሮኝ ነበር። ነገር ግን ጥናቱ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣በኬኒዲ እና በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ቤተ መጻህፍት ፈልጌ አላገኘሁትም። ሆኖም ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያለው ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የተሰራ አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ ለማግኘት ችያለሁ። ጥናቱ በ1990 "የአክሱምና አካባቢዋ እረኞች የሚሰሟቸው የዘፈን ግጥሞች" በሚል ርዕስ በተክላይ ትዛዙ የቀረበ ነው። አጥኚው አንድ መቶ ሁለት የዘፈን ግጥሞችን በስምንት ቀበሌዎች ከሚያዚያ አጋማሽ እስከ ግንቦት አጋማሽ ድረስ መሰብሰቡን ገልጿል። እነዚህን የሰበሰባቸውን ግጥሞች በይዘት በመከፋፈል፣ የግጥሞችን ቅርፅ፣ አሰነኛኘት፣ ሀረግ ምጣኔ፣ ቤት አመታትና፣ የዘይቤ አጠቃቀም ምን እንደሚመስሉ ገልጿል። የይዘት ትንተናውን ያደረገው የአውዳመት የዘፈን ግጥሞችና ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የሚገጥሟቸው የዘፈን ግጥሞች ብሎ ነው።

በመጀመርያው ክፍል በቅዱስ ዮሀንስ፣ በመስቀል፣ በገና፣ በሐምሌ አቦ፣ የሚዘፈኑትን በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለማሽላ ጥበቃ፣ ስለቦታዎች እና ስለፍቅርና ወሲብ ይዘፈናሉ ያላቸውን ግጥሞች ተመልክቷል።

ከኔ ጥናት ጋር ሰብስቦ የይዘት ትንተና ማድረጉ ቢያመሳስለውም የእሱ ዋና ትኩረት የዘፈን ግጥሞቹን ይዘት መሰረት አድርገው የግጥሙን ቅርፅ፣ አሰኛኘት፣ ሐረግ ምጣኔ፣ ቤት አመታትና ዘይቤያዊ አጠቃቀም መመርመር ላይ ነው። ነገር ግን እረኝነት ምንድን ነው? የእረኞች ራሳቸው ቃል ግጥም አላቸው? ክዋኔያቸው ምን ይመስላል? ማህበረሰቡ ስለ እነሱ ያለው አመለካከት፣የቃል ግጥሞቹ አደራረስ፣ ተስተላልፎና ክዋኔ ምን ይመስላል?፣ ማህበረሰቡ

እረኞችን እንዴት ይገልጿቸዋል? የሚሉትንና አጠቃላይ ያለውን ገፅታ አይዳስስም፡፡ በመሆኑም ከኔ ጥናት ጋር የጎላ ልዩነት አለው፡፡

## 2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

ይህ ክፍል እረኝነት ምንድን ነው? የቃል ግጥም ምንነት እና ፋይዳ፣ ቃላዊነት፣ መመደቢያ ዘዴዎች እና የጥናቱ ማጠንጠኛ የሆነው የክዋኔ ምንነትና እንዴትነት የተካተቱበት ነው፡፡

### 2.2.1. እረኝነት ምንድን ነው?

ስለ እረኛ ሲነሳ ከብት ወይም ሰው ጥበቃን እናስባለን፡፡ ለመሆኑ እረኛ ምንድነው? ይህን ቃል ከሳቴ ብርሃን ተሰማ (1951፣8) "ከብትን አሰማርቶ ወደ ከፉ ቦታ እንዳይሄድ የሚጠብቅ" በማለት ትርጓሜ ሰጥተውት ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ ደግሞ ደስታ ተክለወልድ (1970፣138) "አጋጅ፣ ጠባቂ፣ ዘላን፣ ዳሳገሳ፣ ጫኝ..." በማለት ተርጉመውት እናገኛለን፡፡ ከብያኔው መርዳት እንደሚቻለው እረኝነት ከብቶችን በግጦሽ (በጥበቃ) ቦታ አሰማርቶ መጠበቅ ማለት ነው፡፡ እረኞች ከብቶችን ሲጠብቁ ቃል ግጥምን እንደሚደረድሩም ይታወቃል፡፡ ምንም እንኳ የማህበረሰቡ አንድ አካል እንደመሆናቸው መጠን እንዴት የተለየ ቃል ግጥም ሊኖራቸው ቻለ ቢያሰኝም ከተግባራቸው ጋር ተያይዞ የእረኛ ቃል ግጥም ይባላል፡፡ ፈቃደ (1991፣ 87) በርካታ ቃል ግጥሞችን የለቅሶ፣ የሰርግ፣ የበገና፣ የታቦት የእረኛ እያሉ መሰየም የተለመደ ነው፡፡ እነዚህም በተለያዩ መመዘኛ ነው፡፡ ይህም ከሚከወኑበት ምክንያት ጋር፣ ከግጥሞቹ አዝማች፣ ከሙዚቃው መሳርያ እና ከዘፋኙ (ከባለጉዳዩ) ጋር ተያይዞ የተሰጠው ስያሜ ነው ፡፡

ስለዚህ ፈቃደም እንደሚነግሩን የእረኞች ቃል ግጥም ሲባልም ከዘፋኞቹ ወይም ከባለ ጉዳዮቹ ተግባር ጋር ተያይዞ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ እረኞች የማህበረሰቡ አንድ አካል ብቻ ሳይሆኑ የሂወት ፍልስፍና ገላጭ ጭምር ናቸው፡፡ ለምን ቢሉ ማህበረሰቡ መናገርና መተንፈስ የለብኝም ብሎ አምቆ የያዛቸውን ጉዳዮች በቃል ግጥማቸው ያስተላልፋሉ፡፡

## 2.2.2. የቃል ግጥም ምንነት እና ፋይዳ

ቃል ግጥም ከአራቱ የፎክሎር የጥናት መስኮች በስነ-ቃል ውስጥ የሚጠቃለል ነው። ብያኔውን አስመልክቶ በርካታ ነጥቦች ተነስተዋል። ይህንንም በተመለከተ ቃል ግጥም አደራረሱን፣ ተስተላልፎና አከዋወኑን መሰረት በማድረግ እና ቃላዊነቱን መሰረት በማድረግ ብያኔ መስጠት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ልክ እንደ ቃል ግጥም ሁሉ የጹሁፍ ግጥምም ሊነበነብ እና ሊከወን ይችላል Finnegan (1977,3) ፈ.ቃደ (1993፣84) ። እነዚህ ነጥቦች ደግሞ ለቃል ግጥም አንድ ወጥ ብያኔ አለመኖር እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ጉዳዩ አሻሚ ቢሆንም የቃል ግጥምን ተግባር፣ ቃላዊነትና ዘመን ተሻጋሪነት መሰረት በማድረግ የተለያዩ ምሁራን ገለፃ ሰተዋል።

> Oral poetry is not an odd or aberrant phenomenon in human culture, nor a fossilized survival from the far past, destined to wither away with increasing modernization. In fact it is of common occurrence in human society, literate as well as non-literate. It is found all over the world, past and present... (Finnegan,1977:3).

በማለት ሲገልፁ በሌላ መልኩ ደግሞ ፈ.ቃደ (1993፣86) "ቃል ግጥም ማለት አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎው እና አቀራረቡ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ፣ በዘፈን፤ በሙሾ፤ በእንጉርጉሮና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፆች ውስጥ የሚገኝ ህዝባዊ ግጥም ነው" ይላሉ።

ከሁለቱም ብያኔ መረዳት እንደሚቻለው ቃል ግጥም በቃል የሚፈጠር፤ በቃል የሚነገር ወይም የሚተላለፍ፤ በየትኛውም ስፍራ፤ ዘመን፤ ማህበረሰብ እና ሁኔታ ሊገኝ የሚችል የህዝብ ሃብት ነው ማለት ይቻላል። ቃል ግጥም ከስፍራ፣ ከዘመንና ከሁኔታዎች አልፎ ለመነገር እና ለመሰማት አቅም ያለው የሰዎች የአመለካከት፣ የስሜት፣ የፍላጎት እና የፍልስፍና መግለጫ ነው ማለት ይቻላል።

ቃል ግጥምን ከኋላ ቀርነትና ካልተማረው ማህበረሰብ ጋር የማያያዝ ሁኔታዎች ቢስተዋሉም መልክና ፀባዩን ሊቀይር እንጂ በየትኛውም ትውልድና ማህበረሰብ የስሜት (ደስታ፣ሃዘን፣ ፍርሃት፣ አክበሮት እና አድናቆት)፣ የስኬትና የውድቀት መግለጫ በመሆን ሲያገለግል የነበረና ወደፊትም የሚያገለግላል ነው። በመሆኑም የቃል ግጥም ዘመን ተሻጋሪነትና በሁሉም አለም መገኘት አያጠራጥርም።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ቃል ግጥም በርካታ ተግባር /ፋይዳ/ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ቃል ግጥም የሰው ልጅን ውስጣዊ ህይወትና ጥልቅ ስሜት ይገልጻል፣ መረጃ በማቀበል ያገለግላል፡፡ ማህበረሰቡ ሊመጣ የሚችለውን አደጋ ለመቋቋምና ስለታሰበ አስቸጋሪም ሆነ ጥሩ ነገር ማምለጫነት የሚጠቀምበት ጭምር ነው፡፡ እናም ፋይዳው እጅጉን ተዘርዝሮ የማያልቅ ነው ለማለት ያስደፍራል Finnegan (1977, 3-7፡ 1970,273); ፊቃደ (1994፣330-338) ፡፡

## 2.2.3. ቃል ግጥም ቃላዊ የሚያሰኙት

ሥለ ቃል ግጥም ስናነሳ በዋናነት ቃላዊነቱን ታሳቢ እናደርጋለን፡፡ ነገር ግን ይህ ሀሳብ እንደ Finnegan(1977, 14-17) አገላለፅ በቃል ግጥም ውስጥ "ቃላዊነት" የሚለው ቃል አሻሚ ነው፡፡ አንዳንዴ በፅሁፍ ከሚገኙ ስራዎች ጋር ጉልህ ልዩነት ማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም "ቃላዊነት" በአንድ በኩል የተፃፉ ስራዎችን በቃል ከሚገኙ ለመለየት እንደ አንድ መስፈርት ወይም መለያ እንጠቀምበታለን፡፡ ቃላዊነቱን መሰረት አድርገን ደግሞ ሶስት መስፈርቶችን በማስቀመጥ የልዩነት ድንበር ማበጀት ይቻላል፡፡ ይህም አደራረሱ ስርጭቱና ክዋኔ ነው፡፡ Finnegan (1977,17) "The three ways in which apoem can most readily be called "oral" are items of (1) its composition (2) its mode of transmission and (3) related to (2) its performance" በማለት ሶስቱን መለያ ነጥቦች ያስቀምጣሉ፡፡ ነገር ግን እንደ መፍትሄ ወይም ጊዜያዊ መስፈርት ሊታዩ የሚችሉ መለያ ነጥቦች ናቸው፡፡

አንድ ቃል ግጥም እንዴት ይደረሳል? ሲባል በቃል አጥንቶ በመሸምደድ ወይም ቀድሞ በተሰማው ላይ ማሻሻያ በማድረግ ሊባል ይችላል፡፡ ከዋኙ በሚከወንበት ወቅት በመሃሉ የነበሩትን የዜማ አወራረድ ስልት ተከትሎ የራሱን አዳዲስ ስንኞችና ቃላት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ከዋኙ የታዳሚዎችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ለማነቃቃት፣ ክዋኔውን ለማራዘምና የታዳሚውን አመለካከትና አኗኗር በየጊዜው ሲለወጥ ወቅታዊ ለውጡን ለመግለፅ ነባሩን ግጥም ስለሚለውጠው ነው፡፡ ይህ የለውጥ ባህሪይ በአብዛኛው በቃል ግጥሞች ላይ ይታያል፡፡

Finnegan (1977,53) እንደሚያስረዱት በክዋኔ ወቅት ቃል ግጥሞች በተለያየ መንገድ ሊደረሱ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ሙካከል ሽምደዳ (Memorization)፣ እዚያው በዚያው ወይም ወዲያውነት (imporisation) እና ተመስጦ (inspiration) ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የሽምደዳ አደራረስ ስልት ከዋኙ ቀድሞ የተከወነውን ቃል ግጥም በክዋኔ ወቅት ይዘቱን ሳይለቅ እንዳለ የሚቀርብበት

መንገድ ነው። የእዚያው በዚያው አደራረስ ስልት ደግሞ ከዋኙ የከዋኔውን ሁኔታ ተመስርቶ የነበረውን ቃል ግጥም የራሱን አዳዲስ ሃሳቦች እየጨመረ በማሻሻል የሚያቀርብበት ነው። ተመስጦ አደራረስ ስልት ከዋኙ በአንዳንድ አነቃቂ ነገረ ጉዳዮች ተነሳስቶ የሚገጥማቸውን ግጥሞች የሚመለከት ነው Finnegan (1977, 52-87) ።

በአንድ ጊዜ የተፈጠረና አወቃቀሩ በቃል የተሸመደደ ከሆነ ለውጥ ሳይደረግበት ሊከወን ይችላል። ነገር ግን ከጊዜ ቆይታ ምክንያትም ሆነ ከመርሳት እንዲሁም ከአጋጣሚው ለማጣጣም የቃላትም ሆነ የዐረፍተ ነገር ለውጥ ሊደረግ ይችላል። ነገር ግን ቃላቱ በሌላ ቃላት ሳይተኩ የሚቆይበት አጋጣሚ ውስን ነው። Finnegan እንደሚሉት በትምህርት መልክ ካልተሰጡ በስተቀር።

እኔ ለጥናት የመረጥኩት የእረኛ ቃል ግጥምም እረኞች በእረኝነት ጊዜ በርካታ ቃል ግጥምን በተለያየ መልኩ ቢያቀርቡም አጠቃላይ ገፅታው ግን ከላይ ከተብራራው የአደራረስ ስልት ጋር ተመሳሳይ ነው። ምክንያቱም በሽምደዳ ጊዜ አንድ ቦታ የተባለ ሌላ ቦታ ሲባልና ሙሉ ጉዳዩ እንዳለ የሚሰማበት አጋጣሚ ቀላል አይደለም። በመሆኑም ከላይ የተብራሩትን የአደራረስ ስልት ተከትለው በርካታ ቃል ግጥሞች ይደረሳሉ።

ሁለተኛው የቃል ግጥም ቃላዊነት መስፈርት "ቃላዊ ክዋኔ" ነው። ቃላዊ ክዋኔ ለቃል ግጥም መኖር አንዱ ምክንያት ነው። አንድ የቃል ግጥም ለዛውን ሳያጣ ሙሉ መልእክቱን እንደያዘ ለመተላለፍ ቃላዊ ክዋኔው ወሳኝ ነው። ክዋኔ አስፈላጊ የሚሆነው በቃል ግጥም ህልውናነቱ ብቻ አይደለም። ቃል ግጥምን ከሚከወንበት አውድ አንፃር ለመሰብሰብና ለመተንተን የማይቀር ጉዳይ በመሆኑም ነው። ቃል ግጥምን ለማጥናት ለቃል ግጥሙ ስበብ እና ውጤት የሆኑትን ሁነቶች ከነአጃቢዎቻቸው ማጤኑ ጠቃሚ ነው። ለዚህ ደግሞ ወሳኙ ክዋኔ ነው።

የቃል ግጥም በመዘፈን ወይም በመዜም ፣ በመነብነብ እና በንግግር ሊቀርብና በአንድ ከዋኝ ፣ በቅብብሎሽና በመሳሪያዎች ታጅቦ ሊከወን እንደሚችል Finnegan (1977 ፣120-121) ያስረዳሉ።

የቃል ግጥም ቃላዊነት ሶስተኛው መስፈርት ቃላዊ ስርጭቱ ወይም ቃላዊ ተስተላልፎው (oral transmission) ነው። ይኸውም በቃል የተፈጠሩ ግጥሞች በቃል ከዘመን ወደ ዘመን፣ ከቦታ ወደ ቦታ መተላለፋቸውና መሸጋገራቸውን የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ሲነሳ ግን ተስተላልፎው በክዋኔው ላይ እንደተመሰረተ ማሰብ ይገባል። ምክንያቱም ሊተላለፍ የሚችለው

በአንደበት ውስጥ የተፈጠረውን ቃል ግጥም የፈጠረው ሰው ያን ቃል ግጥም የሚያስተላለፍበት ማህበራዊም ሆነ ሌላ አጋጣሚ ካላገኘና ካልከወነው ከሰውየው ጋር አብሮ ሊቀበር ይችላል። ስለዚህ የተስተላልፎው ህልውና ከክዋኔ ጋር በዕጅጉ የተያያዘ ነው።

ቃል ግጥሞች ይዘታቸውን ሳይቀይሩ ከዘመን ዘመን፣ ከቦታ ቦታ እንደሚተላለፉ ሁሉ ማሻሻያ ተደርጎባቸውም ይተላለፋሉ። ለዚህ እንደምክንያት የሚነሳው ቃል ግጥሞች በተለያየ አጋጣሚ በተለያየ ዘመንና ቦታ በአንድ ዓይነት ቅርፅና ይዘት መተላለፍ መቻላቸው ነው። ለዚህ ደግሞ በማሳያነት የሚጠቀሰው የሰው ልጅ አንድን ሀሳብ ሸምድዶ የመያዝ ችሎታው ነው። በጥቅሉ የቃል ግጥሞች ከአንድ ሰው አንደበት ከወጡ በኋላ ወደ ሌላ ሰው ጆሮ መድረሳቸው ይታወቃል። በዚህ አጋጣሚም መጀመሪያ የነበረው ቅርፅ ሊቀየር ብሎም በአዲስ መልክ ሊቀርብ ይችላል Finnegan (1977,134-153) ።

## 2.2.4. የቃል ግጥም ባህሪ

ቃል ግጥም እንደ ስነ ቃል ዘርፍነቱ የተለያዩ ባህሪያት አሉት። ከነዚህም ውስጥ ተከዋኝነት፣ ተለዋዋጭነት፣ ድግግሞሽና ተመሳሳይነት ዋና ይጠቀሳሉ Okpewho (1992,9) ። እነዚህ ባህሪያት ተያያዥነት አላቸው። ተከዋኝነቱን መሰረት በማድረግ ሌሎቹን ባህሪያቶች ልናያቸው፣ ልናነባቸው እና ልናደምጣቸው እንችላለን። በመሆኑም ከዋኙ ባህሉ በሚፈቅደውና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ባለው መልኩ ሊከውን ግድ ነው።

ሁለተኛው የቃል ግጥም ባህሪይ ተለዋዋጭነት ነው። አንድ ቃል ግጥም ተፈጥሮ፤ በቃል ይከወናል። በዚህ ጊዜ አንድ አድማጭ ይህን የሰማውን ቃል ግጥም በሌላ አጋጣሚ ሊከውነው ይችላል። ቃል ግጥም ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ወይም ከአንድ ባህል ወደ ሌላ ባህል ሲሸጋገር ተለዋዋጭነት ይታይበታል። ምክንያቱም እንደ ፅሁፍ ግጥም እንዳለ የመቆየቱ ሁኔታ ላያጋጥመው ይችላል። ተለዋዋጭነቱም በክፊል የቃላት፣ የሀረጋት፣ የስንኝ ወይም የአረፍተ ነገር ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሆን ይችላል ዘሪሁን (1992፣25) ።

Finnegan (1970,373-374) እንደሚገልፁት አንድ ቃል ግጥም በተለያዩ ሰዎችና በተለያየ ጊዜ ሲከወን ሁልጊዜ አንድ አይነት አይደለም። ለውጥ ሊኖረው ይችላል። ይህም የሚከሰተው በመርሳት፣ የራስን ችሎታ በመጠቀም፣ አሻሽሎ ለማቅረብ ወይም ደግሞ ከአጋጣሚው ጋር ለማስማማት ሊሆን ይችላል።

በሶስተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው የቃል ግጥም ባህሪ ድግግሞሽ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ተመሳሳይነት ሊነሳ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ትይዩነቱን ስናስብ ድግግሞሽን ማንሳታችን አይቀርምና፡፡ ድግግሞሹ በቃላት ደረጃ፣ በሀረጋት፣ በስንኞች፣ በሁኔታዎች፣ በሃሳብና በአያያዥ ቃላት ደረጃ ሊሆን ይችላል፡፡ አብዛኛው የቃል ግጥም ገጣሚ ቃል ግጥሙ የአካባቢውን ዳራ መሰረት አድርጎ እስከፈጠረው ድረስ ከሁኔታዎች ጋር ማጣጣሙና የራሱን ችሎታ ተጠቅሞ መግጠሙ አይቀሬ ነው፡፡ ስለሆነም ድግግሞሽ ተለዋዋጭነትና ተመሳስሎ ቃል ግጥሙ በሚከወነበት ወቅት የሚታዩ ባህርያት ናቸው፡፡

## 2.2.5. ክዋኔና የክዋኔ አላባውያን

አንድን ነገር ለማከናወን ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ያስፈልጋሉ፡፡ ድርጊቱን የሚያከናውን አካል /ተዋናይ/ እና ተመልካች፡፡ የሁለቱን ግንኙነት ማጥናትና መገንዘብ ደግሞ የፎክሎር ባለሙያዎች ዋና ተግባር ነው ፡፡ ለመሆኑ ክዋኔ ማለት ምን ማለት ነው? እንደ Bauman (1986 ,41) ገለፃ፡-

> In one common usage performance is the actual execution of an action as opposed to capacities, models, or an abstraction from it. In the performing arts this distinction can be seen in the contrast between composed guidelines or models for artistic presentational rendition of those works before an audience.

ከጥቅሱ እንደምንረዳው ክዋኔ አንድ የፎክሎር አይነት በሚታይ እውነተኛ ድርጊት ውስጥ ገብቶ የሚቀርብበት ሁኔታ ነው፡፡ የሚቀርበው ድርጊት ካለው የከዋኙ ብቃትና የአከዋወን ስልት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ሲሆን ለፎክሎር አይነቱም የሚቀርበው ድርጊት የሚመጥንና ድርጊቱን (action) ታዳሚዎቹም ሆኑ ከዋኞቹ ማራኪ በሆነ መልኩ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

እያንዳንዱ ተመልካች የመድረክ ላይ ሰዎችን እንቅስቃሴና ብቃት ሥራቸውን ካቀረቡበት ማህበረሰብ ባህልና ወግ አንፃር መመልከት ይኖርበታል፡፡ አለበለዚያ ግን የከዋኞቹን ሀሳብና መልዕክት ውስብስብና ምልአ ላያደርገው ይችላል፡፡ ክዋኔ ለቃል ግጥም በግልም ሆነ በቡድን ቢከወኑ ለመኖራቸው ዋስትና ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ ፊቃደ እንዲህ ይላሉ፡-

> የአፋዊ ኪነተ ቃል ህልውናው በክዋኔ ነው፡፡ ከደራሲና ከተደራሲያኑ አንደበት በመውረድ፣ በመንገር፣ በመዘመር፣ በመተረቱ፣ በመዘፈኑና በመደርደሩ ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል፡፡ አፋዊ ኪነተ ቃል በህዝብ መሃል ካልተከወነ ወይም በሚከወንበት መንገድ ካልተቀረሰ ህልውና አጣ ማለት ነው፡፡ ካልተከወነና ካልተቀረሰ ሞተ ማለት ነው (1984፣ 3-4)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Finnegan (1977,28) "....Since, an oral poem is an essentially ephemeral work of art, and has no existence or continuity apart from its performance." ሁለቱም እንደሚነግሩን ለቃል ግጥም መኖር ክዋኔ ወሣኝ ነው፡፡ በርካታ ቃል ግጥሞች ካልተከወኑ (ካልተዘፈነ፣ ካልተዘመረ፣ ካልተጨፈረ፣ ካልተነገረና ለእይታ ካልበቃ) ለትውልድ የሚተላለፍበት ሌላ አማራጭ የለም፡፡ ሲከወን ብቻ ነው ሊያሳዝንና ሊያስደስት የሚችለው፡፡ ስለዚህ ቃል ግጥምና ክዋኔ ተነጣጥለው መታየት የለባቸውም፤ ከተነጣጠሉ ህያውነት እንደሌላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

የተለያዩ የቃል ግጥም ዓይነቶች ቢኖሩም ሁሉም የቃል ግጥሞች እንደየባህሪያቸው የራሳቸው የሆኑ ክዋኔዎች አሏቸው፡፡ በዚህም የሚከወኑበት የመከወኛ መቼት /setting/፣ ታዳሚ፣ ከዋኝ፣ ቴክስት (text) እና ወዘተ እንደራሳቸው ባህሪና ተግባር በተለያየ መልኩ እንዳላቸው Bauman (1977,13) *Finnegan* (1977,28) ፊቃደ (1984፣3) ይገልፃሉ፡፡ ይህ የሚያሳየን የስነ ቃል እስትንፋስ ክዋኔ እንደመሆኑ መጠን ክዋኔ የሚቆምባቸው የራሱ የሆነ መታከኪያዎች (ኢለምንቶች) አሉት ማለት ነው፡፡

> The term "performance" has been used to convey a dual sense of artistic actions-the doing of folklore- and artistic event the performance situation, involving performer, art form, audience and setting-both of which are basic to the developing performance approach. (Bauman 1977, 4-5)

በማለት ከዋኝ፣ታዳሚ፣አውድ፣መቼትና አጋጣሚ የጠበቀ ቁርኝት እንዳላቸውና ለክዋኔ ተኮር ንድፍ ሃሳብ መሰረት እንደሆኑ ይነግሩናል፡፡

ከዋኝ ማለት በአንድ አጋጣሚ የሚቀርብን የቃል ግጥም በመሪነት የሚያቀነቅን (የሚነበንብ) ሰው ማለት ነው፡፡ ይህም ቃል ግጥም ከትውልድ ትውልድ ብሎም ከቦታ ቦታ እንዲሸጋገር የሚያስችል ወሳኝ አካል ነው፡፡ ስለሆነም አብዛኛውን የቃል ግጥም አይነቶች የሚከውኑ በሙያው የተካኑ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ ይህንን ሀሳብ Dorson (1972,86) ህዝባዊ ግጥም ታዋቂ በሆኑና ልዩ ችሎታ ባላቸው ሰዎች የሚፈጠር እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

በርካታ ቃል ግጥሞች ራሳቸውን የቻሉና ላቅ ያለ ሙያ ያላቸው ከዋኞች አሏቸው፡፡ ጥናቱ በሚያተኩርበት ማህብረሰብም የእረኞች ቃል ግጥምን በተለያየ መንገድ በመከወን የሚታወቁ የቃል ግጥም ከዋኞች አሉ፡፡ እነዚህ ከዋኞች በአካባቢው አጠራር "ትንቢተኞች" በመባል የሚታወቁ ናቸው፡፡ ይህ ስያሜ ግን ሁሉንም እረኞች አያካትትም፡፡

እንደ Finnegan (1977,216) አገላለፅ ታዳሚ ማለት በክዋኔ ጊዜ የሚቀርበውን ክዋኔ የሚከታተል፤ ከዋኙን በማበረታታት በክዋኔው የሚሳተፍ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ከዋኙ ክዋኔውን የሚያቀርብለት አካል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ታዳሚን የሚሹ እንዳሉ ሁሉ ታዳሚን የማይፈልጉ የስራ፣ የእርሻ እና የእረኛ ቃል ግጥሞችም አሉ፡፡ እነዚህም ቢሆን አልፎ አልፎ የሚሹበት አጋጣሚ አለ፡፡ ለምሳሌ የእረኞች ቃል ግጥም ላይ ለብቻ የሚባል እንዳለ ሁሉ በተቀባይ፣ አውራጅና በተለያዩ ክዋኔዎች ታጅበው የሚቀርቡ ቃል ግጥሞች አሉ፡፡

አውድ አንድ የፎክሎር አይነት የሚታይበት ወይም የሚከወንበት አጋጣሚ ነው፡፡ የቃል ግጥም ደግሞ አውድ ከሚያስፈልጋቸው የፎክሎር አይነቶች አንዱ ሲሆን የቃል ግጥም ደርዳሪዎችም በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ የሚደረድሯቸውን ቃል ግጥሞች ታዳሚ በተቀበለው የአከዋወን ስልት ይከውኗቸዋል፡፡

የመስክ ምሁር የሆኑት Dan Ben-Amos (1993, 209) አውድን "In contemporary usage the term "context" refers to a broadly defined background of a composition or a structure, as well as to the parts that precede and follow a given passage." በማለት አውድን ሰፋ ባለ መልኩ ማየት እንደሚቻልና ለአንድ የፎክሎር አይነት አደራረስ (composition) መነሻ ከመሆኑም በላይ የፎክሎር አይነቱን አወቃቀራዊ አካሄድና በውስጡ የሚይዛቸውን ቀደሚና ተከታታይ ሂደቶች እንደሚያሳይ አብራርተዋል፡፡

Bauman (1983, 362-366) እንደሚገልፁት አውድ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም ባህላዊ አውድ (Cultural context) እና ማህበራዊ አውድ (Social context) ናቸው፡፡ እንደ ምሁሩ ገለፃ ባህላዊ አውድ በስሩ የፍቺ አውድ (Context of meaning)፣አውዳዊ የተግባቦት ስልትና (Context of communicative system)፣ ተቋማዊ አውድ (Institutional Context) የሚሉ ሶስት አይነት አውዶችን ይይዛል፡፡ ማህበራዊ አውድ ደግሞ ማህበራዊ ደረጃ (Social Base)፣ ግለሰባዊ አውድ (Individual Context) እና ሁኔታዊ አውድን (Situatinal Context) ይይዛል፡፡ እንደ Bauman (1983,367) ገለፃ አንድ የፎክሎር ተመራማሪ ከመስክ ላይ የሰበሰባቸውን

መረጃዎች ከላይ በቀረቡት ስድስት ዋና ዋና አውዶች አደራጅቶ በማቅረብ ከስህተት የፀዳ የመስክ መረጃ ሰብስቦ ጥናቱን ምልዑ ማድረግ ይቻላል፡፡

መቼት ማለት ቃል ግጥም የሚቀርብበትን ጊዜና ቦታ የሚያመለክት ነው፡፡ ማንኛውም ቃል ግጥም በመዜምም ይቅረብ በመነብነብ የሚቀርብበት የራሱ የሆነ ጊዜና ቦታ (አጋጣሚ) ይኖረዋል፡፡ ለክወናውም ሆነ ለአፈጣጠሩ የራሱ ጊዜና ቦታ አለው እንጂ በዘፈቀደ አይዘፈንም፣ አይጨፈርም፣ አይቀርብም፡፡ በሰርግ ላይ የሙሾ ግጥም አይወርድም፣ በለቅሶ ቀን አይዘፈንም፣ እስክስታ አይወረድም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም የየራሳቸው መቼት አላቸው፡፡ ስለዚህ እረኞችም ቃል ግጥሞችን የሚቀርቡበት የራሳቸው የሆነ መቼት አላቸው፡፡

መልዕክት ማለት በአንድ ክዋኔ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት እንደማለት ነው፡፡ በዚህም በቃል ግጥሙ ውስጥ ከዋኙ ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በክዋኔው አማካይነት የምንረዳበት ነው፡፡ ደንብ ማለት ደግሞ አንድ ክዋኔ ሲከወን በሚከወንለት ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው የራሱ የሆነ ህግና ደንብ ነው Martha (2005,127-139)፡፡ ለዚህም እንደምሳሌ እረኞች የሚያወርዷቸው ቃላዊ ግጥሞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ለምሳሌ የዘፈን ግጥሞቹን ፣ የሽለላና የፉከራ ቃላዊ ግጥሞችን ብንመለከት የራሳቸው የሆነ መቼት፣መልእክት፣አውድ እና ሌሎችም የክዋኔ ኢለመንቶች ይገለጹባቸዋል፡፡


አብዛኛውን ጊዜ “ቴክስትን” ብቻውን አናገኘውም፤ ይልቁንም በቡድን መልክ እንጂ፡፡ ሰዎች ግጥም ሲገጥሙ፣ መዝሙር ሲዘምሩና ተረት ሲተረት ድምፅ፣ ቃላት ወይም ዐረፍተ ነገር ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የእያንዳንዱን ግጥም፣ ተረት፣ መዝሙርና ወዘተ. ይዘት እንደ አካባቢው፣ እንደ ተዋናዮና እንደ ቡድኑ ሁኔታ ይለያያል ፡፡

በአጠቃላይ አንድ የቃል ግጥም አጥኚ ቃል ግጥሙን ያጠና ዘንድ ተከውኖ ማየት አለበት፡፡ ስለዚህም በክዋኔው ወቅት የእያንዳንዱን ድርጊት እንቅስቃሴ ማን፣ ለምን፣ መቼ፣ የት፣ ምን፣ እንዴት እና ለማን እንደሚከወን በትኩረት ማየት ተገቢ ነው፡፡ ለጥናት የተመረጠው የእረኞች ቃል ግጥም ክዋኔም ከላይ እደተብራራው ይታይበታል፡፡


## 3. የጥናቱ አካባቢ ዳራ

በዚህ ክፍል ጥናቱ የሚካሄድበትን አካባቢ ነባራዊ ሁኔታ የሚጠቁሙና ከዚህ ስራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው የአካባቢው መግለጫዎች ይወሳሉ፡፡ በዚህ መሰረት የአማራ ክልል ፣ የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ና የለጋምቦ ወረዳን ገፅታ የሚያሳዩ የካርታ መግለጫዎች፣ የለጋምቦ ወረዳን አጠቃላይ ገፅታ፣ የለጋምቦ ወረዳ አረኞች ማህበራዊ ህይወት፣ የኢኮኖሚ መሰረት፣ የይላዳ ባህላዊ የትግል ስነ-ስረዓት እና የአስተዳደራዊ ታሪክ ምንነትና እንዴትነት ይብራራል፡፡


### 3.1. የካርታ የአማራ ክልል፣ የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞንና የለጋምቦ ወረዳ ካርታ



የአማራ ክልል ካርታ ምንጭ፡- (የደቡብ ወሎ ዞን ባህልና ቱሪዝም)



የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ካርታ ምንጭ፡- (የደቡብ ወሎ ዞን ባህልና




የለጋምቦ ወረዳ ካርታ ምንጭ (የለጋምቦ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም)

## 3.2. የለጋምቦ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ

የለጋምቦ ወረዳ በደቡብ ወሎ ዞን ከሚገኙት አስራ ስምንት ወረዳዎች መካከል አንዱ ነው። ወረዳዋ ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ከባህር ዳር 580 ኪ.ሎ ሜትር ከአዲስ አበባ 500 ኪ.ሎ ሜትር ከዞኑ ርዕሰ ከተማ ከደሴ በስተምዕራብ 100 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። ወረዳዋ በገጠር ወንድ 83674 ሴት 86307 ድምር 169981 በከተማ ወንድ 4491 ሴት 4549 ድምር 9039 በአጠቃላይ 179020 የህዝብ ብዛት ይገኝባታል። ለጋምቦ በምስራቅ ወረኢሉ እና ደሴ ዙርያ፣ በሰሜን ሳይንት፣ ተንታና ኩታበር ወረዳ፣ በምዕራብ ደብረሲና መካነ-ሰላም ወረዳ ፣ በደቡብ ከላላ ወረዳዎች ያዋስኗታል። በውስጧ 32 የገጠር ቀበሌና 3 የከተማ ቀበሌዎችን በመያዝ በድምሩ በ35 ቀበሌ የተከፋፈለች ናት። የወረዳዋ አየር ንብረት ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ ውርጭ ነው የለጋምቦ አጠቃላይ ገፅታ (2004፣ 2 ፣ያልታተመ)

ወረዳው አብዛኛው ደጋማ ሲሆን ውርጭም በመጠኑ ይታይበታል። በወይና ደጋው አካባቢ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ጓያ፣ አተር፣ ምስር፣ ባቄላ፣ ገብስ፣ ሽምብራ በብዛት ሲመረት የደጋማው አካባቢ ምርቶች ደግሞ ገብስ፣ ምስር፣ አተርና አጃ ናቸው። ወረዳው ዘመናዊ የሆነ አኗኗርና አለባበስ የሚታይበት አካባቢ ነው። የለጋምቦ ወረዳ አሁን ላይ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠ በመምጣቱ ከቅልስ ቤት ወደ ቆርቆሮ፣ ከመሬት መኝታ ወደ አልጋ በመለወጥ ላይ ይገኛል። በወረዳው ውስጥ ሁለት ሀይማኖቶች በብዛት የሚታዩ ሲሆን አንደኛ ሙስሊም ሁለተኛ የክርስትና ሃይማኖት ነው። አብዛኛው የወረዳው ህዝብ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ነው የለጋምቦ አጠቃላይ ገፅታ (2004፣ 2 ፣ያልታተመ)።

## 3.3. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ማህበራዊ ህይወት

አብዛኛው የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ከብቶችን የሚሠማሩት ጊምባ ሜዳ ፣ቱሉ ጎራ፣ ጭሩ ሜዳ እና መልካርያ በተባሉ ቦታዎች ነው። በነዚህም ሜዳዎች ከብቶች የሚግጡት ሳር እና በአካባቢው ያለ ወንዝ (የከብቶች ውሃ ማጠጫ ቦታ አለ)። አካባቢው የከብት እርባታ በሠፊው የሚከናወንበት ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሃብታም ገበሬ ራሱን ማስተዳደር ያልቻለውን ሠው ይቀጥራል። የቅጥር ሁኔታውም በሦስት መልኩ ነው (ቃለ መጠይቅ፣አቶ ከበደ አደፍርስ ፣ሚያዚያ 8/2004) ።

የመጀመሪያው በደመወዝ (በብር ወይም በእህል) የሚቀጠሩት ነው። እረኛው ደሞዝ በወር ወይም በዓመት ሊሰጠው ይችላል። ተቀጣሪው ልጅ ከ 10 ዓመት በታች ከሆነ "ነፍስ

እስኪያውቅ" በማለት የሚከፈለውን እህልም ሆነ ብር ቤተሠብ ይወስዳል። ልጅ በወጣትና በጎልማሳነት እድሜ ያለ ከሆነ የደሞዝ ክፍያውን ራሱ ይቀበላል። እረኛው ከከብት ጥበቃ ውጭ ሌላ የእርሻና መሠል ሥራዎችን መሥራት የሚችል ከሆነ የደመዎዙ መጠን ይጨምራል ። እንደ ሥራው ይከፈለዋል በማለት ደመወዝ በሥምምነት የሚለውን መርህ እንደሚከተለው ገልፀዋል (ቃለ መጠይቅ፣አቶ ከበደ አደፍርስ ፣ሚያዚያ 8/2004) ።

ሁለተኛው የቅጥር ሁኔታ ጋብቻን መሠረት ያደረገ ነው። እነዚህ እረኞች በአንድ ሀብታም ቤት የምትወለድ ሴት ልጅን (በአገልጋይነት ያለች) ለጋብቻ ያስጠይቃሉ። በዚህ ጊዜ ህጻንዋ ለጋብቻ እስክትደርስ በከብት እረኝነትና መሰል ስራዎችን በቤተሰቦቻ ቤት በማገልገል ይቆያል። እድሜዋ ለጋብቻ ሲደርስ ያካበቱትን ሃብት ይዘው ጋብቻ ይፈፅማሉ። ይህ በአካባቢው አጠራር "ቆጥ አስር" ይባላል። ይህ የቅጥር ሁኔታ ለወንዶች ብቻ የሚደረግ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት በአብዛኛው የውጭና የከብት ጥበቃን ሥራ በአካባቢው በወንዶች ብቻ የተለመደና ሴቶች ቤት ውስጥ ያለን ሥራ በመስራት ስለሚያገለግሉ ነው። ይህ ደግሞ ባህሉ ያስተማረንና ከአባቶቻችን የወረሥነው ነው ይላሉ (ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሪስ የሱፍ፣ የካቲት 8/2004) ።

ሦስተኛው የቅጥር ሁኔታ ለእረኛው አስፈላጊውን ወጭ በመቻል ትምህርቱን እያስተማረ ከብት እንዲጠብቅ የሚያደርግበት ውል ነው (ቃለ መጠይቅ፣ከበደ ፋሪስ ፣ሚያዝያ፣8/2004) ።

እረኞች የጥበቃ ሥራቸውን ሲያከናውኑ ሊያጋጥሟቸው ከሚችሉ አንዳንድ ችግሮች እየተቋቋሙ ነው። ለምሳሌ በበጋ፣ የፀሐይ ወቅት በክረምት በብርድና በዝናብ ሲጠነክር በወኔ ሥራቸውን ያከናውናሉ። ከብቶቻቸውን እንዳይሠረቁ፣ ገደል ገብተው እንዳይሠበሩ፣ እንዳይዋጉ ፣ውሃ ውስጥ እንዳይገቡ ወዘተ ይከላከላሉ። በለጋምቦ አካባቢ የሚገኙ እረኞች ሁለት አይነት መስተጋብር አላቸው (ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሪስ የሱፍ፣ የካቲት 8/2004) ።

የመጀመርያው እርስ በርሳቸው ያላቸውን መስተጋብር ነው። ይህም ገና ከሩቅ ሲተያዩ በያሉበት ሆነው "ውው" የሚል የንግግር ድምጽ በማሰማት ስላምታ ይለዋወጣሉ። በአካል ከተግናኙ በኋላ ደግሞ ይላፋሉ፣ይቃለዳሉ እየተቀባበሉ ይዘፍናሉ፣ይፎክራሉ፣ያቅራራሉ ወዘተ። ይህ ጠንካራ ግንኙነታቸው በደስታ ብቻ ሳይሆን በችግርም ጊዜ ነው። ከመካከላቸው አንዱ ጓደኛቸው ቢታመም ከብቶቹን ይጠብቁለታል፤ ከብት ቢጠፋበት ያፋልጉታል። ሁለተኛ ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ጋር ያላቸው ግንኙነት ነው። ቤተሰቦቻቸውን እርሻ በማረስ ፣ሰብል በመጠበቅ፣አረም በማረም እና በአጨዳ በማገዝ ከሌሎች ስዎችም ጋር እንዲሁ መስተጋብር አላቸው የለጋምቦ ዐጭር ቅኝት (2003፣5፣ ያልታተመ)።

## 3.4. የኢኮኖሚ መሰረት

የለጋምቦ ወረዳ ህዝብ በዋነኝነት ከሚተዳደርባቸው የኢኮኖሚ መሰረቶች ውስጥ ግብርና እና የከብት እርባታ ተጠቃሽ ናቸው። በዚህም ወረዳው በአመት ሁለት ጊዜ የእርሻ ምርት ስራ ያካሄዳል። ወረዳው በዞኑ ከሚገኙ ዝናብ አጠር ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ነው። በተጨማሪ አብዛኛው መልክአምድር ተራራማ በመሆኑ ለም አፈር በጎርፍ እየታጠበ የሚወሰድበት አጋጣሚ ሰፊ ነው። በተጨማሪ የከርሰ ምድር ውሃን በመጠቀምና የመስኖ ስራን መሰረት በማድረግ አርሶ አደሩ በአመት እስከ ሶስት ጊዜ እያመረተ እንደሆነ እና ወረዳው በአመት ከበልግም ሆነ ከመኸር 558621 ኩንታል ምርት እንደሚያገኝ ገልጸዋል (ቃለ መጠይቅ፣አሰፋ ሙሃመድ፣ የካቲት 12/2004)።

ከዚህ በተጨማሪ ወረዳው በከብት እርባታ ይታወቃል። ይህ እንዲሆን ደሞ የወረዳው የአየር ንብረትና መልክአምድር ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው። በወረዳው ውስጥ በአሁኑ ወቅት 93197 የዳልጋ ከብት 28668 የጋማ ከብት 27773 ፍየልና በግ የ2439 የዶሮ ሀብት በአጠቃላይ 242087 እንስሳት ይገኛሉ። በወረዳው የሚገኙ አርሶ አደሮች በተለያዩ ስልጠናዎች በመታገዝ ከተለያዩ ምርጥ ዝርያዎች ጋር በማዳቀል ኢኮኖሚያዊ ፍጆታን ለማሳደግ ችለዋል። ለዚህም እንደ አብነት የሚጠቀሰው የወረዳዋ የአየር ንብረት ለምርጥ ዝርያዎች ምቹ ከመሆኑ የተነሳ በ3 ወር ለእርድ መድረስ መቻላቸው ነው። ከዚህ በተጨማሪም የከብት ማደለብ ስራም በተሳካ መልኩ እየተካሄደ እንደሆነ እና በአንድ አመት ውስጥ እስከ 22 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት እንደቻሉ ተገልጻል  የለጋምቦ ወረዳ አጭር ቅኝት (2002፣16፣ ያልታተመ)።

## 3.5. የይላዳ ባህላዊ የትግል ስነ-ስረዓት

በደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ውስጥ ከሚገኙና የረጅም ጊዜ የአስተዳደር፣ የባህልና የታሪክ ማዕቀፍ ካላቸው ወረዳዎች ውስጥ አንዱ የሆነው የለጋምቦ ወረዳ ተለይቶ ከሚታወቅባቸው በርካታ ባህላዊ ሁነቶች ውስጥ የእረኛ ቃል ግጥም እና ባህላዊ የትግል ጨዋታ ተጠቃሽ ነው።

ይህም ማህበራዊ አመጣጥን ሃይማኖትንና ዘርን ሳይለይ እጅግ ልዩና ድንቅ በሆነ ባህላዊ ስርዓት በቡሔ የበዓል አከባበር ወቅት የሚከናወን እንደሆነና የራሱ የሆኑ ልዩ እሴቶች እንዳሉት የጨዋታው ባህላዊ ዳኛና የ75 አመት ዕድሜ ባለፀጋ የሆኑት ሙሃመድ አሰን በጉዳዩ ዙሪያ ገለጻ አድርገውልኛል። ይህ ባህላዊ የትግል ጨዋታ ስለተጀመረበት ጊዜ እርግጠኛ መረጃ ማግኘት ባይቻልም  በተደራጀ ሁኔታ መካሄድ የጀመረው በአፄ ዮሀንስ ዘመነ-መንግስት ነው።

በወቅቱ ጨዋታው ከግራር ልጫ ከተሰራ ጅራፍ በሚካሄድ ግርፊያ ይካሄድ የነበረ ቢሆንም ይህ ሁኔታ ጉዳት እያስከተለ በመምጣቱ በዚያው ወቅት በአካላዊ የመጣጣል ትግል እንዲካሄድ ተወስኖ እስከዛሬ ድረስ በዚሁ ዓይነት ስልት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ አቅም እየተገመተ ከተመጣጣኝ ሰው ጋር በሚካሄደው በዚህ ባህላዊ የትግል ጨዋታ ውስጥ ከታዳጊዎች እስከ ጎልማሶች ድረስ ሁሉም ሰው የሚታገል የነበረ ሲሆን ሰው እየበዛ በመምጣቱ በአሁኑ ወቅት በተወሰነ ሰዓት በተወሰኑ እረኞችና ግለሰቦች ብቻ የሚደረግ ሆኗል (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 18/2004 ) ፡፡

ከወለቃ ወንዝ ወዲያና ወዲያ ማለትም የገነቴና የይላዳ ቀበሌዎች በቡድን ተደራጅተው አታጋዮችን ባህላዊ ዳኞችን በመምረጥ መልካሪያ በሚባል ደልዳላ መልካ ላይ በበሽሎው ዳርቻ የሚከናወን ሲሆን ከጨዋታው መጀመር አስቀድሞ የውሃ ዋና ይካሄዳል፡፡ ጨዋታው ከሁለቱም ቡድን ማለትም ከወንዝ ወዲህና ወዲያ ከሚመጣው ቡድን በሚመረጡ (የገነቴና የይላዳ) 2 ወይም 3 አታጋዮች የሚመራ ሲሆን በዚህ ባህላዊ የትግል ጨዋታ ውስጥ ጉዳት ቢያጋጥም ተጨዋቹ (ታጋዩ) ራሱ የሚወጣው ሲሆን "በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ" የሚለው ብሂል እዚህም ይሰራል የለጋምቦ ወረዳ አጭር ቅኝት (2002፣16፣ ያልታተመ)፡፡

ይህን ባህላዊ ጨዋታ ምክንያት አድርጎ በክፉ ልቦና በመነሳሳት የጨዋታውን ህግ የሚጥስ ቢኖር በጥንቱ ወግና ባህል በጨዋታው ዳኞች ቅጣት የሚጣልበት ሲሆን ይህም ቅጣት ርግማንንና መገለልን ጨምሮ ከ300-400 ብር ወይም በሬ አርዶ አገሩን ይቅርታ እስከመጠየቅ ይደርሳል፡፡ የርግማን ይዘት አስመልክቶም የጨዋታው የምንጊዜም የክብር አባት የሆኑት አቶ ማመድ እንድሬ ሲገልፁ፡-

*"ልጁን ከደረቱ*
*ክብቱን ከበረቱ ይነጥልበት*
*ዓመት አይቀላቅለው*
*ወርም አያድርሰው"*

ይህን እና ሌሎች ማህበራዊ መገለልና መነጠልን የሚያመለክቱ ርግማኖች ይረግማሉ፡፡ በመከፊቻ ስረዓቱ የነበረው የጋራ የመመራረቅ ስርዓት በመዝጊውም በአባቶች ይከናወናል፡፡ ለአብነት ያክል ብናይ፡-

*"በቀጣዩ አዝመራ ይግጠመን*
*በዘንድሮው ያልቀናን በቀጣዩ ድል ይግጠመን*
*በሰላም በጤና እንገናኝ*
*ሞት አይለየን...አይነጥለን"*

በሚል የቡራኬ ቃል ይጠናቀቃል። ይህ ባህላዊ የትግል ጨዋታ የህብረተሰቡን የጋራ ባህላዊ እሴቶች ከማጠናከሩም በላይ የመቻቻልን፣ የአብሮነትንና የወደፊት የጋራ ዕድልን የሚያመለክት እንደሆነ አልይ ይማም ይናገራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣14፣2004) ።

## 3.6. የለጋምቦ ወረዳ አስተዳደራዊ ታሪክ

ለጋምቦ የኦሮምኛ ቃል ነው። ለጋ ወንዝ ማለት ሲሆን አምቦ ማለት ደግሞ ጨው ጨው የሚል ውሃ ማለት ነው። ስለዚህሙሉ ትርጉሙ ጨው ጨው የሚል ወንዝ ያለበት ቦታ ማለት ነው። ለጋምቦ በሶስት ገባር አገር በቁጥር 3000 እንደነበርና 1000 ገባር ፊጣ፣ 1000 ገባር መሀል አገር፣ 1000 ገባር ደረባ ተብሎ ይታወቅ ነበር። ይህ ሶስት ገባር በ1 ገዥ ሲተዳደር በየገባሩ ደግሞ 2 ምስለኔ በምክትል ገዥ ይሾምለት ነበር። ጣሊያን ከመግባቱ በፊት ለጋምቦ ከሻለቃዎች ጦር ሌላ 900 ወታደር ፊታውራሪ መብረቁ ሃይሌ በተባሉ ሹም ሻለቃነት ይተዳደር ነበር የለጋምቦ ወረዳ አጭር ቅኝት (2002፣17-18፣ያልታተመ)።

በየጊዜው እየተሾሙ ከመጡ መኳንንቶች ውስጥም ራስ ወሌ ጉግሳ፣ የራስ ወሌ ልጅና ስሙን በአባታቸው ያወጡለት ራስ ወሌ ጉግሳ ወሌ፣ ራስ ሀብተ ማርያም፣ ደጃች ሽበሽ ሚኒሊክ ደጅአዝማች ተስፋ ትኩ፣ ራስ እምሩ ኀይሌ እነዚህ በሙሉ ጣሊያን ከመምጣቱ በፊት በቅደም ተከተላቸው እየተፈራረቁ የገዙ ገገርዎች ናቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን ለጋምቦ ከተማ አልነበራትም የነዚህ ሁሉ ሹማምንት መቀመጫ ግን የአሁኗ አቀስታ ነበረች።

ጣሊያን በድል ከተመለሰና ንጉሱ ከተረጋጉ በኋላ አሁንም መኳንንቶች እየተፈራረቁ ለጋምቦን መግዛት ጀመሩ። ጣሊያን ከሄደ በኋላ ቀኝ አዝማች ስዩም ዋለሉ፤ ፊታውራሪ በቀለ ደነገጤ፣ ፊታውራሪ ከበደ ያዘው፣ ፊታውራሪ ወሌ ጉግሳ (እኒህ ሰው ከቀደሙት ጋር በስም ሞክሼ ናቸው) ደጅ አዝማች ከበደ አራጋው፣ ቀኝ አዝማች ወንድአፈራ አውራሪስ እና ብላታ ውቤ ደነገጤ በቅደም ተከተላቸው ለጋምቦን ገዝተዋል። ከብላታ ውቤ ደነገጤ በኋላ ፊታውራሪ ኃይለማርያም በላይ የተባሉ ገዥ ወደ አካባቢው መጡ። በዚህ ጊዜ ዘመኑ 1940ዓ.ም ነበር። አቀስታ በእኒህ ገዥ ወደ ወረዳ ከተማነት እንድትከለል ተደረገ የለጋምቦ ወረዳ አጭር ቅኝት (2002፣17-18፣ያልታተመ)።

የከተማው ክልልም የደለል ወንዝ በምዕራብ የቁንዲ ጎራ እንደሻሽ በመለስ በምስራቅ፣ ከጃንጅር ጎራ እስከ ወታደሮች ካምፕ ድረስ የከተማዋ ክልል ተብሎ ተከለለ። በአካባቢው የነበሩት መሳፍንቶችና መኳንንቶችም፣ቦታ እየተቀበሉ ቤት መስራት ጀመሩ። ከፊታውራሪ ሀይለማርያም

በላይ በኋላም መቶ አለቃ ከበደ ገብረህይወት፣ ፊታውራሪ ሽፈራው እርገጤ፣ ፊታውራሪ ሊበን ሐይለስላሴ ሲሆኑ ደርግ ሲመጣ አካባቢ የራስ ገብረህይወት የልጅ ልጅ የነበሩት ፋሲል ሊበን የተባሉት ገዥ ሲያስተዳደሩ ነበር የለጋምቦ ወረዳ አጭር ቅኝት (2002፣17-18፣ያልታተመ)።

# 4. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃልግጥም አደራረስ፣ አከዋወንና ተስተላልፎ

የዚህ ክፍል ትኩረት የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥምን በምን አይነት ዘዴ እንደሚፈጥሩ እና እንደሚደርሱ፤ የፈጠሩትን (የደረሱትን) ቃል ግጥም፣ በምን አይነት መንገድ እንደ ሚከውኑት እና እንደሚያሰሙት እንዲሁም የቃል ግጥሞቹን እንዴት ከቦታ ቦታ እና ከዘመን ዘመን እንደሚያሸጋገሩ እና ተስተላልፏአቸው ምን እንደሚመስል መግለጽ ነው።

## 4.1. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም አደራረስ

የለጋምቦ እረኞች ቃል ግጥም አፈጣጠር ወይም አደራረስ (compostion) ምን እንደሚመስል ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን። እንደ መረጃ አቀባዮች ኑርዮ ጋሻው እና እንድሪስ የሱፍ ማብራርያ በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ እረኞች አዳዲስ ቃል ግጥሞችን በፉከራ፣ በቀረርቶ፣ በሆታ፣ በዘፈንና በተለያየ መልኩ ይሰማሉ። ሰምተውም ይይዛሉ፣ እነዚህን የያዟቸውን ቃል ግጥሞች ከብት ሲጠብቁ (በእረኝነት ስፍራ) መልሰው ያቀነቅኑቸዋል። በተለይም ቀረርቶ እና ፉከራ ሰዎች የሚሰሙበት አጋጣሚ ሰፊ እንደሆነ ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 22/2004፣ ካሴት ቁጥር፣ 3 ፣ሀ)።

የፉከራና የቀረርቶ ቃል ግጥሞችን እረኞች አይፈጥሩም። የሚደርሷቸው በሰርግ፣ በለቅሶ፣ በደቦ፤ በሽምግልና እና መሰል አጋጣሚዎች ላይ ትልልቅ ሰዎች ናቸው። ነገር ግን እረኞች ከእነሱ በመስማት ቃል ግጥሙን በእረኝነት ስፍራ ይጠቀሙበታል። ከዚህም በተጨማሪ ጥንት ጀምረው ይባሉ የነበሩ ግጥሞችንም ሲገጥሙ ይታያል። ይህ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ከሌላው ማህበረሰብ ሰምተው፣ ሸምድደውና አስታውሰው እንደሚያቀርቡ ያመላክታል። ይህን ጉዳይ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ቱሉ አውልያ በሚባለው ቦታ በፉከራ ያቀረቧቸውን ቃል ግጥሞች በአስረጅነት እንመልከት፡-

*50- ቀጭ ቀጭ እንደበረዶ*
*በልጅነቱ በረሃ ለምዶ።*

*158 - ቤታችን ተቃጥሎ አስተኝቶት ባመድ*
*አሁን ብንታረቅ ልንሆን ወይ ዘመድ።* [3]

---

[3] መረጃ ሰጭ ፡-እንድሪስ አሰን (እድሜ 14)፣ ገነቴ ቀበሌ፣ እረኛ፣የካቲት 5/2004፣መልካርያ። እንዲሁም ኑርዮ ጋሻው (እድሜ 12)፣ቱሉ አውልያ ቀበሌ ፣እረኛ፣የካቲት 22/2004፣ቱሉ ጎራ።

ከላይ በተራ ቁጥር 50 እና 158 የተገለጹትን ቃል ግጥሞች በተሰበሰበው መረጃ ማየት እንደተቻለው በተመሳሳይ ሁኔታ በጊምባ እና ጭሩ አካባቢ ያሉ አረኞችም ያለምንም የቃል ለውጥ አቅርበዋቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተራ ቁጥር 50 የቀረበውን ቃል ግጥም በምናይበት ጊዜ ጥንት ጀምሮ ሲባል የነበረ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የሚያሳየው ቃል ግጥም ዘመን ተሻጋሪና በሽምደዳ የሚቀርብ እንደሆነ ነው፡፡ ይህን የሚያሳዩ ቃል ግጥሞች በአባሪ ውስጥ በተራ ቁጥር 28፣33፣51፣52፣53፣86 እና 221 ላይ የተጠቀሱት ናቸው፡፡

የሊጋምቦ ወረዳ እረኞች የቃል ግጥምን በመሸምደድ እንደሚያቀርቡ ሁሉ በእረኝነት ስፍራ በቀልድ መልክ በቃል ግጥም ይሰዳደባሉ፣ የአካባቢውን የብርድ ሁኔታ ለመቃቃም ይዘፍናሉ ፣ይጨፍራሉ በዚህ ጊዜም በቃል ግጥሞቹ ላይ የቃል፣ የሃረግና የስንኝ ለውጥን በማድረግም እንደገና ይደርሳሉ፡፡ ይህን ሀሳብ ወጣት ኑርዮ ጋሻው ሲያስረዳ የሚከተለውን ይላል፡፡

> *በርካታ ግጥም የምንገጥመው በአብዛኛው ቤተሰቦቻችን የሚሉትን በመስማት እና ከምናየው ወቅታዊ ነገር እንዲሁም ከጓደኞቻችን ጋር በከብት እረኝነት ስፍራ አብረን ስንውል የተለያዩ ነገሮችን በምናይበት ጊዜ እና ስንጫወት እየፈጠርን እርስ በርሳችን በቅብብሎሽ እየተነጋገርን በመለማመድ ነው (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት 15/2004 ካሴት ቁጥር 3፣ሀ) ፡፡*

በተጨማሪም ወጣት እንድሪስ አሰን ይህንን ሃሳብ ሲያጠናክር "በተለያየ ቦታ የሰማናቸውንም ሆነ ፈጥረን የተለያዩ ግጥሞችን እንገጥማለን" በማለት ይገልጻል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የሊጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥሞቻቸውን ሸምድደው ብቻ ሳይሆን የተለያዩ አጋጣሚዎችን መሰረት አድርገው በመፍጠርም ይከውናሉ፡፡ እኔም ጊምባ እና ቱሉ አውልያ አካባቢ ለመስክ ስራ በቆየሁባቸው ስድስት ቀናት ባደረኩት ምልከታ ለዘመን መንገርያነት የሚጠቀሙበትን ግጥም ሁለት ሆነው ሲከውኑ አንዱ የሚለውን ሌላው በዚያው አውድ ካለው ሁኔታ ተነስቶ ግጥም በመፍጠርና በግጥሙ ላይ የተለያየ ለውጥ በማድረግ እንደሚገጥሙ አስተውያለሁ፡፡ ስለዚህ መጠነኛ የሆነ ወይም ሙሉ በሙሉ ለውጥ ሊኖር እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ይህም የቃል፣ የሀረግ፣ የስንኝ፣ የጭብጥ እና መሰል ለውጥን ሊያመጣ ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል ቀጣዮቹን ቃል ግጥሞች እንመልከት፡-

*109- አህያ መጣች ተጭና ላዳ*
*ችግር ይወርዳል ወደ ይላዳ፡፡*

*110- አህያ መጣች ተጭና ሚደ*
*ችግር ይወርዳል ወደ ገራደ፡፡*[4]

እነዚህን ሁለት መንቶ ግጥሞች ስንመለከት የቃል ለውጥንና የይዘት ለውጥ እናያለን፡፡ በዚህም ይላዳ እና ገራደ የሚባሉ ሁለት የመኖርያ አካባቢዎች ተመስርተው የሚመጣውን ችግር በቃል ግጥማቸው ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም ችግር በተለያየ አካባቢ እንደሚመጣ አህያ መጣች ተጭና ላዳ እና - አህያ መጣች ተጭና ሚደ በማለት የተለያዩ ቃላትን በመተካት የይዘት ለውጥን ሲያመጡ ይታያል፡፡ ይህ የሚያመለክተው እረኞቹ ማስተላለፍ የፈለጉትን መልእክት መግለጽ በሚፈልጉት መልኩ አስተካክለው እንደሚደርሱ ነው፡፡

በአጠቃላይ እረኞች ራሳቸው የፈጠሩዋቸውን ወይም በሌላ ሰው የተፈጠሩ ቃል ግጥሞችን ቃል በቃል በመሸምደድ እና ከአውዱ ለማስማማት ማሻሻያ በማድረግ እንደሚገጥሙ ያመላክታል፡፡

## 4.2. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም ክዋኔ

የእረኞች ቃል ግጥም ለመደመጥም ሆነ ለመሰማት መከወኑ ግድ ነው፡፡ በእረኝነት ስፍራ እረኞች ከብቶችን እየጠበቁ ያንጎራጉራሉ፣ ይዘፍናሉ፣ይፎክራሉ፣ያቅራራሉ፣ የተለያዩ ዜማዎችን ያዜማሉ፡፡ ለጥናት በተመረጡት ቦታዎች በነበረኝ የመስክ ቆይታ ለማየት እንደቻልኩት እነዚህን ክዋኔዎች የሚፈጽሙት ከብት በሚጠብቁበት ቦታ፣ ከብቶችን ውሃ ሳያጠጡ፣ በመኖርያ ቤታቸው አካባቢ ጠዋትና ማታ ከብቶችን ወደ ሜዳ ከማሰማራታቸው በፊት እና ለከብቶች ሳር(መኖ) በሚሰጡበት ጊዜ ለብቻቸው በእንጉርጉሮ መልክ በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲሁም እንዲከውኑ ተጠይቀው የሚከውኑባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ ለመመልከት ችያለሁ፡፡ በወቅቱም በተናጠል፣ በጥንድ እና በቡድን የተለያዩ ፉከራና ቀረርቶዎችን፣ የዘፈንና የእንጉርጉሮ ቃል ግጥሞችን አውርደዋል፡፡ ሲከውኑም ከዘፈን ወደ ፉከራና ቀረርቶ፣ከሆታ ወደ ዘፈን እንደሚሸጋገሩ ጭሩ፣ቱሉ አውልያ እና ጊምባ አካባቢ በነበረኝ የመስክ ቆይታ ተመልክቻለሁ፡፡

[4] መረጃ ሰጭ ፡- ብረዲን ሃምዛ (እድሜ 13)፣ ቱሉ አውልያ ቀበሌ፣ ተማሪና እረኛ፣የካቲት 22/2004፣ቱሉ ጎራ፡፡ እንዲሁም ኢብራሂም ሃሰን (እድሜ 14)፣ቱሉ አውልያ ቀበሌ ፣እረኛ፣የካቲት 18/2004፣ጊምባ ሜዳ፡፡ (የትንቢት ግጥምን በመንገር አስተዋጾ ያደረጉ)

እረኞቹ ከብት በሚጠብቁበት ጊዜም በየጊዜው ከሰሙትም ሆነ ፈጥረው ደስታና ሃዘን፣ ስኬትና ውድቀትን፣ ማግኘትና ማጣትን፣ጥጋብና ረሃብን አስመልክተው ያዜማሉ፤ ይዘፍናሉ፣ የተለያዩ ነገረ ጉዳዮችንም ያነሳሉ።

በሊጋምቦ ወረዳ አካባቢ የሚገኙ እረኞች ቃል ግጥምን የሚከውኑት በብዙ መንገድ ነው። የቃል ግጥም ክዋኔ ከላይ እንደተገለጸው በሶስት አይነት መንገድ ሊከወን ይችላል። እረኞችም በተናጠል፣ በጥንድ፣ በቡድን (በዜማ መልክ፤ በምልልስና በቅብብሎሽ) ይከውናሉ። እነዚህን ቀጥለን እንመለከታቸዋለን።

### 4.2.1. በተናጠል የሚከወኑ የእረኞች ቃል ግጥም

የተናጠል እረኞች ቃል ግጥም ክዋኔ እረኞች በየግላቸው (በየራሳቸው)የሚያዜሟቸውንና የሚያንጎራጉሯቸውን ቃል ግጥሞች የሚዳስስ ነው። ይህን ጉዳይ ፎክ ማለት ከአንደ ሰው በላይ እንደሆነ ዳንደስ ያስረዳል ሆነም እረኞችን በምናይበት ጊዜ ፎክሎርን ለየበቻቸውም (በግለሰብ ደረጃ) ሲከውኑ ይታያል። እረኞች መካከል አንዱ የሆነው እንድሪስ አሰን ሲናገር፡-

> *በግላችን የምናዜምበት እና የምናንጎራጉሩበት አጋጣሚ ብዙ ነው። በመኖሪያ ቤታችን አካባቢ ጨፌ (ሳር) ባለበት ቦታ ሆነን ለብቻችን ስንጠብቅ፣ ከጓደኞቻችን ተለይተን ከብቶቻችንን ወደ ቤታችን ስንነዳና ወደተለያየ ቦታ በግላችን ስንቀሳቀስ ለየብቻችን እንዘፍናለን (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት22/2004 ካሴት ቁጥር 4፣ለ)።*

በማለት በየግላቸው እንዴት እንደሚገጥሙ ገልጿል። በተጨማሪም ይህንን ሃሳብ በተመሳሳይ ኑርዮ ጋሻው እና እብራሄም ተሾመ ገልፀውታል። እኔም ይላዳ፣ገነቴ፣ጊምባ እና ጭሩ በነበረኝ የመስክ ቆይታ በምልከታዬ ማየት እንደቻልኩት በቀያቸው ለብቻቸው ከብት ሲጠብቁ፣ ውሃ ሲቀዱ፣ ከብቶችን ውሃ ሲያጠጡ እና ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ በግላቸው የሚያንጉራጉሩበትና የሚዘፍኑበት አጋጣሚ እንዳለ ማየት ችያለሁ። ከተሰበሰቡት መረጃዎች መካከል የሚከተሉትን ለምሳሌ እንመልከት፡-

*53 - የበጎች እረኛ ሆኘ ከርሚያለሁ*
*መስከረም ሲጠባ መጥቶ አይሻለሁ።*

*56- ፍየል ቅጠል እንጂ አትበላም ገለባ*
*ልቤ ገሰገሰ ወደ አዲስ አበባ።* [5]

---

[5] መረጃ ሰጭ፡- እታፈራሁ ይመር (እድሜ 14)፣ ጭሩ ቀበሌ፣ ተማሪና እረኛ፣ሚያዚያ 10/2004፣ቱሉ ጎራ።

በተራ ቁጥር 53 እና 56 የቀረቡት ቃል ግጥሞች እረኞች ከሚያዜሟቸው ተናጠላዊ (ግላዊ) ግጥሞች ለአብነት የቀረቡ ናቸው ። አብዛኞቹ ግጥሞች የራስን ወይም የግልን ፍላጎትና ምኞት የሚያንፀባርቁ ናቸው ማለት ይቻላል። በዚህ መሰረት ያገኘኋቸው አብዛኞቹ ቃል ግጥሞች የሚያሳዩት የራሳቸውን ተሰፋ፣ምኞት፣ ፍላጎት እና መሻትን ነው።

### 4.2.2. በጥንድ (በቅብብሎሽ) የሚከወኑ የእረኞች ቃል ግጥም

የለጋምቦ አካባቢ እረኞች በተናጠል እንደሚያዜሙ ሁሉ በጥንድ (ለሁለት) በቅብብሎሽ ያዜማሉ። ዜማውን በአብዛኛው ተሰብስበው በሚጨዋቱበት ጊዜ ጎን ለጎን እና ማዶ ለማዶ ሆነው በወንዝ ዳር አካባቢ ከብቶችን ውሃ በሚያጠጡበት ጊዜ፣ በእንጨት ሰበራ እና በአመት አንድ ጊዜ በሚያካሂዱት የይለዳ ባህላዊ የትግል ጨዋታ ላይ ይከውኑታል።

ለዚህም ቱሉ አውልያ አካባቢ በቆየሁበት አጋጣሚ እረኞች ከብት በሚጠብቁበት ጊዜ በተለይም የፉከራ፣ ቀረርቶ እና የፍቅር ቃል ግጥሞችን በቅብብሎሽ ሲከውኑ አይቻለሁ። ማስረጃ ይሆን ዘንድ ወጣት እንድሪስ አሊና ኢብራሂም ተሾመ ያቀረቧቸውን የቀረርቶና ፉከራ ቃል ግጥሞች እንመልከት፡-

*54. የቅርጫ ስጋ ዝንብ የወረረው*
*እንቢ አለ ልቤ ክልብሽ እያለው።*

*55- ደጋ ለደጋ ይዘራል ገብስ*
*አፈር አልብሸው አፈር ልልበስ።* [6]

### 4.2.3. በቡድን የሚከወኑ የእረኞች ቃል ግጥም

የቡድን የአከዋወን በመጠኑም ቢሆን Finnegan እንደሚሉት በመሳሪያ ታጅበው የሚቀርቡት ውስጥ ሊጠቃለል ይችላል። ምክንያቱም በእጅ በማጨብጨብና በከፍተኛ ሁኔታ የድምፅ እጀባ የሚደረግበት ስለሆነ። ይህ ክዋኔ ከሁለት በላይ የሆኑ እረኞች የሚሳተፉበት ነው። በአንድ አውራጅ በሌሎች ተቀባይነት የሚዘፈኑ የዘፈን፣የሆታ፣ የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች ላይ ይበልጥ ይከውኑታል። ከዚህ በተጨማሪ በቡድን ሆነው በአንድ ድምፅ የሚያዜሟቸው የበግ ጥበቃ ግጥሞችና በተለያዩ ጨዋታዎች ላይ የሚደረድሯቸው የአሸናፊና ተሸናፊ ሆታ

[6] መረጃ ሰጭ ፡- እንድሪስ አሊ (እድሜ 12)፣ ጭሩ ቀበሌ፣ እረኛ፣የካቲት 10/2004፣ጭሩ ሜዳ። እንዲሁም ኢብራሂም ተሾመ (እድሜ 14)፣ጭሩ ቀበሌ ፣ተማሪና እረኛ፣የካቲት 20/2004፣ጭሩ ሜዳ። (የትንቢት ግጥም የደረደሩ)

ግጥሞችን ያካትታል፡፡ ወጣት እንድሪስ አሊ፣ እብራሂም ተሾመ እና ሌሎችም ወጣቶች እንደሚሉት ከሌሎቹ በተሻለ በቡድን የሚከውኑቸው የዘፈን ግጥሞች ደስታን ይፈጥሩላቸዋል፡፡ ምክንያቱም በግጥሞቹ አብዛኛውን ጊዜ የፉክክር እና አሸናፊነት ሁኔታን ስለሚገልፁባቸው እንደሆነ ማብራርያ ሰተዋል፡፡

ለዚህም እንደ ምሳሌ እረኞች የሚሳተፉበትን የይላዳ ባህላዊ የትግል ጨዋታ ማንሳት ይቻላል፡፡ ይህ ጨዋታ በምርቃን ተከፍቶ በምርቃን የሚዘጋ የራሱ የሆነ መክፈቻና መዝጊያ ስርዓት ያለው ነው፡፡ እረኞቹ የትግል ስርዓቱን በዳኞች አማካይነት ከከወኑ በኋላ ያሸነፈ በከፍተኛ ሁኔታ እየዘፈነ ና እየጨፈረ ይሄዳል፡፡ የተሸነፈ ደግሞ ለተዘፈነለት ምላሽ የሚሰጥበት አጋጣሚ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ቀጥሎ በዘፈን ያቀረቡትን ቃል ግጥም እንመልከት፡-

57- *አለ ሆላ እንቢተኛው ና (2)*
*አለ ሆላ የኛማ ልጆች ቀጫጭኖቹ*
*ይናደፋሉ እንደ ንቦቹ*
*በጥቁር ጭራ ብለምጠው*
*አሬራው ወጣ የቀላወጠው፡፡*

ወጣቶቹ ተሰብስበው ክብት በሚጠብቁበት ቱሉ አውልያ በተባለ ጎራ ስር ተገኝቼ ከሚገጥሟአቸው ቃል ግጥሞች እንዲሉልኝ ጠየኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ኑርያ ጋሻው ጓደኞቹን ሰብስቦ እንዝፈን በማለት ከላይ የተጠቀሰውን ቃል ግጥም መዝፈን ጀመሩ፡፡ በምልከታየም እንዳየሁት ሁሉም የራሳቸው የሆነ ሚና ነበራቸው፡፡ ይኸውም ኑርዮ እንደዋና አቀንቃኝ (ከዋኝ) ሆኖ ሲያገለግል ሌሎቹ ደግሞ እንደ ታዳሚና አጃቢ በመሆን በክዋኔው ተሳትፈዋል፡፡ በዚህም ኑርዮ አለ ሆላ እንቢተኛው ና(2) ብሎ ሲጨርስ ታዳሚዎቹ እሱ ያለውን በአንድ ድምፅ በማስተጋባት ይደግሙታል፡፡ እንዲህ እያሉ ሌሎቹንም ቃል ግጥሞች ይቀጥላሉ፡፡ በዚህ ክዋኔ የታዳሚዎች ሚና በቃል ግጥም አጃቢነት ጎልቶ የሚታይበት እና ያቀንቃኙ ተሰሚነት የጎላበት እንደሆነ በምልከታየ ለማየት ችያለሁ፡፡

## 4.3. የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም ተስተላልፎ

የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም ተስተላልፎ ምን እንደሚመስልና መጀመሪያ ቃል ግጥሙን ከየት እንደሚያገኙ ኢብራሂም ተሾመ ሲገልፅ፡- "በርካታ የዘፈን፣ የቀረርቶና ፉከራ ግጥሞችን እንዲሁም የሆታ ግጥሞችን ከጓደኞቼ ጋር በእረኝነት ስፍራ፣ ከቤተሰቦቼ በመጠየቅ፤ በአካባቢዬ ሲዘፈን ከሰማሁትና ካየሁት በመነሳት እገጥማለሁ"(ቃለ-መጠይቅ፣የካቲት 20/2004) በማለት

ለመዳውን ገልጾልኛል፡፡ እንደሱ አገላለጽ ግጥሞቹን የሚያገኙት ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ እና ከራሳቸው በመፍጠር ነው ፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ የለጋምቦ ወረዳ እረኞች በአንድ አውድ የተለያየ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞችን ይገጥማሉ፡፡ ለዚህ እንደ አስረጂ ቀጣዮቹን ቃል ግጥሞች እንይ፡-

*119 -አህያ መጣች ተጭና ግልድም*
*መሬት የሸጠ እንዴት ይለድም፡፡*

*120 -አህያ መጣች ተጭና ግልድም*
*በልግ ያልዘራ ሰው እንዴት ይለድም፡፡*[7]

የሁለቱን መንቶ ቃል ግጥሞች ይዘት ስንመለከት ተመሳሳይ ነው፡፡ ነገር ግን ከአውዱ እንዲስማማ በማድረግ መሬት የሸጠ ሰው እና በልግ ያልዘራ ብዙ ነገር እንደሚያጣ ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ እንደምናየው አህያ መጣች ተጭና ግልድም በሚለው ስንኝ አውዱን ሳይቀይሩ የሃረግ ለውጥ በማድረግ የተለያየ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞችን አቅርበዋል፡፡ ይህ የሚያሳየን የሰሙትን በመሸምደድ እንደሚያስተላለፉ ሁሉ ለአውዱ እንዲስማማ የተለያዩ ለውጦችን በማድረግም ይገጥማሉ፡፡

[7] መረጃ ሰጭ ፡- ኡስማን ሰይድ (እድሜ 14)፣ ቁሉ አውልያ ቀበሌ፣ እረኛ፣የካቲት 15/2004 ቁሉ ጎራ፡፡(የትንቢት ቃል ግጥም ደርዳሪ)

# 5. የለጋምቦ ወረዳ አረኞች ቃል ግጥም ይዘት ትንተና

በዚህ ጥናት ከ300 በላይ ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል። ቃል ግጥሞቹ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የያዙ ሲሆን በያዙት ይዘት መሰረት ለትንታኔ ተደራጅተዋል።

የቃል ግጥሞቹ ምደባ የተደረገው ጥናቱን በዋናነት ያሳያሉ የተባሉትን ዓብይ ነገረ ጉዳዮች በመመስረት ንዑሳን የሆኑትን ሃሳቦች በሥሩ በማካተት ነው። ከዚህም ጋር በተያያዘ ፊቃደ (1993፣ 90) "በብዙ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ፣ የጋራ ይዘቶች ናቸው ከምንላቸው ይዘቶችን መርጠን በእነሱ መሰረት የክልስፍና ስራችንን ማከናወን እንችላለን" በማለት ይገልፃሉ። ስለዚህ ንዑሳንዎቹ ጉዳዮች በዋናው ጉዳይ ስር ይወሳሉ ማለት ነው።

በትንታኔው ለቃል ግጥሞቹ መፈጠር መንስኤ የሆኑትን አጋጣሚዎች ከትንተና ጋር አቀናጅቶ መስራት አስፈላጊ እንደሆነ Ben-Amos (1993,210) "orally performed verbal art to its logical conclusions, insisting that any valid interpretation consider the entire cultural, social, and situational context. The meaning of a text is its meaning in context" እንደ Ben-Amos ገለጻ የቃል ግጥሞቹን ይዘት ለመተንተን የተከወኑባቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ግለሰባዊ አውዶች እንዲሁም አጋጣሚዎችን በመመልከትና በማጤን ተገቢና አሳማኝ የሆነ ትንታኔ እና ድምድሜ ለመስጠት ያስችላል። እኔም በዚህ ሃሳብ መሰረት የቃል ግጥሞቹን አውድ በማጤን የይዘት ትንተና አድርጌለሁ።

የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ከያዙት ይዘት አንጻር በሰባት ተመድበዋል። እነሱም ትችታዊ፣ ትንቢታዊ፣ መሳደቢያ፣ ማሞገሻ፣ ምክር ለጋሽ፣ ማንነትን የሚገልፁና የፍቅር መግለጫ በሚል የቀረቡ ናቸው። ለትንታኔ የተመረጡት ቃል ግጥሞችም አባሪ ላይ በተቀመጡበት ተራ ቁጥር ቅደም ተከተል ሳይሆን የተነሳውን ርዕሰ ጉዳይ ይበልጥ አጉልተው የሚያሳዩትን እንደ አስፈላጊነታቸው በመምረጥ ነው። በመሆኑም በስራው ውስጥ ማሳያ ይሆን ዘንድ 53 ቃል ግጥሞች ተመርጠው ገለጻና ትንተና ተደርጎባቸዋል። በዚህ መሰረት የይዘት ትንተናው እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 5.1. ትችታዊ የቃል ግጥሞች

የሊጋምቦ ወረዳ አረኛች የማህበረሰቡ አንድ አካል እንደመሆናቸው መጠን በየዕለቱ የሚያስተውሉትን እና የሚያጋጥሟቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ (አስተዳደራዊ)፣ እኩይ እና ሰናይ ተግባራት በቃል ግጥሞቻቸው ይተቻሉ። በዚህም በየዘመኑ ያለውን የአስተዳደር ስርዓት፣ የሴቶችን የእኩልነት መብትንና ሌሎች ጉዳዮችንም በቃል ግጥማቸው ይነቅፋሉ፣ ያወግዛሉ፣ ይተቻሉ።

በኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ ነገስታትና ሹማምንቶች በስልጣን ላይ ቆይተው አልፈዋል። የእነዚህን ሹማምንት አስተዳደራዊ ስርዓት ድክመትና ጥንካሬ አረኛች በቃል ግጥሞቻቸው ይተቻሉ። በዚህም አሳዛኝና አስከፊ ድርጊቶቻቸውን በእንጉርጉሮ፣ በዘፈን፣ በቀረርቶና በፉከራ እንዲሁም በሌሎች ቃላዊ ግጥሞች አንፀባርቀዋል።

ከቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለውን የመሬት ይዞታ በተመለከተ ብርዳማ በነበረው ጊምባ ሜዳ አካባቢ ለብቻቸው ብርድልብሳቸውን ለብሰው ከብቶችን ሲጠብቁ ያገኘሃቸው አረኛ ከበደ ፋሪስ በአረኝነት ስፍራ ከሚገጥሟቸው ቃል ግጥሞች እንዲደረድሩልኝ ስጠይቃቸው እሽታቸውን በመግለፅ የሚከተለውን ትችት አዘል ቃል ግጥም ደርድረዋል፦

*ቃል ግጥም 1፦*

*አዱኒያ ታልቅና ስትመር እንደሬት*
*ትንሹም ትልቁም ይላል መሬት መሬት*
*ሁለት ንጉሥ ሄዶ ሶስተኛው ሲመጣ*
*ከመሬት ላይ ያለው ምነው በጉድ ወጣ።*[8]

ከቃል ግጥሙ እንደምንረዳው በድሎት እና በተድላ ላይ የነበሩ ሰዎች እንደነበሩ"አዱኒያ"[9] በሚለው ቃል ርስት እና ሃብት እንደሸሻቸው መረዳት እንችላለን። ይሁን እንጅ ይህ ሃብት እና ጥሪት በጊዜ ሂደት ርቋቸዋል። እንደ ቃል ግጥሙ ተናጋሪ ጥንት ስፊ "ጋሻ" መሬትን ይዘው ማረስ ቢችሉም ‹ኢህአዴግ› ከመጣ በኋላ የመሬት ቅነሳ ሲደረግ አናሳ መሬት እንደተሰጣቸውና ሃብታቸው ቀንሶ መኖር እንዳልቻሉ ለዚህም ተጠያቂ ያደረጉት አሁን እያስተዳደረ ያለውን መንግስት ነው። ከዚህም በላይ ቀደም ሲል የነበሩትን ሁለት የአስተዳደር ስርዓቶች መልካምነት በማውሳት የ ‹ኢህአዴግ› ን አስተዳደራዊ ስርዓት ይተቻሉ። "*ከመሬት ላይ ያለው ምነው በጉድ ወጣ*" በማለት ያለውን የችግርና የመከራን ደረጃ አጉልተው ስርአቱ የቀድሞ ተድላችንን

[8] *መረጃ ሰጭ ፦ ከበደ ፋሪስ* (እድሜ 80)፣ ጊምባ ቀበሌ፣ አረኛ፣የካቲት 7/2004፣ ጊምባ ሜዳ።
[9] *እንደ መረጃ አቀባይ ከበደ ፋሪስ (የካቲት 7/2004) ገለጻ አዱኒያ ማለት ሀብት ወይም ርስት ማለት ነው።*

ሊመልስ አልቻለም ሲሉ ተጠያቂ አድርገውታል። የእርሻ መሬት ፍላጎታቸው በአሁኑ የአስተዳደር ስርአት አጥጋቢ ምላሽ ባለመስጠቱ እና ተድላ ሃብታቸው በመጥፋቱ ችግር እና መከራችን ቀጥሏል የሚል ድምጸት በቃል ግጥሙ አመልክተዋል። "*ትንሹም ትልቁም ይላል መሬት መሬት*" በሚለው ስንኝ አሁንም ድረስ ለችግራቸው ደረስኩላችሁ ያላቸው አካል አለመኖሩን ከምሬት ጋር አያይዘው ገልፀዋል። በተጨማሪም ከዚህ ቃል ግጥም ጋር በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 7፣14፣15፣26 እና 39 የተገለጹት የቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ይዘት አላቸው።

በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ "አገር" በሴት ፆታ እንደምትጠራ ሁሉ የለጋምቦ ወረዳ እረኞችም ‹ኢህአዴግ›ን በሴት ፆታ ይጠራሉ። ከዚህ ጋር አያይዘውም ንጉስ ትባላለች አጼ ትመስላለች ሲሉ በሴት ፆታ መስለው ስላለው የመሬት ክፍፍል ይናገራሉ፡-

*ቃል ግጥም 2፡-*

*በመተማ በኩል ይፈልቃል ወጠጤ*
*ትባላለች ንጉሥ ትመስላለች አጤ*
*መሬቱን ከፈለች አርጋ ስንዝር ከጋት*
*ይህስ የሚመስለው ለጓሚው ሹም መግባት።*[10]

ይህን የቃል ግጥም የደደሩልኝ እንድሪስ የሱፍ የተባሉ አዛውንት እረኛ ሲሆኑ መቀርጨሚያ በሚባለው ቀበሌ መቀርጨሚያ ጨፊ በተባለ ቦታ በእረኝነት ላይ እንዳሉ ነው። ግጥሙንም ሲደረድሩ የብሶት ስሜት ይነበብባቸው እንደነበር ለማየት ችያለሁ። በቃል ግጥሙም እንደምናየው በሀገራችን ባህል ያኮረፈ መሸሸጊያ እና መደበቂያ በረሃ ነው። ሽፍቶች በበረሃ በሚኖራቸው ቆይታ ለህይወታቸው አስፈላጊ የሚባሉ እንደ ምግብ፣ልብስ እና የጦር መሳሪያ ያሉ ግብአቶችን ለማግኘት ሲሉ በአካባቢው ያሉትን ነዋሪዎች ይረብሻሉ። አስገድደውም ቢሆን ይቀማሉ ።ታዲያ ይህ የቃል ግጥም ገጣሚ አሁን ላይ ሃገሪቱን በማስተዳደር ላይ ያሉትን አካላት እኛን ሲረብሹ የኖሩ ነበሩ በማለት "*በመተማ በኩል ይፈልቃል ወጠጤ* " በማለት ገልጿቸዋል። ወጠጤ እረባሽ ነው፣ጉልበተኛ እና ማናለብኝ ባይ ባህሪ አለው። እረኞቹ በቃል ግጥማቸው ይህን ባህሪ ለ‹ኢህአዴግ› መንግስት ሲያላብሱ በመተማ በኩል እንደገባ ከላይ የተጠቀሰውን ስንኝ ማስረገጫ አድርገው ነው።
በቃል ግጥሙ ይህ ረባሽ እና አስቸጋሪ ሽፍታ የንጉስነት እና የአጤነትን ጭንብል ካባ መልበሱን "*ትመስላለች አጤ*" በሚለው ስንኝ እንደ አጼዎቹ ስረዓት መሬትን በአጥጋቢ ሁኔታ

[10] መረጃ ሰጭ ፡- እንድሪስ የሱፍ (እድሜ 70)፣ መቀርጨሜያ ቀበሌ፣ ገበሬ፣የካቲት 11/2004፣መቀርጨሜ ጨፊ።

እንዳልሰጣቸውና መሬት ላይ ያለው የመሬት አከፋፈል ስርዓት እንደጥንቱ ሰፊ እንዳልሆነ "መሬቱን ከፊለች አርጋ ስንዝር ከጋት" በሚለው ስንኝ የመሬቱን መጠን ከአውራ ጣት እስከ መካከለኛው ትልቅ የእጅ ጣት ብሎም እሱን እንኳ መልሶ በማይደገመው ከአውራ ጣት እስከ ትንሽ የእጅ ጣት በአለው ጋት በመወከል እጅግ በጣም አናሳ መሬት እንደተሰጣቸው የግጥሙ አቀንቃኝ ያስረዳሉ፡፡ በግጥሙ ውስጥ አቀንቃኙ የመሬት ክፍፍሉን *"ይህስ የሚመስለው ለጓሚው ሹም መግባት"* በሚለው ስንኝ ማስረገጫነት የሙብት ጥያቄንም አብረው ያነሳሉ፡፡ ይህንንም የስረአቱ ለጋሚነትና መብት ነፋጊነት ለመጠቆም ተፊልጎ የቀረበ ይመስላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የ‹ኢህአዴግ›ን የመሬት አከፋፈል ሥርዓት በመተቸት የጥንቱን መልካምነት እንዲህ ሲሉ በቃል ግጥማቸው ይገልጻሉ፡-

*ቃል ግጥም 3 ፡- ጥንት ነበረ እንጂ በኃይለ ስላሴ በልዑሉ በዘውዱ*
*ሰፋ ከፍ ማለት ለቀቅ ከመንገዱ፡፡*

ይህን ቃል ግጥም እንድሪስ አሊ ቃል ግጥም 2ን በደረደሩበት ድባብ ውስጥ እንዳሉ የደረደሩት ነው፡፡ ግጥሙም በቃል ግጥም 2 ያነሱትን የብሶት ድምጽ ይበልጥ ያጎሉበት መሆኑን በነበራቸው ስሜት ለማየት ችያለሁ፡፡ እንደ ቃል ግጥሙ አውራጅ ገለጻ አሁን ላይ ያለው የመሬት አከፋፈል ስርዓት ከጥንቱ ጋር ሲነፃፀር በጣም ትንሽ ነው፡፡ ጥንት ቀያችንን እንኳ እንደፈለግን አርሰን እንበላ ነበር፡፡ አሁን አንችልም በማለት ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ በቃል ግጥሙም እንደተገልጸው በኃይለ ስላሴ የነበረውን የመሬት አከፋፈል ስርአት ጥሩነት በመግለፅ የአሁኑን ይተቻሉ፡፡ በዚህም መሬትን ሰፋ አድርጎ መያዝ ጥንት ቀረ በማለት *"ጥንት ነበረ እንጂ"* የሚለውን የማንጸርያ ስንኝ በመጠቀም ተችተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተራ ቁጥር 2 እና 3 የተገለጹት ቃል ግጥሞች ጋር በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 8፣11፣16፣23፣24፣31 እና 41 የተገለጹት ተመሳሳይ ይዘት ይዘው ይገኛሉ፡፡

ከ‹ኢህአዴግ› የአስተደዳር ስርዓት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ትችታዊ ጉዳዮች እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡ እረኞች ሰናይ መስለው እኩይ ናቸው ያሏቸውንም ነገረ ጉዳዮች ሲያወግዙና ሲተቹ ይታያል፡፡ ከነዚህም መካከል የሴቶች የእኩልነት መብት ተጠቃሽ ነው፡፡ ከአሁን በፊት ያልነበረ ይህ የሴቶች የእኩልነት መብት ተገቢ ቢሆንም ሴቶች ተገቢ አድርገው አልተጠቀሙበትም ይላሉ፡፡ ይህንንም በመስክ ቆይታዬ የጊምባ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት የሰማንያ አመት አዛውንት በጊምባ ሜዳ ከብቶቻቸውን እየጠበቁ በነበረበት ወቅት ግጥም እንዲደረድሩ

ተጠይቀው በዘመናዊነት ላይ ያላቸው የግል አመለካከት በሚከተለው ግጥም ለማሳየት ሞክረዋል፡-

*ቃል ግጥም 4 ፡-* *ደሞ ተመረጡ ደሞ ተመረጡ የእኩል መብት አሉ*
*የወንዱንም ሱሪ ለበሰችው ሴት ታጠቀችው ሴት*
*ኮቱንም ለበሰች አልጋውንም ያዘች*
*አደባባይ ውላ እቤትዋ ስትመጣ ባልዋን ገለመጠች*
*ልቀቂኝ ያላት ለት የኩል መብት አለች*
*የእኩል መብት ሰጥቶ የለቀቃት ለታ*
*ሹመቱንም ያዙኩት መሬቱንም ያዙኩት*
*እያለች እንዲያው ስትብቃቃ ስኩራ ስኩራ*
*ድንገት ጉፍ አለባት ኤድስ አባወራ።*

እንደ ቃል ግጥሙ ተናጋሪ ሴቶች በተለያየ ስራ ቦታ ላይ ውለው ሲመጡ ቀድሞ ለባላቸው ይሰጡት የነበረውን ተገቢ የሆነ ክብር ቀንሰዋል። ሴት ልጅ ተነፍጓት የኖረውን መብት ሁሉ በአንዴ ብትጎናጸፍም እየተጠቀመችበት አይደለም በሚል *"ድንገት ጉፍ አለባት ኤድስ አባወራ"* በማለት መጨረሻዋ ውድቀት ነው አይነት ድምዳሜ በግጥሙ ላይ ይስተዋላል። በአለባበስ ረገድም ጥንት ቀሚስ ይለብሱ የነበሩ ሴቶች በአሁን ሰዓት የእኩል መብት በማለት ሱሪና ኮት መልበስ እንደጀመሩና ከባላቸው ጋር ሲጋጩ የሃብት ክፍፍል በእኩልት በመፈፀማቸው ኩራት ስለተሰማቸው ተገቢ ያልሆነ ድርጊትን ይፈፅማሉ። ይህም ተግባራቸው ደግሞ ለትልቅ ችግር እና በሽታ አጋልጣቸዋል በማለት ይተቻሉ።

ሌላ በትችት መልክ ከሚነሱ ማህበራዊ ጉዳዮች አንዱ የትዳር ጉዳይ ነው። በለጋምቦ አካባቢ በድሮ ጊዜ ሚስት የሚታጨው በቤተሰብ አማካይነት ነበር። ለወንዱ የምትሆንውን ሴት ዘርዋ ታይቶ ፤ሃብትዋ ተቆጥሮ፣ ‹ልጅህን ለልጄ› በማለት ሽማግሌ ተልኮ ጋብቻ ይጠየቅና ይፈፀማል። ይህ ሥርዓት ‹ጎጂ ባህል› ተብሎ ቀርቷል። በአሁን ሰዓት ከሴቶች የእኩልነት መብት ጋር ተያይዞ ሴቶች ከፍተኛ ሃላፊነት አላቸው። ይህንንም ከበደ ፋሪስ መሪ የለቀቀ መብት መስጠት ተገቢ እንዳልሆነ የሚገልጽውን ቃል ግጥም በቃል ግጥም 4 ላይ የነበራቸውን አቋም አጠናክረው በስሜት የሚከተለውን ቃል ግይም ደርድረዋል፡-

*ቃል ግጥም 5፡- የሴት አባወራ ከመጣ ባዋጁ*
*የተፈረደውን ባያውቁት ነው እንጁ*
*ባል የለ ሚስት የለ ሁሉ ጋለሞታ*
*ትዳር የሚገኘው በየትኛው ቦታ።*

የቃል ግጥሙ አቀንቃኚ የሰው ልጆችን ዘመናዊነት ከዘመናዊነት መሰል ኋላቀርነት ጋር በማያያዝ ትዳር እንዴት ይያዝ ሲሉ ጋለሞታነትን ያወግዛሉ። ትዳር ለምን አይፀናም በማለት ይተቻሉ። በተራ ቁጥር 4 እና 5 ለትንተና የተወሰዱትን ቃል ግጥሞች በይዘት የሚመስሉ ቃል ግጥሞች በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 17፣18 እና 28 ይገኛሉ።

በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ አፄዎች በተለያየ የአገዛዝ ሥርዓት ሕዝብን አስተዳድረው አልፈዋል። ሁሉም የራሳቸው ኮሚቴ ወይም የቀበሌ ሊቀመናብርት ነበሯቸው፤አሁን ላይ ያለው መንግስትም እንዲሁ የራሱን ሊቀመናብርት ሹሞ ነው ስርዓቱን የሚያራምደው ። እነዚህ ሊቀመናብርት ለራሳቸው እንጂ ለአረኞች ምንም ፋይዳ እንዳላደረጉላቸው የቃል ግጥሙ ተናጋሪ የሚከተለውን ይላሉ፡-

*ቃል ግጥም 6 ፡- ሎሚ ኮለል ኮለል የልጆች ጨዋታ*
*ኮሚቴ ነን ባዮች ጠዋት የተናገሩት አይገኝ ለማታ*
*ያም መጣ ያም መጣ ሁሉም ለራሱ ነው*
*ቢያስታውሱን እንኳ ለኛ የሚደርስን ያው ትራፊያቸው ነው።*[11]

ይህን የቃል ግጥም የደረደሩልኝ የብርድልብሳቸውን ለብሰው የጊምባ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት ሽህ ሁሴን በሽር የተባሉ የስባ ዘጠኝ አመት አዛውንት ሲሆኑ ጊምባ ሜዳ ከብት ሲጠብቁ ነው።የደረሰባቸውን በደልም በደረደሩት ቃል ግጥም ብቻ ሳይሆን ስሜታቸው ያሳይ ነበር። በቃል ግጥም ስድስት እንደሚታየው የኮሚቴዎች ተግባር ልጆች የልጅነት ህይወታቸውን ከሚያዝናኑባቸው ጨዋታዎች ጋር ተገናኝቷል፤ተቆራኝቷል። በቃል ግጥሙ ውስጥ "*ሎሚ ኮለል ኮለል*" ለልጆች ከጨዋታነት እና ከማዝናናት ሌላ ሚና የለውም በሚል ስሜት ኮሚቴዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና እርባና ቢስ ያደርገዋል ። የኮሚቴዎቹን ስራ ከህፃናት ያልበሰለ አእምሮ ጋር አገናኝቶ ከንቱነታቸውን ይናገራሉ ። "*ኮሚቴ ነን ባዮች ጠዋት የተናገሩት አይገኝ ለማታ*" በማለት በቃላቸው የማይፀኑ፣ በውሸት የተተበተቡ ፣ ህሊና ቢሶች እንደሆኑ በፌዝ "*ኮሚቴ ነን ባዮች* " እያለ በቃል ግጥሙ ውስጥ ያቀነቅናል። በቃል ግጥሙ እንደሚታየው በስልጣን ርካብ ላይ ያሉ ሰዎች ለሌሎች የሚያዝኑትና የሚራሩት የራሳቸውን ጥቅምና ፍላጎት ካሟሉ በኋላ እንደሆነ የቃል ግጥሙ አውራጅ "ቢያስታውሱን እንኳ ለኛ የሚደርስን ያው ትራፊያቸው ነው" በሚለው ስንኝ ያለባቸውን ብሶት እና ምሬት ያሳያል።

---

[11] መረጃ ሰጭ ፡- ሁሴን በሽር (እድሜ 79)፣ ጊምባ ቀበሌ፣ ገበሬና አረኛ፣የካቲት 13/2004፣ጊምባ ሜዳ።

የቃል ግጥም አውራጁ "ኮሚቴ ነን ባዮች" በሚለው ስንኝ የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር እንጂ ለህዝብ የቆሙ አለመሆናቸውን እና ሁሉም ስልጣን ይዘው ባስተዳደሩበት ዘመን ለህዝቡ ሳይሆን ለራሳቸው ጥቅም እንደሮጡ "ያም መጣ ያም መጣ ሁሉም ለራሱ ነው" በሚለው ስንኝ አስረግጦ ይነግራል። ምክንያቱም ህግን ሲያወጡ እንኳ ለራሳቸው እንዲመቻቸው አድርገው ጠዋት የተናገሩት ካልጣማቸውና ካልተመቻቸው ማታ ሽረው ሌላ ህግን በመደንገግ የሚያስተዳድሩ ናቸው በማለት ሃሳባቸውን እና የውስጣቸውን ብሶት በቃል ግጥሙ ገልጿል። በተራ ቁጥር 6 ለትንተና የተወሰደውን ቃል ግጥም በይዘት የሚመስሉ ቃል ግጥሞች በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 30 እና 42 ይገኛሉ። በአጠቃላይ ትችታዊ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች በአባሪ ላይ ከተራ ቁጥር 1-42 ቀርበዋል።

## 5.2. ማንነትን የሚገልፁ የቃል ግጥሞች

የሲጋምቦ ወረዳ እረኞች የራሳቸውን ማንነት[12] በዘፈን፣ በፉከራ፣ በቀረርቶና በእንጉርጉሮ መልክ ይገልፃሉ። በዚህም የትመጣነታቸውን፣ የአለባበስ ባህላቸውን ፣ ጀግንነታቸውን፣የተለየ ተሰጥዎ እንዳላቸው እና እነሱን መቀላቀል የፈለገ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት የሚገልፁ ቃል ግጥሞችን አቀንቅነዋል።

በመስክ ቆይታዬ ወቅትም ለጥናት በተመረጡት ቦታዎች እንደተመለከትኩት የሲጋምቦ ወረዳ አካባቢ እረኞች በእረኝነት ጊዜ የሚለብሷቸው ልብሶች ዘወትር ከሚለብሷቸው ይለያሉ። እረኞቹ ከበግ ቆዳ የሚሰራ "ለምድ"፤ በጭንቅላታቸው ላይ በአካባቢው ማህበረሰብ አጠራር "ጉኒና" የሚባል ከበግ ፀጉር የሚሰራ ኮፍያ፣ በእጃቸው ለቆሎ መያዣነት የሚያገለግል "ቁርቁንባ" ወይም አኩፋዳ፤ ከወገባቸው በታች ደግሞ አጭር ቁምጣና ከፕላስቲክ የተሰራ በአካባቢው አጠራር "ጅብ አይበላሽ" በመባል የሚታወቅ ጫማ ያደርጋሉ። በአሁኑ ሰአት ግን ይህ አለባበስ በስፋት መታየቱ እየቀነሰ መጧል።[13]

---

[12] በዚህ ስራ ውስጥ ማንነት ማለት እረኞች በቃል ግጥማቸው የራሳቸውን ሰብዕና እና አጠቃላይ ሁኔታ የሚያንፀባርቁበት ነው። ይህም እኔ እንዲህ ነኝ፣ እኔ እንዲህ እመስላለሁ በማለት በአለባበስ፣ በዘር እና በሌሎች የራሳቸውን ሰብዕናና አካላዊም ሆነ ውስጣዊ ሁኔታን የሚያሳይ ነው።

[13] እየቀነሰ መጥቷል ሲባል እረኞች ይለብሷቸው እና ይከውኗቸው የነበሩ እኔ የማስታውሳቸው የተለያዩ የቃል ግጥም ክዋኔዎች እየጠፉ መምጣታቸውን መስክ በነበረኝ ቆይታ በምልከታዬ አይቻለሁ ።በተለይም ሁሉም እረኞች ይለብሷቸው የነበሩ የለምድ እና የማቅ አልባሳት አሁን ላይ እጅግ በመነመነ መልኩ (ሁሉንም እረኞች በማያካትት ሁኔታ) አልፎ አልፎ ለብሰው አይቻለሁ። ከዚህም በተጨማሪ ከአሁን በፊት በተቀናጀ ሁኔታ(በተለያዩ ክዋኔዎች) ታጅቦ ይከውኑት የነበረው የትንቢት ግጥም አሁን ላይ በተለያዩ ምክንያቶች በስፋት አይከወንም።

ሆኖም አልፎ አልፎ ቢሆንም አሁንም አለ። ይህንን ሀሳብ እረኞቹ በሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ማሳየቱ ይሻላል፦

*ቃል ግጥም 43፦ ጊምባ ያደገው አባ ቦሌ አገር*
*ውሽቴን እንደሁ ይችት ኩራቴ ለምዴ ትናገር*
*በጎቹን ሳግድ ለምዴን ለብሼ*
*በከረጢቴ ቆሎዬን ይዤ።*

ይህን ቃል ግጥም እንዲሪስ አሊ የተባለ የጭሩ ቀበሌ ነዋሪና የ12 አመት ቁምጣና ለምድ ለባሹ ታዳጊ እረኛ ጭሩ ሜዳ ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር ከብቶችን እየጠበቀ ባለበት ሁኔታ ግጥም እንዲገጥሙልኝ ስጠይቅ ከጓደኞቹ በተሻለ ድምጹን ከፍ በማድረግ እንዲያጅቡት በጥቅሻ ምልክት እያሳየ በሽለላና ጎንበስ ቀና በሚል እንቅስቃሴ ብትሩን ከፊ ዝቅ እያደረገ ወኔ በተላበሰ ሁነታ የደረደሩ ነው።

የግጥሙ ተናጋሪ ጊምባ በተባለው አካባቢ ያውም አባ ቦሌ አገር ተወልዶ በማደጉ የሚኩራበትን ለምድ ለመልበስ እንደታደለ በቃል ግጥሙ ያሳያል። በቃል ግጥሙ እንደምናየው እረኛው በእረኝነት ስፍራ የሚለብሰው ልብስ ለምድ እንደሆነ እና ወደ ከብት ጥበቃ ሲሄድም ቆሎ በከረጢት እንደሚይዝ ይገልጻል። በዚህ አለባሱ ኩራት እንደሚሰማው በቃል ግጥሙ ውስጥ "*ይችት ኩራቴ ለምዴ ትናገር*" በሚለው ስንኝ የለበሰውን ለምድ በሴት ፆታ አቆላምጦ ያዜማል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 69 እና 79 የተገለጹት ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ይዘት ይዘው እንመለከታለን።

በለጋምቦ አካባቢ እረኞች ለምድ ለብሰው በግ በሚጠብቁበት ሰዓት በማህበረሰቡ ውስጥ ወደፊት ምን ይፈጠራል? አሁንስ? የሚለው ነገር እንደሚታያቸውና ይህ ደግሞ ከፈጣሪ የተሰጣቸው ፀጋ እንደሆነ ይናገራሉ። በዚህም በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ ትንቢት ተናጋሪ እና እውነትን አዋቂ ተደርገው ይታመናሉ። እረኞችም ራሳቸውን እንደአዋቂ አድርገው ይቆጥራሉ። አዋቂነታቸውም በማህበረሰቡ ውስጥ ጭምር ተቀባይነት እንዳለው አቶ ሁሴን ሙሀዬ ፧እንድሪስ የሱፍ፧ ከበደ ፋሪስ እና ሸህ ሁሴን በሽር በተለያየ ጊዜ በተመሳሳይ እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፦

*እረኞች ራሳቸው የሚፈርዱና የሚሆነውን የሚናገሩ ሳይሆን የሚነግራቸው አውሊያ*[14] *አለ። ይህም የቱሉ አውሊያ፣ የጭሩ አውሊያ፣ የጊምባ አውሊያ፣ የጎሪት አውሊያ፣ የጨፌ አውሊያ፤ ተሰብስበው ቆሎአቸውን በሚበሉበት ጊዜ የነገሯቸውን ነው የሚናገሩት። ይህ ደግሞ ከላይ ከፈጣሪ የተሰጣቸው ነው (የካቲት 7 እና 20/2004 ፣ ካሴት ቁጥር 1፣እና 6 )።*

በማለት የእረኞችን ትንቢት ተናጋሪነት ከፈጣሪ የተሰጣቸው መሆኑን ይናገራሉ። እረኞች ትንቢት መናገርን ከፈጣሪ የተሰጣቸው የመፍረድ ፀጋ አድርገው ይቆጥራሉ። ይህንንም ጊምባ በተባለ ቦታ ልዩ ስሙ ድርቡሽ በሚባል አካባቢ በሚገኝ ጨፌ ላይ ለብቻው ከብት ሲጠብቅ የገኘሁት እረኛ ባደረኩለት ቃለ መጠይቅ በእንጉርጉሮ የሚከተለው ቃል ግጥም ደርደሯል።

*ቃል ግጥም 44፡ - እስኪ ላንጎራጉር በጎቼን አግጄ*
*ለምዴን አጥልቂያለሁ በሁለቱም እጄ*
*ከላይኛው ጌታ በተሰጠኝ ፀጋ*
*ሁሉን እነግራለሁ ትንሽ ሳልዘነጋ።*

የግጥሙ ተናጋሪ እንደገለፀው እረኞቹ በጎችን ሲጠብቁ ለምድ ለብሰው ነው። በዚህም በቃል ግጥሙ ፈጣሪ ሰጥቶኛል ብሎ የሚያምነው ልዩ ስጦታ እንዳለ ***"ከላይኛው ጌታ በተሰጠኝ ፀጋ"*** በሚለው ስንኝ ውስጥ ከላይ ከፈጣሪ የተለየ ተሰጥዎ እንደተቸረው ያሳያል።

ከዚህም በላይ በተሰጠው የመፍረድ ጸጋ አንድም ምንም ሳያዛንፍ፤ አንድም ረዥም ጊዜን ሳያቆይ እንደሚፈርድ ***"ሁሉን እነግራለሁ ትንሽ ሳልዘነጋ "*** በሚለው ስንኝ ውስጥ ***"ሳልዘነጋ"*** በሚለው ቃል ምንም ሳያሳስትና ብዙ ቀናትን ሳይፈጅበት እንደሚፈርድ ይነግረናል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 82፣85 እና 86 የተገለጹት ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው መሆኑን ልብ ይሏል።

ከዚህ በተጨማሪ የለጋምቦ አካባቢ እረኞች ከማን ዘር እንደመጡና በመጡበት ዘር ምን ያህል ኩራት እንደሚሰማቸው ይናገራሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ እንድሪስ አሊ ጭሩ ሜዳ አካባቢ ከብቶችን በሚጠብቅበት ወቅት በማን ይነካኛል እና ማን ይደፍረኛል ስሜት በለጋነት እድሜው እንኳን የጀግና ዘር መሆኑን በሁለት እጆቹ እያወዛወዘ በሚይዛቸው ብትሮቹ ሽለላዊ በሆነ መልኩ ግጥም ደርድሮልኛል። ቃል ግጥሙም የሚከተለው ነው፡-

---

[14] *እንደ መረጃ አቀባይ ከበደ ፋሪስ ገለጻ (የካቲት7/2004) አውሊያ ማለት እረኞች ቃል ግጥምን በሚገጥሙበት ጊዜ ትንቢትን እንዲናገሩ የሚያግዛቸው መንፈስ እንደሆነ አስረደተዋል። በተመሳሳይ በከሳቴ ብረሃን የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (1970፣666) የዛር፣ የቆሌ ነገር፣ በረንትቻ የሚታረድበት አድባር ሆኖ በመንፈስ ሰዎችን የሚረዳ በማለት ማብራርያ ይሰጡታል።*

*ቃል ግጥም 45፡- ምንሽሬን ይዤ ልበል ዘወር ዘወር*
*ትንሽ ይበቃል እሳትና ነገር*
*አልጠናም እንጂ ክንዴ ቢጠና*
*ይበታትናል እንደ አውሮፕና*
*ዘሬ ከጥንትም መብረቅ ነውና።*

ለጋምቦ ከጣልያን ወረራ በፊት በሶስት ገባር የሚተዳደር 3000 ሺ.ህ ህዝብ ነበረው። ይህንን ህዝብ ያስተዳድሩ የነበሩት ፊታውራሪ መብረቁ ሀይሌ ይባሉ ነበር። እኚህ ሰው አካባቢውን ከማስተዳደር በተጨማሪ ወታደራዊ ስልጠና የወሰዱ ስለነበር 900 የጦር ወታደሮችን በሻለቃነት ይመሩ ነበር የለጋምቦ ወረዳ አጭር ቅኝት (17-2002/18፤ያልታተመ)።

ከዚህ የተነሳም በሃገሩ ላይ ታላቅ ክብር ነበራቸው። ይህን ክብርና ሀይለኝነታቸውን መሰረት በማድረግ "ግብርን ስም ይግለፀው" ይባልላቸው ነበር። በቅፅልም "መብረቅ በሃይሉ" ይሉዋቸው እንደነበር  የቃል ግጥሙ አቀባይ ይናገራል። እረኞችም ይህን መሰረት አድርገው የመብረቅ ዘር ሆነን አንፈራም፤አንደፈርም በማለት ይፎክራሉ።

ከላይ በቀረበው የቃል ግጥም እንድሪስ ወኔ በተላበሰ ፉከራ ሲያወርደው ከላይኛው ማብራሪያ የዘለለ ትርጓሜ መስጠት ያስችላል ። ወጣቱ የራሱን ክንድና ሃይል ከአውሮፕላን እና መብረቅ ድብደባ እንዲሁም ከጭፍጨፋ ጋር በማወዳደር ይገልፀዋል። በዚህም "እኔ አሁን ወጣት ሆኜ ክንዴ ባይጠና ነው እንጅ ትንሽ ሳድግ ከፍ ስል የሚችለኝ የለም" በማለት ያዜማል። ይህንንም ከጥንት ጀምሮ ዘሮቹ እንደ መብረቅ የሚበጣጥሱ እና የሚበታትኑ እንደሆኑ "*ዘሬ ከጥንትም መብረቅ ነውና* " በሚለው ስንኝ ከሰማይ በሚወርደው መብረቅ በመመሰል ልክ እንደ መብረቅ የሚበታትንና የሚበጣጥስ ክንድ እንደሚኖረው ይህ ጀግንነቱም ከጥንት ካያት ቅድመአያቶች የነበረ እንደ ነበር ይገልጻል። በተጨማሪም ከዚህ ሃሳብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቃል ግጥሞች በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 65፣ 75፣ 81 እና 84 ያሉት ናቸው።

በሌላ መልኩ ደግሞ እረኞች ሚስጥራቸው እንዲታወቅባቸው አይፈልጉም። ሚስጥር ጠባቂ ሰው መሆን አስፈላጊ እንደሆነና እነሱም ሚስጥር ጠባቂ እንደሆኑ በቃል ግጥም ይገልፃሉ። እኛን የሚቀላቀል ሚስጥር ጠባቂ መሆን አለበት ይላሉ። ከእረኞች ግጥምም ሆነ የነሱ የሆነ ነገርን በሙሉ በግልፅ ለማግኘት እነሱን መምሰል አስፈላጊ እንደሆነ ወጣት ኑርየ ጋሻው *"ከጓደኞቻችን ጋር እንፎክራለን ፤እናቅራራለን ፤ኳስ ፤እንካሰላንትያ እንጫወታለን ፤እንዘፍናለን፣ እንጨፍራለን ፤ግጥም እንገጥማለን ይህን ስናደርግ ከኛ ጋር መጫወት የፈለገ ሰው እንደኛ ማድረግ*

*አለበት*" በማለት እነሱን ለመቀላቀል መመሳሰል እንደሚያስፈለግ ያብራራል *(ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት14/2004)* ። እረኞች ይህንን ጉዳይ በግጥም ሲያሳዩ፡-

*ቃል ግጥም 46፡- ሁለት አፈ ለምለም ሶስት አፈ ከፋታ*
*ከኛ ይጫወታል እኛን የመሰለ*
*ሚስጥርን ሲነግሩት ሲያስሩት ያልተፈታ።*

የቃል ግጥሙ ደርዳሪ እንደሚነግረን ከእረኞች ጋር አብሮ መሆን እና መጫወት የፈለገ ሰው እነሱን መምሰል እና የነሱን ሰብእና መላበስ እንዳለበት "*ከኛ ይጫወታል እኛን የመሰለ* " በሚለው ስንኝ ውስጥ እንደእነሱ መሆን እንደሚያስፈልግ ይገልፃል። እኛን የሚቀላቀል (ከኛ ጋር መዋል የፈለገ) ሚስጥር ጠባቂ መሆን አለበት ። ካልተናገርክ ተብሎ በፖሊስ ቢገደድ እንኳ የመጣውን ፍርድ በመቀበል መሰለፍ እንጂ ሚስጥራችንን መናገር የለበትም። ቢታሰርም ይታሰር እንጂ ፍፁም መናገር የለበትም በማለት "*ሚስጥርን ሲነግሩት ሲያስሩት ያልተፈታ* " በሚለው ስንኝ መስረገጫነት ይነገራል። ከዚህ ቃል ግጥም ጋር በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 46 እና 49 የተቀመጡት ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ይዘት አላቸው።

እረኞች ከብት በመጠበቅ ላይ ሳሉ ለመጠበቂያነት የሚጠቀሙበት መሳሪያ ብትር (ዱላ) ይባላል። ታዲያ ይህ ብትር ለከብት መጠበቂያነት ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን ከሰው ጋር ግጭት ሲደርስባቸውም ለመከላከያነት ይጠቀሙበታል። በዚህም የማንነታቸው መገለጫና ከእጃቸው የማይለያቸው መሳሪያ በግ የሰረቃቸውን አውሬም ሆነ ሰው መከላከያቸው ነው። ቀጣዩ ቃል ግጥምም ይህንኑ ያወሳል፡-

*ቃል ግጥም 47፡- ገና በይ ገና በይ ገና ለወደፊቱ*
*እሳት ይነዳል ከፊት ለፊቱ*
*አያት ብትሬ ታስታውቃለች*
*እንደ አዘንተኛ ፊትዋን ነጭታለች*
*ጠላትዋን እማ ታስራዋለች።*

ይህን ቃል ግጥም የ12 አመት እረኛ ኑርዬ ጋሻው ከመሰል ጓደኞቹ ጋር ቱሉ ጎራ ላይ ከብቶችን ሲጠብቅ ነው የደረደረልኝ ። ጓደኞቹም ገረጥሙን ሲደረድር እውነት ነው በሚል ስሜት ሲያጅቱ ለማየት ችያለሁ። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 56 እና 72 የተገለጹት ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ይዘት ይዘው እንመለከታለን።

በለጋምቦ ገጠራማ አካባቢ ልዩ ቦታው "ይላዳ" በተባለ ቦታ የሚኖሩ በሃብትና በባላባትነታቸው የሚታወቁ ሰዎች በብዛት በተራራ ይመስላሉ።[15] እነዚህ ሰዎች በአካባቢው የሚፈጠርን ግጭት በመፍታት፣ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች በታላቅነታቸው ሽማግሌ በመሆን ያገለግላሉ።

በአካባቢውም "አድባር" በመባል የሚታወቁ ናቸው። እረኞች ይህንን ጉዳይ በእረኝነት ስፍራ በቀረርቶና በፉከራ ሲገልፁ ለማየት ችያለሁ። የነዚህን ባላባቶች መሬት ዘራቸው ካልሆነ የሌላ ሰው አያርሰውም። ይህን ጉዳይ ሲገልፅም እኔ የተራሮች ዘር ሆኜ እኔን የማያውቅ ካልሆነ እንዴት የአባቴን (የኔን ዘር) መሬት ሌላ ያርሳል በሚል ደራ በተቀላቀለበት ስሜት ጭሩ ሜዳ ከብት በመጠበቅ ላይ በነበሩበት ጊዜ የሚከተለውን ቃል ግጥም አቀንቅኗል፡-

*ቃል ግጥም 48፡-* *ያባቴን መሬት ማነው ያረሰው*
*በትላም ዱላ ደም ሳላለብሰው*
*አያቀኝ እንደሁ ይስማ ንገሩት*
*የጀግና ዘር ነኝ የነ ተራሩት።*

በግጥሙ እንደሚታየው በማን ይደፍረኛል ስሜት የባላባትነት ክብሬን የሚነሳና የሚደፍር እኔነቴን አልተረዳም በሚል ***"አያቀኝ እንደሁ ይስማ ንገሩት"*** እያለ ማስጠንቀቂያ መልእክት አስተላፏል። ገጣሚው የቀድሞ ቤተሰባዊ ማንነቱን ***"የጀግና ዘር ነኝ የነ ተራሩት"*** በማለት የጀግና ዘር እንደሆነና ታላቅነት እንደሚሰማው ያሳያል። ለአባሪ ከቀረቡት ቃል ግጥሞች ውስጥ በተራ ቁጥር 63፣71 እና 77 የተገለጹት ቃል ግጥሞች በተራ ቁጥር 48 ከቀረበው ቃል ግጥም ይዘት ጋር ተመሳሳይ ይዘት አላቸው። በአጠቃላይ ማንነትን የመግለጽ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች በአባሪ ውስጥ ከተራ ቁጥር 43-89 ቀርበዋል።

## 5.3. ትንቢታዊ የቃል ግጥሞች

ወደ ይዘት ትንተና ከመግባቴ በፊት ስለ ትንቢት[16] ምን እንደሆነ እገልጻለሁ። ይህ ቃል ግጥም የለጋምቦ እረኞች ትኩረት ሰጥተው የሚያዜሙት የቃል ግጥም ከመሆኑም በላይ በማህበረሰቡ ዘንድም ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ነው።

---

[15] *እንደ መረጃ አቀባይ አልዩ ይማም (የካቲት 5/2004) አገላለጽ በዚያ አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በተራራ ይመስላሉ ማለትልክ ተራራ ከሜዳ እደሚለይ ሁሉ ባላቸው ሃብት እና ለሃገሩ አስታራቂ ሽማግሌ በመሆናቸውና ከማንኛም ተራ ሰው ይልቅ የተለየ ክብር ስላላቸው "ልዩ" መሆናቸውን ለመግለጽ ነው።*

[16] *እንደ ከሳቴ ብረሃን የዐማርኛ መዝገበ ቃላት ትንቢት የሚለውን እግዚአብሄር እንዲኽ አለኝ እያለ በመንፈስ ቅዱስ አለባዊነት ወደ ፊት የሚሆነውን ነገር አስቀድሞ መናገር፣መተንበይ ወይም ትርጓሜን መተርጐም የሚችል በማለት ትርጓሜ ሰጥተው ይገኛል (1970፣538)።*

እረኞች የትንቢት ቃል ግጥም ሲገጥሙ ወደፊት ይህ ይሆናል፣ ይመጣል በማለት ወደፊት የሚሆነውን ነገር በማስጠንቀቂያ መልክ ለአካባቢው ማህበረሰብም ሆነ ለሌላ አካባቢ ሰው ይናገራሉ። ይህን ሲያደርጉ መጀመሪያ ሁሉም እረኞች ከቤታቸው ቆሎ በቁርቁምባ በመያዝ የያዙትን ቆሎ አንድ ቦታ ቁጭ ብለው በመቀላቀል ይበላሉ። ቆሏቸውን በልተው ከጨረሱ በኋላ "እልዊ አህያ መጣች ተጭና እንደዚህ ይሆናል" በማለት በፍርድ መልክ በቃል ግጥሞቻቸው ይናገራሉ። ታዲያ ይህ ጉዳይ በማህበረሰቡ ዘንድ ታማኝነትን ያተረፈ ከመሆኑ የተነሳ "እረኛ ምን አለ?" ተብሎ መጠየቅ በአካባቢው የተለመደ ነው። ይህን ጉዳይ በእረኝነት ህይወት ውስጥ ያለፉት አቶ ከበደ አደፍርስ አሁንም በእርጅና ዘመናቸው በክብት ጥበቃ ላይ ያሉ የሰማንያ አመት አዛውንት እንዲህ ይገልፁታል።

> *እረኞች ጊምባ ቱሉ ዓውልያ ላይ ተሰብስበው የርማ ገበያ ቅርባቸው ስለነበር ጫት ገዝተው፣ ቆሎ በቁርቁንባ ይዘው፤ ቆሎ እየበሉ ጫቱን እየቃሙ የሚነግራቸው አካል በመካከል ላይ ይገኛል። የሚመጣውን ዘመን፤ የሚዘፈነውን ዘፈኑን ሁሉ፤ ታሪኩን ሁሉ በመካከላቸው ሆኖ በተሰወረ መልኩ በቃል ያስረዳቸዋል። ያንን ይዘው በእየቦታቸው እየተበታተኑ እልዊ በሚል የዜማ ቋንቋ እንደ ትንቢት በግጥም ይናገራሉ (ቃለመጠይቅ፣ የካቲት፣ 24/2004 ፣ካሴት ቁጥር 6፣ለ) ።*

እንደ መረጃ አቀባዩ የእረኞች ትንቢታዊ ቃል ግጥም ጥንትም የነበረና ግጥሙን የሚቀነቅኑት በራሳቸው ብቻ ሳይሆን በአጋዥ ሃይል ጭምር እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ይህ ጉዳይ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ቦታ አለው። ይህም የሆነው ከአሁን በፊት በእረኞች አንደበት በቃላዊ ግጥም የተዜሙ የትንቢት ግጥሞች ይሆናሉ ተብለው ስለሚታመን ነው። በቤተመንግስት አካባቢ ያሉ ባለስልጣናት ሳይቀሩ በጉዳዩ በመመስጥ "የጊምባ እረኛ ምን አለ?" በማለት ጠይቀው የሚረዱበት ጊዜ እንደነበር ከበደ ፋሪስ ሲገልጹ፡-

> *ንግግራቸው እንደ ተጫዋቾች ግጥም በግጥም የተሞላ ነው። እልዊ እያሉ የአነጋገር ቋንቋ አላቸው እንዲህ ይደረጋል፤ እንዲህ ይደረጋል በማለት ይገጥማሉ። ያ ነገር በቤተመንግስቱም ሆነ በህዝቡ ላይ እነሱ ያሉት ነገር እየተደረገ ስለሚታይ ህዝቡም ያምንበት ነበር በማለት ነው (ቃለመጠይቅ፣ የካቲት፣ 20/2004)።*

ታዲያ እነዚህ እንደ "ነቢይ" የሚታዩ የለጋምቦ ወረዳ እረኞች በየአካባቢያቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የሚሰጣቸው ክብርና ቦታ ታላቅ ነው። አንዳንዴም እንደ ቁልፍ "አዝራር"፣ ሳንቲምና ብር እየሰጡ ወደፊት የሚሆነውን ነገር ከነሱ መጠየቅ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድም ሆነ ከአካባቢው ውጭ ባሉ ነዋሪዎች የተለመደ ነው። እረኛ ትንቢት ተናጋሪ፣ ወደፊት የሚሆነውን

ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ እንድሪስ የሱፍና ሠይድ ይማም እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል፡-

> *በያዙት ቆሎ ጎራ ላይ ይቀመጡና "ዱአ" ያደርጋሉ፡፡ ቆሏችንን ከበላን ዝናብ ይጥልልናል እያሉ እክትት ዝናብ መታን እንግዲህ በጎቻችንን እናምጣ ወደቤታችን እንሂድ ይላሉ፡፡ በፀሐዩ ማለት ነው፡፡ እንግዲህ ምን ይብቃን በማለት ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ መጠንቀቂያ "እርሙን" አላቸው(የራሳቸው የአምልኮ ጸሎት) በአርሙናቸው ዝናብ ይጥልላቸዋል (ቃለመጠይቅ፣ የካቲት፣ 20/2004)፡፡*

እንደ መረጃ አቀባዮቹ አባባል የእረኞች ፀሎት መሬት ላይ የማይወድቅ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የተለየ ሀይል አላቸው ተብሎም ይታመናል፡፡ ቱሉ አውልያ በነበረኝ የመስክ ቆይታ በምልከታዬ ማየት እንደቻልኩት አብዛኞቹ የትንቢት ግጥሞች የሚዜሙት በጋራ ሲሆን ግጥሞቹን የሚናገሩትም ቱሉ አውልያ በሚባል ጉራ ስር በጉችን ሲጠብቁ ነው፡፡ የዚህን ጉራ ስያሜ አስመልክቶ እንድሪስ የሱፍ እና ሰይድ ይማም የተባሉ መረጃ ሰጭዎች የሚከተለውን ብለዋል፡-

> *የዚህ ጎራ ስያሜ የተሰጠው በዘፈቀደ ሳይሆን ለእረኞች ግጥምን የሚነግር የአውልያ መፍለቂያ በመሆኑ ነው፡፡ ቱሉ ማለት መፍለቂያ፣ ቱልግ ቱልግ የሚል ሀሳብን የሚሰጥ ማለት ነው፡፡ አውልያ ማለት ደግሞ የሚፈልቀውን ሀሳብ በስውር የሚናገር፣ የማይታይና የማይጨበጥ አካል ማለት ነው፡፡ ለዚህ ነው እረኞች ውስጠ ሚስጥር የሚነግራቸው አለ የምንለው በማለት ማብራሪያ ሰተዋል (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 8/2004 ፣ካሴት ቁጥር 1፣ሀ፣)* ፡፡

የትንቢት ግጥሞቹ ይዘት በዋናነት ካሁን በፊት በእረኞች ተነግረው ተግባራዊ ሆነዋል ተብለው የሚታመንባቸው እና በአሁኑ ወቅት የተባሉ በሚል በሁለት መልኩ ይታያሉ፡፡ በዚህ መንገድ ያየሁበት ምክንያት ከድሮ ጀምሮ ያለውን ተአማኒነት ለማሳየት ነው፡፡

የትንቢት ግጥሞቹ በአብዛኛው በተለያየ አካባቢ ያለን የእርሻ ምርት፣ የመሬት ይዞታ እና የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ከአሁን በፊት በእረኞች በቃል ግጥም በዜማ ተደርድረው ተግባራዊ ሆነዋል በሚል ጊምባ ሜዳ ከብት በሚጠብቁበት ወቅት እስኪ ከአሁን በፊት ከአሁን በፊት በትንቢት መልክ ተግጥመው ተግባራዊነቱን በድርጊት ያያችሁትን ንገሩኝ ብዬ በምተይቅበት ሰአት ከእረኞች መካከል አንዱ የሆነው ከበደ ፋሪስ ይሆናል በሚል ስሜት ቀጣዩቹን ግጥሞች ደርድሯል፡-

*ቃል ግጥም 90፦ አሀያ መጣች ተጭና ሻሽ*
*ኃይለ ስላሴ አጥብቀህ ሽሽ፡፡*

*ቃል ግጥም 91፦ አሀያ መጣች ተጭና ጓሳ*
*እንግዲህ ደርጉ ጓዝህን አንሳ፡፡*[17]

በተራ ቁጥር 90 የተቀመጠው የትንቢት ግጥም በፊት የኃይለ ስላሴ አገዛዝ ከመውደቁ በፊት ቀድመው የተነገሩ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ የአስተዳደር ስርዓት እንደሚያበቃለት የሚነግሩ ቃል ግጥሞች በመደርደር ተንባይነታቸውን "*ኃይለ ስላሴ አጥብቀህ ሽሽ*" በማለት እንደገለጹ ይናገራሉ፡፡ በተራ ቁጥር 91 እንደሚታየው ደግሞ የደርግ አስተዳደራዊ ስርዓት የስልጣን እርካቡን ከረገጠ በኋላም እረኞች አስተዳደራዊ ስርዓቱ ሳያበቃ ወደፊት እንደሚገረሰስ ቀድመው "*እንግዲህ ደርጉ ጓዝህን አንሳ* " በማለት በየጊዜው ለሁሉቱም ትንቢታዊ የቃል ግጥሞችን ደርድረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

‹ኢህአዴግ› ወደ ስልጣን ከመምጣቱ በፊት የአካባቢው የእርሻ ምርት የተሻለና ዘመናዊ እንደሚሆን ጊምባ ሜዳ አካባቢ የእረኝነት ልብሱን ከላይ እስከ ታች ለብሶ (ለምድ፣ጉኒና፣ጅብአይበላሽና ቁንጣ) ከብት በመጠበቅ ላይ የሚገን እንድሪስ ሃሰን የተባ እረኛ እንዲህ ተብለ ነበር ሲል ቀጣዮን ቃል ግጥም ደርድረዋል፦

*ቃል ግጥም 93 ፦ አሀያ መጣች ተጭና ለምድ*
*አንድ ትልም እርሶ ሁለት ጉድጓድ፡፡*

በግጥሙ እንደተገለጸው የሚታረስው መሬት ትንሽ *ቢሆንም የሚሰጠው ምርት ጥሩ እና አጥጋቢ ነው፡፡* "*አንድ ትልም አርሶ ሁለት ጉድጓድ*" ሲል ከአንድ ማሳ ለዚያውም አንድ መስመር ታርሳ ሁለት በመሬት ውስጥ የሚቀበር ጉድጓድ እህል እንዲያገኙ እና የምርቱን መጠን የተሻለ እንደሚሆን ያሳያል፡፡ በሌላ ሁኔታ እነዚህ ሰዎች ምርታቸው አድጓል በሚል ስሜት የሚኖሩበት ቤት ከሳር ወደ ቆርቆሮ ቢሽጋገርም ቆርቆሮ ለመግዛት ሲሉ ሀብታቸውን አፍስሰው ለረሀብ ይጋለጣሉ በሚል ጊምባ ሜዳ ከብትን ሲጠብቅ ያገኘሁት እረኛ እንዲህ ብለው ነበር በማለት ቀጣዮን ቃል ግጥም ደርድረዋል፦

*ቃል ግጥም 94፦ አሀያ መጣች ተጭና ቅጠል*
*ቆርቆሮ ሰርቶ በረሀብ መቃጠል፡፡*

---

[17] መረጃ ሰጭ ፦ ሰይድ ይማም (እድሜ 25)፣ መቀርጨሜ ቀበሌ፣ ነገዶና እረኛ፣የካቲት 20/2004፣ቱሉ አውልያ፡፡

የቃል ግጥሙ ድምጸት ገበሬዎች ያመረቱትን ምርት በርካሽ ዋጋ እየሸጡ በውድ ዋጋ ቆርቆሮ ስለሚገዙ የረሃብ ክርን አድቅቋቸዋል፤መትቷቸዋል። ይህንንም ሃሳብ "*ቆርቆሮ ሰርቶ በረሀብ መቃጠል*" በሚለው ስንኝ ቆርቆሮ መስራታቸው ከስም እና ከረሃብ ውጭ የሚያመጣላቸው አንዳችም ነገር እንደሌለ በምሬት መግለጽ የፈለጉ ይመስላል። እንዲሁም በአባሪው ውስጥ ከተራ ቁጥር 96-120 የተቀመጡት ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ይዘት ይዘው እንመለከታለን።

በመስክ ቆይታዬ በሌላ መልኩ አሁን ላይ የተነገሩ ትንቢታዊ ቃል ግጥሞችም ለመሰብሰበ ችያለሁ። እነዚህ ቃል ግጥሞች በአጭር ጊዜ ወይም በረዥም ጊዜ ሊፈፀሙ እንደሚችሉ የቃል ግጥሞቹ ተናጋሪዎች ያምናሉ። እነዚህን የትንቢት ግጥሞች በአሁኑ ሰአት የሚገጥሙበት ቦታ ቱሉ ጎራ ይባላል። ቦታው ሜዳ ሳይሆን አንድ መለስተኛ ጎራ አለችበት። በዚች ጎራ (ጋራ) ስር እረኞች ተሰብስበው መጀመርያ አንድ ግጥም ደርደሪ ከመካከላቸው ይመረጣል። የሚመረጠው ግጥም ደርዳሪ በፍላጎት ጭምር ነው። ከዛም ይህ ታይቶኛል በሚል በትንቢት መልክ ይናገራል ። በዚህ መልኩ ትንቢት ተናጋሪዎቹ ይፈራረቃሉ። መስረጃ ይሆነኝ ዘንድም የሶስት እሮኞችን የትንቢት ግጥም ወስጀ መልእክታቸውን እንደሚከተለው አያለሁ፡-

*ቃል ግጥም 95፡- አሀያ መጣች ተጭና ገንቦ፣*
*በልግ በለገ ወደ ለጋምቦ።*

ከቃል ግጥሙ እንደምናየው ለጋምቦ አካባቢ እህል የሚዘራው ሁለት ጊዜ ነው ይህም የመጀመሪያው በሃምሌ እና ነሃሴ ዝናብ በሚጥልበት ጊዜ የሚዘሩበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጠርና የካቲት በበልግ ወቅት እህልን ይዘራሉ። ነገር ግን የበልግ ዝናብ በ2004 በታሰበበት ጊዜ አልጣለም በዚህን ጊዜ እረኞች በተራ ቁጥር 95 የተጠቀሰውን ቃል ግጥም በተረጋጋ ድምጸት ወደ ለጋምቦ የበልግ ዝናብ እንደሚጥል "በልግ በለገ ወደ ለጋምቦ" በሚለው ስንኝ እንደሚታየው ተናግረዋል። ይህንንም ከየካቲት ሶስት እስከ ሃያሶስት የመጀመሪያ ዙር የመስክ ቆይታዬ ሲያዜሙ ሰምቼ ነበር። ታዲያ ከአንድ ወር በኋላ ዝናብ በመዝነቡ የአካባቢው ገበሬዎች የተለያዩ ጥራጥሬዎችን መዝራት እንደቻሉ ከሚያዝያ አራት እስከ አስራ ሶስት በነበረኝ ሁለተኛ ዙር የመስክ ቆይታ ተመልክቻለሁ።

ከላይ እንደተገለጸው ጥር አጋማሽ ጀምሮ በለጋምቦ አካባቢ በብዛት የበልግ እህል የሚዘራበት ጊዜ ነው። ይሁን እንጂ በወቅቱ ዝናብ አልነበረም። ከዝናቡ መጥፋት ጋር ተያይዞ ደግሞ የእህል ውድነት በአካባቢው ይፈጠራል። ይህንን ጉዳይ እረኞች በቃል ግጥማቸው ሲናገሩ በልግ ስለሚበልግ እህል ይረክሳል፤ እናንተ ለጤናችሁ አስቡ ብለዋል።

*ቃል ግጥም 97፡- አህያ መጣች ተጭና ሞሰብ፣*
*እህል ይረክሳል ለጤናህ አስብ፡፡*

ከላይ በቃል ግጥሙ እንደምናየው አህያዋ ተጭና የሚትመጣው ሞሰብ ነው ሞሰብ ደግሞ ለእንጀራ መያገሮነት የሚያገለግል ነው፡፡ ስለዚህ አይዟችሁ ለጤናችሁ አስቡ እህል እንደሆን ይረክሳል በማለት ለእንጀራ መያገሮነት የሚያገለግለው ሞሰብ ለብስራት ማብሰሪያነት ተጠቅመው ስለ ወደፊት እህል መርከስ በቃል ግጥማቸው ተናገረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወደፊት ይመጣል ብለው የተናገሩት ከበርበሬ ውድነት ጋር ተያይዞ ነው፡፡ ይህም ቀጣዩን ይመስላል፡-

*ቃል ግጥም 96፡- አህያ መጣች ተጭና ለበቅ፣*
*በርበሬ ጠፍቷል ሳማህን ስበቅ፡፡*

በማለት በርበሬ እጅግ በጣም ስለሚወደድ በምትኩ እንደበርበሬ ሊያቃጥል የሚችለውን ሳማ ትጠቀማላችሁ ሲሉ "*በርበሬ ጠፍቷል ሳማህን ስበቅ*" በሚል የማስጠንቀቂያ ስሜት አዘል ቃል ግጥም በርበሬ እንደሚጠፋ ተናግረዋል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ የትንቢት ቃል ግጥሞች በህብረተሰቡ ዘንድ "እረኛ ዛሬ ምን አለ?" በሚል በየጊዜው ያለውን ሁኔታ የሚጠየቁበት አጋጣሚ ከጥንት ጀምሮ አሁን ድረስ እንዳለ ከቃል ግጥም ደርዳሪዎቹ ጠይቆ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህም እረኞች በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ቦታ እና ተደማጭነት እንዳላቸው ከላይ በተሰጠው ማብራሪያ መረዳት ይቻላል፡፡ ከነዚህ ቃል ግጥሞች ይዘት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው በአባሪው ውስጥ ከተራ ቁጥር 121-140 ይገኛሉ፡፡

## 5.4. ምክር ለጋሽ የቃል ግጥሞች

እረኞች በቃል ግጥማቸው እንደሚያሞግሱና እንደሚተቹ ሁሉ መልካም ነው ብለው ያሰቡትን ነገርም በምክር መልክ ይለግሳሉ፡፡ በዚህም የሚያስተምሩ፣ የሚገስፁ እና የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የሚያነሱ ቃል ግጥሞችን ገጥመዋል፡፡ በመሆኑም ጠንክሮ የመሥራት አስፈላጊነት፣ የሥደት መጥፎነት፣ አስተዋይነትና አስቀድሞ መጠንቀቅን ገልጸዋል፡፡

የአካባቢው ማህበረሰብ በዋናነት በከብት ማድለብና በእርሻ የሚተዳደር እንደመሆኑ መጠን እርሻን በተገቢው ሁኔታ ማረስ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል፡፡እረኞች ጥሩ አድርጎ ማረስ ጥሩ የሆነ ውጤት አለው በማለት ይመክራሉ፡፡ ይህንም ቱሉ ጎራ ያሉ ኑርየ ጋሻውና ብረዲን ሃምዛ

የተባሉ እረኞች በርካታ ቁጥር ካላቸው ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ከብትን ሲጠብቁ ወኔ በተላበሰ መልኩ በፉከራና በቀረርቶ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ካቅረሩ ቡሃላ በፉከራ መልክ ሲያወርዱ ታዳሚው "አሃ" በሚል ድምጽና በጭብጨባ ሲያጅባቸው ነበር፡፡ ይህም ወኔን (ድፍረትን) እደፈጠረላቸው በምልከታየ ለማየት ችያለሁ፡፡ ቃል ግጥሞችም የሚከተሉት ናቸው፡-

*ቃል ግጥም 141፡- ማረስ ነው እንጂ ገልበጥበጥ አርጎ እዲቡ ድረስ*
*የመጣ እንግዳ በልቶ ጠጥቶ ጠግቦ እንዲመለስ፡፡*

*ቃል ግጥም 142፡- እርሻ ነው ማረስ "ዲብ" አዘልሎ*
*ቀይ ሴት አይቶ አይሆንም ኑሮ፡፡*

የቃል ግጥም ደርዳሪው የተሳካና የተቃና ኑሮ ለመኖር ገበሬ አባጣ ጎርባጣ ሳይል ማረስ ይበጀዋል የሚል ምክርን ይለግሳል፡፡ በግጥሙ አራሽነት የተለካው በጥሩ ሁኔታ አገላብጦ ከማረስ ጋር ነው፡፡ ለዚህም ነው **"ማረስ ነው እንጂ ገልበጥበጥ አርጎ እዲቡ ድረስ"** በማለት ከጥግ እስከ ጥግ ማረስ ለዘመድም ለራስምኡራት መሆኑን የገለጸው፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ገበሬ በቀይ ሴት ላይ አይኑን እየጣለ የሚኖር ከሆነ ኑሮው የተጎሳቆለ እንደሚሆን ***"ቀይ ሴት አይቶ አይሆንም ኑሮ"*** በሚለው ስንኝ ለገበሬው በአርፊህ ተቀመጥ ስሜት ትኩረቱ እርሻ ላይ እንጂ ቀይ ሴትን አይቶ መጎምገፖት ላይ እንዳይሆን የቃል ግጥም ደርዳሪው ይመክራል፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 168 ያለውን ቃል ግጥም መመልከት ይቻላል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በሃገራችን እየተካሄደ ያለውን ስደት አስመልክቶ ምክር የሚለግሱ የቃል ግጥሞችም አሉ፡፡ እነዚህም የሰው ሀገር ከመሄድ ይልቅ የራሳችንን ሃገር ብናለማ የተሻለ እንደሆነ የሚገልጹ ናቸው፡፡ የቃል ግጥሞቹ ከገጠር ወደ ከተማ እና ከሃገር ውስጥ ወደ ውጭ ሃገራት የሚደረገው ስደት ይብቃ የሚል የምክር ይዘት አላቸው፡፡ በዚህም ሃሳብ ከገጠር ወደ አዲስ አበባ የሚደረገውን የስደት አላስፈላጊነት አስመልክቶ እረኛ እንዲሪስ አሰን ምስት አካባቢ ጊምባ ወንዝ ከብቶችን ውሃ ሲያጠጣ አግኝቸው ቀጣዩን ቃል ግጥም ደርድራል፡-

*ቃል ግጥም 143፡- ፍየል ቅጠል እንጂ አይበላም ገለባ*
*ምንድነው ስደቱ ወደ አዲስ አበባ*
*በራስ ሀገር ሰርቶ መሆን ነው ደርባባ፡፡*

ከቃል ግጥሙ እንደምናየው ስደቱ ከክፍለሃገር ወደ አዲስ አበባ ነው፡፡ የዚህን አላስፈላጊነትም በምክር የሰው ሀገር መሻት ወይም መመልከት እንደራስ አገር አይሆንም ስለዚህ በሃገራችን ጥሩ ስራ እንስራ በማለት ይናገራሉ፡፡ በተጨማሪም በራሳችን ሃገር ሰርተን መለወጥና መሻሻል

እንዳለብን በቃልግጥሙ ውስጥ *"በራስ ሀገር ሰርቶ መሆን ነው ደርባባ"* በሚለው ስንኝ በራሳችን ሃገር ሰርተን የሚያስደስት ነገርን መፍጠር እንጂ ስደት አይጠቅምም በማለት ይመክራሉ፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ ወደሌሎች የውጭ ሃገራት የሚደረገውን ስደት ተገቢ እዳልሆነ እረኛ አህመድ በሽር ጭሩ ሜዳ ከብቶችን ሲጠብቅ በፋከራ ሲደረድራቸው ከነበሩ ቃል ግጥሞች መካከል ቀጣዩን ግጥም ለማሳያነት ወስጃለሁ፡-

*ቃል ግጥም 144፡-* *ያያ ሸማግሌ ውሃ ነው ቀለቡ*
*ምነው ባረብ አገር አይኖችህ አይኖችሽ ባይቅለበለቡ፡፡*[18]

የቃል ግጥም ተናጋሪው ወደ አረብ ሃገር መመልከትን ከሸማግሌ ጋር በማያያዝ ከአረብ ሃገር በሚመጣ የልጆች ላብ ኑሯቸውን የመሰረቱ ተጧሪዎችን የሃገራችሁን ውሃ ጠጥታችሁ ኑሩ በሚል ይመክራል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ለምን የሰው ሃገርን እንመኛለን በሚል *"ምነው ባረብ አገር አይኖችህ አይኖችሽ ባይቅለበለቡ "* በሚለው ስንኝ ሴትም ሆን ወንድ ወደአረብ ሃገር ለመሄድ መጓጓታቸው ተገቢ እንዳልሆነ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ እረኛ እንዲሪስ አሊና አህመድ በሽር ጭሩ አካባቢ በሚገኝ ወንዝ ወደ ማታ አካባቢ ከብቶችን ውሃ አጠጥተው ሲጨርሱ ከብቶቹን ወንዙ አካባቢ በሚገኝ ጨሌ ላይ በማጋጥ ከበርካታ ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ሌሎች ቃል ግጥሞችን በቀረርቶና በፋከራ መልክም በተለያዩ እንስሳትና እፅዋት በመመሰል ሲያዜሙ ለማስተዋል ችያለሁ፡፡ ለዚህም እንደምሳሌ ቀጣዩን ቃል ግጥም እንይ፡-

*ቃል ግጥም 145፡-* *ኧረ ምን ቢሆን ነው ኧረ መርዙ*
*እሱ ያመጣውን እሱ እስኪመልሰው*
*ምነው ባገሩ ላይ በቆማጣ ፈረስ*
*አርሶ አይበላም ወይ ሰው፡፡*

ከስንኞቹ እንደምንረዳው እረኞች የስደትን አላስፈላጊነት በቀረርቶና በእንጉርጉሮ መልክ ለምን ተብሎ ምን ሲደረግ እኛ ጀግና እና ደፋር ነን እኮ በማለት *"ኧረ ምን ቢሆን ነው ኧረ መርዙ"* በሚለው ስንኝ ለስደት መጋለጥ የለብንም ሲል ይገልፃል፡፡ ፈጣሪ ያመጣውን ነገር ፈጣሪ እስኪመልሰው የምናርስበት በሬ ብናጣ እንኳ ከምንሰደድ በቆማጣ ፈረስም ቢሆን አርሰን ብንበላ ይሻላል በሚል *"ምነው ባገሩ ላይ በቆማጣ ፈረስ አርሶ አይበላም ሰው"* በሚለው ስንኝ በማስረገጥ

[18] መረጃ ሰጭ ፡- አህመድ በሽር (እድሜ 12)፣ ጭሩ ቀበሌ፣ እረኛ፣ ሚያዚያ 5/2004፣ ጭሩ ሜዳ፡፡

የስደትን አላስፈላጊነት መረር ባለ ሁኔታ አሳይቷል። በተመሳሳይ አህመድ በሽር ይህንኑ ጉዳይ በቀጣዩ ቃል ግጥም እንዲህ ሲል ያቀነቅናል፡-

*ቃል ግጥም 146፡- ተይ በሏት ያችን ላም ከስደቱ ላይ*
*ተው በሉ ያን በሬ ከስደቱ ላይ*
*ተው በሉ ያን በሬ ከገደሉ ላይ*
*እሱ ሳሩን እንጂ አሳሩን አያይ።*

እንደ ቃል ግጥሙ ተናጋሪ አገላለጽ በሃገራችን ወደ አረብ ሃገር የሚሰደዱ ሰዎች የሚያገኙትን ብር እንጂ የሚደርስባቸውን ስቃይና መከራ አያዩም ተይ በሏት ያችን ላም፣ ተው በሉ ያን በሬ ከስደቱ ላይ በሚል ማስጠንቀቂያዊ በሆነ ድምጸት ይገልጻል። ከዚህም በላይ የሚመጣውን ችግር እና መከራ ለመግለጽ *"እሱ ሳሩን እንጂ አሳሩን አያይ"* በሚለው ስንኝ ገንዘቡን እንጂ ሊመጣ የሚችለውን መከራና ስቃይ እንደማያስተውሉ በበሬ በመመሰል በሬ ገደል ላይ ሳር ቢያይ ሳሩን እንጂ ወደ ገደል በመግባቱ የሚመጣበትን አደጋ አያይም። በስደት ከሃገራቸው ወደውጭ የሚሄዱ ሰዎችም ለጊዜው ብር (ገንዘብ) ማግኘታቸውን እንጂ ያለውን አስቸጋሪ ሁኔታ አያዩም። ስለዚህ ይጠንቀቁ የሚል ምክርን በቃል ግጥማቸው ሲለግሱ ይታል። በተጨማሪም በተራ ቁጥር 142፣143፣144 እና145 ለትንተና ከተመረጡት ቃል ግጥሞች ጋር ተመሳሳይ ይዘት የያዙት በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 154፣ 155፣ 156 እና 167 የተቀመጡ ቃል ግጥሞች ናቸው።

በሁሉም ማህበረሰቡ ውስጥ ሃብታም እንዳለ ሁሉ ደሃም አለ። እረኞች ይህ ልዩነት እንዴት እንደተፈጠረና ድህነት የሚባለው ልጥፍ መግለጫ በምን እንደሚመጣ እና የስራን ታላቅነት እረኛ ከበደ በርካታ ከብቶችን ጊምባ ሜዳ ከጠዋት አራት ስአት አካባቢ ሲጠብቁ ቃል ግጥም እንዲነግሩኝ በምጠይቅበት ወቅት በርካታ የራሳቸውን ሃብትና ንብረት የሚገልጹ ቃል ግጥሞችን ከደረደሩ በኋላ እንደማሳረግያ ስለድህነት በቃል ግጥማቸው እንዲህ በማለት አቀንቅነዋል፡-

*ቃል ግጥም 147፡- ድህነት እብድ አይደል ዘሎ አይጨመድድ*
*ግን ሰነፍ ካገኘ ካሰረም አይሰድ።*

በቃል ግጥሙ እንደተገለጸው ድህነት የሚባለውን ነገር የምናመጣው ባለመስራት እና በስንፍና እንጅ እንደፈንጣ ዘሎ የሚጣበቅ እንደ እብድ ዘሎ የሚይዝ እዳልሆነ *"ድህነት እብድ አይደል ዘሎ*

አይጨመድድ " በሚለው ስንኝ ድህነትን በእብደት በመወከል ይመክራሉ። ድህነት ዘሎ አይጣበቅምና ከሰራን አይቀርበንም በማለት ጠንክሮ በመስራት መለወጥ እደሚቻል ፤ ካልሰራን እና የስንፍና አባዜ ካለብን ግን ድህነት አጥመልምሎ እንደሚያስቀምጠንና ይበልጥ ችግርን እንደሚያባብስ ለመግለጽ **"ግን ሰነፍ ካገኘ ካሰረም አይሰድ"** በማለት የድህነትን የከፋ ውጤት በማሳወቅ በርትተን እንድንሰራ፣በድህነት ላይ እንድንዘምት ፣ስንፍናን አሽቀንጥረን እንድንጥል ምክሩን ይለግሳል። በአጠቃላይ ምክራዊ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች በአባሪው ውስጥ ከተራ ቁጥር 141-168 ቀርበዋል።

## 5.5. *ሥድባዊ የቃል ግጥሞች*

እረኞች በእረኝነት ሥፍራ እርሥ በርሥ ይሰዳደባሉ። ሥድድቡ አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን ብቻ የሚመለከት በሌላ ጊዜ ደግሞ ያሉበትን ቀበሌ ህዝብ የሚመለከት ነው። ትኩረታቸውም ከፀባይ፣ ከሙያ፣ ውበት፣ ጀግንነት (ከድፍረት እና ፍረሀት)ና ሃብት ጋር የተያያዘ ነው። በአብዛኛው የተወሰነ ክፍተት ተራርቀው በቅብብሎሽ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በሚል ስሜት አንዱ ያንዱን ሃሳብ በመጣል ይሰዳደባሉ።

በለጋምቦ ወረዳ የሚገኙ እረኞች በስድብ መልክ ከሚገልፁት ማህበራዊ አጋጣሚ አንዱ ጀግንነት ነው። ወንድ ልጅ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ታግሎ ካላሸነፈ፣ አርሶ ጥሩ ምርት ካላመረተ፣ በግ ገዝቶ ካላረባ እንዲሁም ሌሎች በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅ የሆኑ ሰናይ ተግባራትን ካልፈፀመ ጀግና አይባልም። የቃልግጥሙ ተናጋሪ ጭሩ ሜዳ ከብቶችን በመጠበቅ ላይ ሳለ በቀረርቶ መልክ የወንድነትን መለክያ ሲገልጽ በሳች ዘንድ የተለየ ባህሪ ሲኖረው እንደሆነ በልበ ምልዑነት ብትሩን በትከሻው ላይ አስቀምጦ እየተጀነነ የሚከተለውን ቃል ግጥም በቀረርቶ አውርዷል፦

*ቃል ግጥም 169፦* *ኽራ ጎራው ኽረ መርዞ (2)*
*ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ*
*ከዳገት አቃኑት ሳር ይብላ እንደ በሬ።*

ከቃል ግጥሙ እንደምናየው ወንድ ልጅ ተወልዶ “አጅሬ” ወይም ደፋር፣ ጀግና ካልተባለ ክብር አይሰጡም እንደ ከብት ይቆጠራል እንጂ። ምክንያቱም ከብት ምንም አያውቅም ወንድ ልጅም ተወልዶ ጀግና ካልሆነ ከከብት ስለማይሻል እዳገት አቃኑት ሳርይብላ በማለት *“ከዳገት አቃኑት ሳር ይብላ እንደ በሬ”* በሚለው ስንኝ ስድብ አዘል ድምጸት ባለው ቃል ግጥም ይነግራሉ። ከዚህ

ቃል ግጥም ጋር ተመሳሳይ ይዘትን የያዙ ቃል ግጥሞች በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 186፣198 እና 200 ተቀምጠው ይገኛሉ።

እረኞች ከላይ ከተገጸው የቃል ግጥም ይዘት በተጨማሪ ስለ ሴት ልጅ ፀባይና በማህበረሰቡ ውስጥ ምን ቦታ እንደሚሰጣትም ስድባዊ ይዘት ባላቸው ቃል ግጥሞች ይገልጻሉ፡-

*ቃል ግጥም 170፡- ከበጎቹ ሁሉ ሆሊት ትበልጣለች*
*ከንፈርዋን ከሳምዋት ሴት ልጅ ትቀብጣለች።*

ከቃል ግጥሙ እንደምንረዳው የሴትን ልጅ ባህሪ *"ሆሊት"* በምትባል ሴት በግ በመመሰል ሴት ልጅ ከንፈርዋን ከተሳመች የምትይዘው የምትጨብጠው ይጠፋታል፤ ልብ ታጣለች በማለት የበግን ፀባይ ለሴት ልጅ በማላበስ ሲገልፁ ይታያል። በተመሳሳይ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ሴት ልጅ የሚሰጣት ክብር ቁልፍ መረጃ አቀባይ የሆኑት ከበደ ፋሪስ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡ *"ኢህአዴግ› ከመጣ በኋላ የሴቶች የእኩልነት መብት አለ ቢል እንኳ እኛ አንቀበለውም ምክንያቱም እንኳን እሱ ባለው መልኩ መብት ሰጥተናቸው አንዳንድ ቀን ስብሰባ ላይ በሰሙት የመብት አላችሁ ወሬ እንኳ አልቻልናቸውም"* በማለት ማብራሪያ ሰጥተዋል (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት ፣18/2004) ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው አመለካከት ሴት ልጅ የተፈጠረችው ለስራ እንጂ አደባባይ ውላ የአደባባይ ስራን እንድትሰራ አይደለም የሚል ስድብ አዘል ድምጸት ያለው ቃል ግጥም ሲያወርዱ፡-

*ቃል ግጥም 171፡- ያህያ ልጅ ፈሳም የጅብ ልጅ ደንደሳም*
*ሴትን ለስራ እንጂ ማን አለ ለዙፋን፡*

ይህን የቃል ግጥም የደረደረልኝ የ12 አመት እድሜ ያለው እረኛ ጭሩ ሜዳ ከጓደኞቹ ጋር ከብቶችን ሲጠብቅ ለሴት ልጅ ያለውን አመለካከት በንቀት መልክ በቃል ግጥሙ ገልጿል፡፡ የቃል ግጥም ተናጋሪ እንደሚገልጹው ሴት ልጅ በቤት ውስጥ የተለያዩ ሥራ እንድትሰራ እንጂ ስልጣን ምን ይሰራላታል? በማለት ሴት ልጅ ክብር እንደማያስፈልጋትና ቢያስፈልጋት እንኳ እንደሌላት ይናገራሉ፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ሁለት ፍቅረኛሞች ጭሩ ሜዳ ከብቶችን በሚጠብቁበት ወቅት በቃል ግጥም ሲሰዳደቡ እንመለከታለን እነዚህ ሁለት የፍቅር ጓደኛሞች በቅርብ ስለሚተዋወቁ እሱ የፀጉርዋን ንጽህና ጉድለት ሲገልጽ የሚከተለውን ይላታል፡-

*ቃል ግጥም 62፡- ያቀስታ መኪና ማረፊያው ደሴ ነው*
*የፀጉርሽ ቆሻሻ አይኔን ሊያጠፋው ነው፡፡*

ብሎ ሲሰድባት እሷ ደግሞ ቀደም ብላ የሆዱ ነገር ሞቱ እንደሆነ ስለምታውቅ ያን አንስታ እንዲህ ስትል ትሰድበዋለች፡-

*ቃል ግጥም 63፡- የፍቅርን ነገር ከቶ የት አውቀኸው*
*ከምጣዱ ቂጣ አይንህን ተክለኸው*
*ጎረምሳው ወዳጄ ውቃቢ የሸሸው*
*ቂጣውን ጨረሰው ተልባውን እስካሸው*
*ዘጠኝ ቂጣ በልቶ አንድ ሲቀረው*
*አይ ጤና ማጣት ብሎ አስቀመጠው፡፡*

በዚህ ስንኝ እንደምናየው ወንዱ ከፍቅር ይልቅ ለሆዱ ቅድሚያ እንደሚሰጥ፣ ቂጣ ጋግራና ተልባ አሽታ እስከምትሰጠው እንደሚቸኩል በልቶም የበላ እንደማይመስል በግጥም ትነግረዋለች፡፡ በተራ ቁጥር 62 ከተገለጸው ቃል ግጥም ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 174፣178፣190፣191 እና 192 ያሉት ሲሆኑ በተራ ቁጥር 63 ላለው ደግሞ 175፣179፣187፣188 እና 189 ተመሳሳዮቹ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የስድብ ቃልግጥሞቹ የእረኞች የፍቅር ህይወታቸውን፣ የሚያደርጉትን ፣ ውበትን፣ ፀባይን፣ የጀግንነትን አስፈላጊነትና የስንፍናን አላስፈላጊነት መሰረት አድርገው የቀረቡ ናቸው፡፡ በአባሪው ውስጥ ስድባዊ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች ከተራ ቁጥር 169-212 ቀርበዋል፡፡

## 5.6. ማሞገሻ የቃል ግጥሞች

እረኞች ውበትን፣የአካባቢውን ማህበረሰብ ደግነት፣ የራሳቸውን ጀግንነት፣ የእርሻን፣ በጎችንና ከብቶችን ምርትንና ሌሎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በጋራ በማንሳት በዜማ መልክ ያወድሳሉ፣ ያሞግሳሉ፣ ያደንቃሉ፡፡ ለጥናት በተመረጡት ቦታዎች በነበረኝ የመስክ ላይ ቆይታ የሙገሳ ቃል ግጥምን የሚከውኑት በአብዛኛው በከብት ጥበቃ ወቅት ወጣቶች ናቸው፡፡ በየግላቸው ግጥምን የሚደረድሩበት አጋጣሚ ቀላል ባይሆንም አልፎ አልፎ

ጥንድ በመሆንም ያወድሳሉ፡፡ ከዚህ በተለየ እረኞች ሰውን ብቻ ሳይሆን ለራሳቸው ከሚሰጡት ክብር የተነሳ ራሳቸውንም እንደሚያወድሱ እረኛ ኑርዬ ጋሻው ቱሉ ጎራ አካባቢ ከብቶችን ሲጠብቅ የሚከተለውን ቃል ግጥም በፉከራ መልክ በጓደኞቹ አጃቢነት ቁጭ ብድግ እያለ ያርደራል፡-

*ቃል ግጥም 213፡-* *ዘራፍ ዘራፍ*
*እጥፍጥፍ ጉጥፍጥፍ እንደ ኩታ ልብስ*
*አስተራረሴ አንጀት የሚያርስ፡፡*

በዚህ ግጥም እንደምንመለከተው ኑርየ ራሱን ሲያሞግስ እኔ እርሻ እችላለሁ በማለት ልክ ኩታ ታጥፎ እንደሚለበስ እኔም ሳርስ ብዙውን የእርሻ መሬት ልክ ታጥፎ እንደሚለበስ ኩታ ቅልጥምጥም፣እጥፍጥፍ አድርጌ በፍጥነት እጨርሳለሁ ሲል "*እጥፍጥፍ ጉጥፍጥፍ እንደ ኩታ ልብስ*" በሚለው ስንኝ ራሱን ገልጿል፡፡ ከዚህም በላይ አስተራረሱ ከራሱ አልፎ ሰዎችን በጥሩ ሁኔታ እንደሚያስደስትም "*አስተራረሴ አንጀት የሚያርሸ*" በማለት ይነግረናል፡፡ ከዚህ ጋራ ተያይዞ ልክ በተራ ቁጥር 213 ያለውን ቃል ግጥም ኑርየ በፉከራ ካወረደ በኋላ ከርሱ ጋር አብሮት ሲፎክር የነበረው ብርዲን ሃምዛ የተባለ ጓደኛው እውነቱን ነው እርሻ ይችላል ሲል ብትሩን ከመሬት ተከል ነቀል እያደረገ በማለት በፉከራ የቃል ግጥሙ ይመሰክራል፡፡ ሲመሰክርም በጣቱ ወደ ጓደኛው በመጠቆም ነው፡፡ ግጥሙ የሚከተለው ነው፡፡

*ቃል ግጥም 214፡-* *ቀጭ ቀጭ እንደ በቆሎ ዕቃ*
*እንኳን ያረሰው የተናገረው እንዱ የሚበቃ*
*እሱ ነው አሉ የወደፊቱ ያገር አለቃ፡*

በቃል ግጥሙ እንደተገለፀው እንኳን ያረሰው የተናገረው ትንሹ እንደሚበቃ ፣ ከዚህም በላይ እሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰዎችም የወደፊት ያገር መሪ ይሆናል እደሚሉት "*እሱ ነው አሉ የወደፊቱ ያገር አለቃ*" በሚለው ስንኝ ልጁ በስራው ታታሪና ጠንካራ ነው ስለዚህ የወደፊት ያገር መሪ ይሆናል በሚል ለጓደኛው ያለውን አድናቆትና ክብር በሙገሳ ሲቸረው ማየትና መስማት ችያለሁ፡፡ ከእነዚህ ሁለት ቃል ግጥሞች ጋር በተያያዘ በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 225፣226 እና 229 የተቀመጡት ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ይዘት ይዘው እንመለከታለን፡፡

በለጋምቦ አካባቢ በአብዛኛው ቤተሰብን፣ አካባቢን፤ ጓደኛን ማሞገስ የተለመደ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ እረኞች ዘንድ ጎልቶ ይታያል፡፡ ይህንንም እረኛ ሁሴን በሸር ገምባ ሜዳ ከብቶችን በመጠበቅ ላይ ሳሉ የአካባቢውን ማህበረሰብ መልካምነትና ደግነት በቃል ግጥማቸው ሲገልጹ፡-

*ቃል ግጥም 215፡- ጊምባ ደጉ ወሎ ደጉ*
*ድርቅ እንኳ ቢመጣ*
*ወላጅ የሌላቸው ያለ አባት አደጉ፡፡*

እንደ ሁሴን ገለጻ በአስራ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሰባት ዓመተ ምህረት በአካባቢው እጅግ ከፍተኛ የሆነ ድርቅ ይከሰታል፡፡ በዚህ ወቅት የአካባቢውን ማህበረሰብ እጅግ በጣም የሚተዛዘንና የሚተሳሰብ በመሆኑ በወቅቱ እናትና አባታቸውን በድርቅ ምክንያት ያጡ ልጆችን ወደ ቤታቸው በመውሰድ በመተባበር ያሳድጉ ነበር፡፡ ይህንን ሃሳብ "*ወላጅ የሌላቸው ያለአባት አደጉ*" በሚለው ስንኝ ለማህበረሰቡ ሙገሳ አቅርበዋል፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ ዘወትር በመልካም ስነ ምግባር ከሚያስጠራቸው ስም ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ምክንያቱም ድርቅ (ችግር) ቢፈጠር እርስ በርስ ስለሚተዛዘኑ የመጣውን ችግር በጋራ በማሳለፍ መጥፎውን ቀን በጥሩ እንዲቀየር ያደርጋሉና ነው፡፡

የለጋምቦ አካባቢ አረኛች የአካባቢው ማህበረሰብ መተዳደሪያ በሆነው የእርሻ ምርትና፣ የበግ እርባታ እንደሚኮሩም እረኛ እንድሪስ አሊ ጭሩ ሜዳ በሚባል የከበት ማስማርያ ቦታ ከብቶቹን ሲጠብቅ በተወለደበት አካባቢ ኩራት እደሚሰማው በተለይም በእርሻና በከብት እርባታ እንዲደሰት እንደሚከተለው በቃል ግጥሙ ገልጾል፡-

*ቃል ግጥም 216፡- አቆልቁለው ሲያዩት ፈረስና በጉ*
*ቀና ብለው ሲያዩት መሀርና በልጉ፡፡*

በቃል ግጥሙ ውስጥ የትውልድ ቀያቸውን ምርት የተትረፈረፈበት፣ የፈረስ ፈንጠዝያ እና ዱካ የማይለየው ቦታ መሆኑን በልበ ሙሉነት ያሳያሉ፡፡ በቃል ግጥሞቹ በአካባቢው እጅግ በርካታና አመርቂ የፈረስ፣የበግና የእርሻ ምርት አጥጋቢነት እንዳለና የእርሻ ምርትም በአመት ሁለት ጊዜ እንደሚያገኙ እና ደስተኛ እንደሆኑ ይጠቁማል፡፡ በተራ ቁጥር 215 እና 216 ለትንተና ከተመረጡት ቃል ግጥሞች ጋር በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 218፣ 119 እና 222 የተቀመጡት ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ይዘት ይዘው እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በተለየ መልኩ ወንዶች ለሚወዷት ሴት፤ ሴቶች ደግሞ ለሚወዱት ወንድ በቃል ግጥሞቻቸው አድናቆትን ይለግሳሉ፡፡ ታዲያ በአካባቢው እጅግ በርካታ ቁጥር ያላቸው እረኞች ተሰብስበው ውሃ ልትቀዳና ኩበት ልትለቅም የመጣችን ሴት ማሞገስ የተለመደ ነው፡፡ በዚህም አንድ ወጣት እረኛ ወደድኩሽ ያላትን ሴት፡-

*ቃል ግጥም 217፡- የበጎች እረኛ ችግ ይላል በጊዜ*
*የሚያረገርገው ወገብዋ እንደመንዜ፡፡*

ልጅትዋ እጅግ በጣም ቀጭንና መካከለኛ ቁመት ያላት ናት፡፡ ወጣቱ እረኛ ይህን ሲገልፅ ቅጥነትዋ መንዜ ከተባለ በአካባቢው አጠራር ቀጭን የጥጥ ፈትል ጋር ሲያነፃፅራት ይታያል፡፡ በዚህም የልጅትዋን አጠቃላይ ውበትና ቅጥነት በተለያየ ነገር በመመስልና በማወዳደር ሲያወድስና ሲያሞግስ ይታያል፡፡ ይህ ቃል ግጥም በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 220፣ 221 እና 223 ከተቀመጡት ቃል ግጥሞች ጋር ተመሳሳይ ይዘት አለው፡፡ በአጠቃላይ ሙገሳዊ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች በአባሪው ውስጥ ከተራ ቁጥር 213-247 ቀርበዋል፡፡

## 5.7. የፍቅር መግለጫ ቃል ግጥሞች

እረኞች ፍቅርን ሽሽግ በሆነ መልኩ ተፈቃሪ ሴቶች ውሃ ሲቀዱ፤እንጨት ሲለቅሙ ወይም በሌሎች አጋጣሚዎች ይገልፁታል፡፡ አብዛኞቹ የፍቅር ግጥሞች በአንድ ሰው ብቻ የሚዜሙ ሳይሆኑ ወንድና ሴት በመሆን በምልልስ የሚቀርቡ ናቸው፡፡

ለጥናት በተመረጡት ቦታዎች በነበረኝ የመስክ ቆይታ ማየት እደቻልኩት በምልልስ የሚያቀርቧቸው የፍቅር ዜማዎች አንዱ የአንዱን ሃሳብ በማስበለጥ በፉክክር የሚያቀርቡበት አጋጣሚ ሰፊ እንደሆነ ማየት ችያለሁ፡፡ ይህም ለምሳሌ ወንዱ ስለ ሴቷ የነበረውን አመለካከት በመጥፎ ቢገልፅባት እሷ ያን ሃሳቡን የሚያስቀለብስ ሌላ ሃሳብ በማዜም ትነግረዋለች፡፡ በመቀርጨሜያ ቀበሌ አካባቢ ከብቶችን የሚጠብቁ ወንዶችና ከአካባቢው ውሃ ለመደት ከመጣች ሴት ጋር በቅብብሎሽ ፍቅራቸውን ይገልጻሉ፡፡ የቃል ግጥሞቹ ምልልስም ፉክክራዊ በሆነ መንፈስ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ስሜት ይንጸባረቅባቸዋል፡፡ በዚህም ሴትዋ አፍቃሪ እኔ ለፍቅር ትልቅ ቦታ ስላለኝ ብሎም ስለማለግም ታምሜ ከርሜ እንኳ እያዘገምኩ መጣሁ ስትል በቃል ግጥም እንዲህ እያለች ፍቅርዋን ትገልጽለታለች፡-

*ቃል ግጥም 248፡- እኔ አንተን አይደለሁ በፍቅር አለግም*
*ታምሜ ከርሜ መጣሁኝ ሳዘግም ፡፡*[19]

ተፈቃሪዋ ፍቅሯን የገለጸችው እሱን ለማግኘት ስትል ታምማ ህመምዋን አላዳመጠችም፡፡ ይህን በየኔ ይበልጥ ስሜት ሃሳብዋን በማፍረስ እሱ ምላሽ ሲሰጣት እኤም ከአንቺ በላይ በፍቅሬ

[19]መረጃ ሰጭ ፡- ስርካለም አስፋው (እድሜ13)፣ መቀርጨሜያ ቀበሌ፣ የቤት ውስጥ አገዥ፣ ሚያዝያ13/2004፣ መቀርጨሚያ ሜዳ፡፡ ፡

ስለማልኮራ እጅግ በጣም ታምሜ እንኳ በከዘራ እየተደገፍኩ ነው ወደ አንች የመጣሁት በማለት ፡-

*ቃል ግጥም 249፡- እኔ አንችን አይደለሁ በፍቅር አልኮራ*
*ታምሜ ከርሜ መጣሁ "በከዘራ" ፡፡* [20]

አፍቃሪው በቃል ግጥሙ ውስጥ አንቺን ለማግኘት ስል በከዘራ እየተደገፍኩ መጣሁ ይላታል ፤ፍቅሩ ከእሷ በላይ መሆኑን እና ለእሟ ያለውን ታላቅ ቦታ ከሟ በማስበለጥ ይነግራታል፡፡ ከዚህ ቃል ግጥም ጋር በተያያዘ በአባሪው ውስጥ በተራ ቁጥር 272፣273፣290፣291፣294 እና 295 የተቀመጡት ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ይዘት ይዘው እንመለከታለን፡፡

በሌላ ምልኩ ደግሞ ቱሉ ጎራ በተባለ የከብት ማሰማርያ ቦታ ከብቶችን ሲጠብቁ ያገኘሃቸው ሁለት ወጣት ወንድና ሴት እረኞች አንድ አፍቃሪ የወደዳትን ልጅ በነጻነት ማግኘት አለመቻሉን እና ቤተሰቦቿም ልጃቸው እንድታገባ አለመፈለጋቸው ሲያስበው በቃል ግጥም ብሶቱን ይገልጻል፡፡ እናም እንግዳ ስለማይወዱ በሽሽግ ፍቅርሽን ገልፀሽልኝ ልሄድ ሲል ይነግራታል፡፡

*ቃል ግጥም 250፡- እናትና አባትሽ አይወዱም እንግዳ*
*ሳሚኝና ልሂድ በሳንቃው ቀዳዳ፡፡*

እሷም ጥያቄውን ተቀብላ አንተ ምን አስጨነቀህ የቤተሰብ ቁጣም ሆነ ብትር እኔ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ የመጣውን ነገር ደግሞ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ እናም አትጨነቅ በማለት ምላሽ ትሰጠዋለች፡፡ ተፈቃሪዋ ለአፍቃሪው የሰጠችው ምላሽ አጥጋቢ ነው፡፡እኔ እመጣለሁ በሚል ስሜት ከአንተ የሚበልጥብኝ የለም ስትል የፍቅሯን መጠን ትገልጻለች፡፡

*ቃል ግጥም 251፡- ምን ያሸብርሃል ለቤተኛ ሰው*
*የመጣውን ዕዳ እኔ ልችለው፡፡* [21]

በፍቅር ውስጥ መስማማት እንዳለ ሁሉ መጋጨትም አለ፡፡ ይህ ድርጊት የገጠመው አፍቃሪ ቱሉ ጎራ በተባለ ቦታ ከብት በመጠበቅ ላይ ሳለ ግጥም ስለ ፍቅር መግጠም ያስደስተኛል በማለት እረኛው ለረዥም ጊዜ ተጣልታው የነበረች የሚወዳት የከንፈር ወዳጁ ከአሁን በኋላ ባትመጭ ይሻላል በሚል፡-

---

[20] መረጃ ሰጭ ፡- ተስማ ጣሰው (እድሜ 19)፣ መቀርጨሜያ ቀበሌ፣ እረኛ፣ ሚያዝያ13/2004 መቀርጨሚያ ሜዳ፡፡
[21] መረጃ ሰጭ ፡- ራሂማ አሊ (እድሜ 12)፣ ቱሉ አውልያ ቀበሌ፣ ተማሪና እረኛ፣ ሚያዝያ 10/2004፣ቱሉ ጎራ፡፡

*ቃል ግጥም 252፡- ታምሜ ታምሜ በጎ መሆኔ ነው*
*ከንግዲሁ መምጣት "ግርሻ" ለመሆን ነው፡፡*

በሚል ስሜት ፍቅሩን የገታው በይበቃኛል ድምዳሜ ነው፡፡ አፍቃሪው ከዚህ እንዲደርስ ያደረገው ውም ከአሁን በፊት ባጣው ፍቅር ውስጡ ስለተጎዳ ከብዙ ጊዜ በኋላ እየረሳት ሲመጣ ልትመጣ እንደፈለገች ስትገልፅለት ብዙ ተጎድቶ እየረሳሁሽ ነው እናም ከአሁን በኋላ በመምጣትሽ የውስጤን ቁስል በአዲስ መልክ መቀስቀስ ነው ሲል *"ከንግዲሁ መምጣት "ግርሻ" ለመሆን ነው"* በማለትይነግራታል፡፡

በሲጋምቦ ወረዳ በገጠርማው አካባቢ በርካታ ከብቶች ያላቸው ባለሀብቶች እረኛን ለከብት ጠባቂ ይቀጥራሉ፡፡ በአንድ ቤት ውስጥ የተቀጠረ ወጣት እረኛ ይላዳ በተባለ ቦታ መልካርያ በሚባ የከብት ማስማርያ ከብቶችን ሲጠብቅ በአጋጣሚ የተቀጠረበትን ቤት ጌታ ልጅ ይወዳል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ነገር ቀርቶብኝ አንችን ብቻ ይስጡኝ ደምወዝም አልፈልግ በማለት ፍቅሩን እንዲህ ሲል ይገልፅላታል፡-

*ቃል ግጥም 253፡- የበጎች እረኛ ችግ ይላል በጊዜ*
*አንችን ይስጡኝ እና ይቅርብኝ ደምወዜ፡፡*[22]

አፍቃሪው ራሱን ለእሷ ፍቅር አሳልፎ ሰጥቷታል፡፡ አላማና ግቡ እሳ ናት ፡፡ሰርቶ ለመለወጥ እረኛ ሆኖ የተቀጠረው አፍቃሪ ሃሳቡን አንስቶ ***"ይቅርብኝ ደምወዜ"*** በማለት የፍቅሩን ልክ ይገልጻል፡፡ በፍቅር ቃል ግጥም የተፈቃሪ ባህሪም ይፋ ወጥቶ ይነገራል፡፡ይህንን ሃሳብ በተመለከተ የቀረበ የቃል ግጥም እንደምሳሌ ብንወስድ፡-

*ቃል ግጥም 254፡- ፍየሊቱ አበባ በጊቱ አሰለፈች*
*ልቤን ወሰደችው እያስለፈለፈች፡፡*[23]

(የካቲት 10/2004፣ካሴት ቁጥር 3፣ ሀ)

ከዚህ ግጥም እንደምንረዳው አፍቃሪው ፍቅረኛውን በበግና በፍየል ሲመስል ይታያል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ሴት ልጅ በፍየል ስትመሰል ጥሩ ምላስ አላት እንደማለት ሲሆን በበግ ስትመሰል ደግሞ መልካምነትዋን ለመግለፅ እንደሆነ ወጣት ዳዊት ነገደ ቃለ መይቅ (የካቲት 19/2004) ይገልፃል፡፡ እናም የፍቅሩን ነገር በበግ እና በፍየል መስሎ ይናገራል፡፡

---

[22] መረጃ ሰጭ ፡- አሊ ይመር (እድሜ 45)፣ ይላዳ ቀበሌ፣ ገበሪና እረኛ፣የካቲት 19/2004፣ መልካርያ፡፡
[23] መረጃ ሰጭ ፡- ሙሃመድ አሰን (እድሜ 20)፣ ገነቴ ቀበሌ፣ ገበሪና እረኛ፣የካቲት 19/2004፣ መልካርያ፡፡

አፍቃሪው በፍየል እና በበግ በመሰላት ልጅ ፍቅር ተነድፎ እጅ ሰጥቷል። የተፈቃሪዋን ለፍላፊነት በአንድ በኩል በግነትዋን (ደግነትዋን) በሌላ በኩል አቁሞ እኔንም በፍቅሯ አስጮህችኝ ሲል በቃል ግጥሙ ሽንፈቱን የገለጸ ይመስላል። በአጠቃላይ የፍቅር መገለጫ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች ከተራ ቁጥር 248-300 በአባሪ ላይ ቀርበዋል።

በአጠቃላይ እረኞች ቃል ግጥሞቻቸውን ለመተቻ፣ ማንነትን ለመግለጫ፣ ወደፊት የሚሆነውን ለመንገርያ፣ ለማሞገሻ፣ ለመምከርያ፣ ለመሳደቢያና ለፍቅርን መግለጫ ብሎም ለመዝናኛነት ተግባር ይገለገሉባቸዋል።

## 6. ማጠቃለያና ይሁንታ

ይህ ጥናት በለጋምቦ ወረዳ የእረኞች ቃል ግጥም ክዋኔና ይዘት ላይ በገላጭ ተንታኝ የትንተና ስልትና በክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ መተንተኛነት ትንተና አካሂዷል። በትንተናውም የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥም አደራረስ፣ ክዋኔና ተስተላልፎ በመሸምደድ ወይም ለአውዱ እንዲስማማ አድርገው በቃል ግጥሞች ላይ የቃል፣ የሀረግና የስንኝ ለውጥ በማድረግ እንደገና ደርሰው እንደሚከውናቸውና እደሚሚያስተላልፏቸው ለማየት ተችሏል።

በሌላ መልኩ ደግሞ እረኞች በአካባቢ ከሚያዩት ነገር በመነሳት የቃል ግጥሞችን እንደ አዲስ እየፈጠሩ እንደሚከውኑና እደሚያስተላልፉ ጥናቱ ያሳያል። እረኞቹ በአዲስ መልክ የፈጠሯቸውን ቃል ግጥሞችም በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን በመከወን እንደሚያስተላልፏቸው በጥናቱ ተረጋግጧል።

የለጋምቦ ወረዳ እረኞች ቃል ግጥምን በእረኝነት ስፈራ፣ ቱሉ አውልያ በሚባል ጎራ ስር፣ ጊምባ ሜዳ፣ ጭሩሜዳ ፣ መቀርጨሜያ ጨፌ እንዲሁም መልካርያና በየአካባቢያቸው በሚገኙ የከብት ውሃ ማጠጫ ቦታዎችና በመኖርያ አካባቢያቸው ጠዋት፣ ቀንና ማታ ቃል ግጥሞችን እንደሚደረድሩ በጥናቱ ተረጋግጧል።

የለጋምቦ ወረዳ እረኞች አስተዳደራዊ ጉዳዮችን፣ የእኩልነት መብትን እና ስንፍናን የሚተቹ፤ የትመጣነታቸውን፣ የአለባበስ ባህላቸውን፣ ጀግንነታቸውና የራሣቸውን የጨዋታ ህግና ደንብ ማአክበርና ማስከበርን የሚያሳዩ ማንነት ገለጭ እና ወደ ፊት ይሆናል ብለው ስለሚያምኑት ማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚነገሩ ትንቢታዊ ይዘት ያላቸውን የቃል ግጥሞች ደርድረዋል።

በተጨማሪም እረኞቹ የስደትን ጉዳትና የማስተዋልን ጠቀሜታ የሚመክሩ ቃል ግጥሞችን፣ መልከ ጥፉነትንና ጸባይ የለሽነት የሚነግሩ ስድባዊ ይዘት ያለቸው፤ የአካባቢውን ማህበረሰብ ደግነት፣ የከብትና የእርሻ ምርት ጥሩነትና ጀግንነታቸውን የሚገያሞግሱና የፍቅር መግለጫ መልእክት አዘል የቃል ግጥሞችን እንደሚያቀነቅኑ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል።

ትንቢታዊ ይዘት ያላቸውን ቃል ግጥሞች በመደርደራቸው ማህበረሠቡ የእረኞች ትንቢት ተግባራዊ ይሆናል ብሎ በማመን የተለየ ክብር እንደሚሠጣቸው በጥናቱ ተረጋግጧል።

በአጠቃላይ እረኞች የሚያቀነቅኗቸው ቃል ግጥሞች በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የህይወት ፍልስፍና፣ አመለካከትና ፍላጎት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚጠቁሙ የአካባቢው መነጽሮች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

እነዚህ የእረኛ ቃል ግጥሞች የእረኞችንም ሆነ የማህበረሠቡን አመለካከትና የህይወት ፍልስፍና የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ትኩረት ሠጥተው ቃል ግጥሞቹ ከነክዋኔያቸው በስፋት ተሰንደው በአርካይብ የሚቀመጡበትን ሁኔታ ቢያመቻቹ የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ዋቢ መፃህፍት

ተክላይ ትዛዙ። "የአክሱምና አካባቢዋ እረኞች የሚሠሟቸው የዘፈን ግጥሞች"፣ የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1990።

ከሣቴ ብርሃን ተሠማ። *ያማርኛ መዝገበ ቃላት።* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፣ 1970።

ዘሪሁን አስፋው። *የሥነ-ፅሁፍ መሠረታውያን።* አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1992።

የለጋምቦ ወረዳ አጭር ቅኝት። "የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን መፅሄት"፣ ጥር 2002 ዓ.ም።

የለጋምቦ ወረዳ የባህልና ቱሪዝም። "አመታዊ የሥራ ሪፖርት"፣ 2003።

ደስታ ተክለወልድ። *ዓዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት።* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1970።

ፈቃደ አዘዘ። "አፋዊ ኪነተ ቃል" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ መፅሔት፣ ቁጥር 2 አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1984።

________።*የስነ ቃል መምሪያ።* አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ ቤት፣ 1993።

Bauman, Richard. "Verbal Art as performance". Waveland: University press, 1977.

______________.*The Field Study of Folklore in Context.* A hand book of American Folklore. ED Richard M. Dorsen, 1983.

______________. *Story, Performance and Event.* Cambridge University Press, 1986.

Ben-Amos, Dan. *Folklore in Context.* South Asian Publishers, New Delhi Madres,1982.

__________. *" Context " in Context.* Western Folklore Vol 52, No.2/4, Theorizing Folklore; Towards New perspective on the politics of culture.1993.

Fekade Azeze. *Unheard Voices*: Drought, Famine and God in Ethiopian Oral Poetry. AAU Press, 1998.

Finnegan, Ruth. *Oral Literature in Africa.* Nairobi: Oxford University Press, 1970.

__________. *Oral Poetry its Nature, Significance and Social Context.* Cambridge: Cambridge University Press, 1977.

__________. *Oral Tradition and the Verbal arts.* A Guide to research practices. London and Now York, 1992.

Goldstin, K.S. *A Guide for Field Works in Folklore.* Pennsylvania Hatbord, Folklore Association inc, 1964.

George, Robert A. and Michael Own Jones. *Folkloristic; An Introduction.* Bloomington, Indian University press, 1995.

Getie, Gelaye. "Peasants and The Ethiopian Agricultural Producers" Cooperative and Their Reflections in Amharic Oral Poetry-A Case Study in YetNora, East Gojjam." 1975-1991 Volume 7, Hamburg Lit Verlag Munster 2000.

Vansian, Jan. *Oral Tradition as History.* University of Wisconsin press. 1985.

Mac, Donald. *A Field work Collection of Oral Literature* in Richard Dorson (Compiled by Fekade Azeze, 2003).

Mac Henery. Robert, Ed. *The New Encyclopedia.* 15th ed. Vol. 9. USA; The university of Chicago, 1993.

Martha C. Sims Martine Stephens. *Living Folklore. an introduction to the study of People and Their Ttraditions.* Utah State University Press, 2005.

Miruka, Okumbo. *Encounter with Oral Literature.* Nairobi; East Africa Educational Publishers Ltd, 1994.

Okpewho, Isodar. *African Oral Literature: Backgrounds, Characters and Continuity.* Bloomington; Indiana University press, 1992.

Richard, M.Dorson. *Folklore and Folklife: An Introduction.* Chicago and London: Press 1972.

# አባሪ አንድ፦ የግጥም ስብስብ

## ትችታዊ የቃል ግጥሞች

1- አዱኒያ ታልቅና ስትመር እንደሬት
ትንሹም ትልቁም ይላል መሬት መሬት
ሁለት ንጉሥ ሄዶ ሶስተኛው ሲመጣ
ከመሬት ላይ ያለው ምነው በጉድ ወጣ።

2- በመተማ በኩል ይፈልቃል ወጠጤ
ትባላለች ንጉሥ ትመስላለች አጤ
መሬቱን ከፈለች አርጋ ስንዝር ከጋት
ይህስ የሚመስለው ለጓሚው ሹም መግባት።

3- ጥንት ነበረ እንጂ በኃይለ ስላሴ በሉሉ በዘውዱ
ሰፋ ከፍ ማለት ለቀቅ ከመንገዱ።

4 -ደሞ ተመረጡ ደሞ ተመረጡ የእኩል መብት አሉ
የወንዱንም ሱሪ ለበሰችው ሴት ታጠቀችው ሴት
ኮቱንም ለበሰች አልጋውንም ያዘች
አደባባይ ውላ እቤትዋ ስትመጣ ባልዋ ገለመጠች
ልቀቂኝ ያላት ለት የኩል መብት አለች
የእኩል መብት ሰጥቶ የለቀቃት ለታ
ሹመቱንም ያዝኩት መሬቱንም ያዝኩት
እያለች እንዲያው ስትብቃቃ ሰኮራ ሰኮራ
ድንገት ጉፍ አለባት ኤድስ አባወራ።

5- የሴት አባወራ በመጣ ባዋጂ
ፈረደውን ባያውቁት ነው እንጂ
ባል የለ ሚስት የለ ሁሉ ጋለሞታ
ትዳር የሚገኘው በየትኛው ቦታ።

ABABA UNIVERSITY
S LIBRARY

6- ሎሚ ኮለል ኮለል የልጆች ጨዋታ

ኮሚቴ ነን ባዮች ጠዋት የተናገሩት አይገኝ ለማታ

ያም መጣ ያም መጣ ሁሉም ለራሱ ነው

ስታውሱን እንኳ ለኛ የሚደርሰን ያው ትራፊያቸው ነው።

7- አዱኒያ ታልቅ እና ስዞር ወደ ጎሮ

ትንሹም ትልቁም በመሬት አንቃሮ

ቁጠባ እያመጣ ይሰራል ቆርቆሮ።

8 -ጥንት በአዬዎቹ ተነጥሮ ተበልቶ

በኃይለ ስላሴ ቂቤ ወተት ቢሉ ከወዬር ተገኝቶ።

9. ሰው እኩል ነው ያልሽው

ሰው እንዴት እኩል ነው

ዋንጫ እና ብርሌ ስራው እየቅል ነው

እያሌቱ መንግስት የውጡት ከሰው ነው።

10 -በኃይለ ስላሴ ደህና ተወልጆ

ደርግማ ሲመጣ ታነኩ ከደጆ።

11. ሹመት ያገኛል ብለው ይሉኛል

መሬት እርስቱን እሱ ነጥቆኛል።

12. እባካችሁ ሰወች ዱለት ስዶልቱ ነግበኒ ብላችሁ

በራስ የሚስፈርድ ነገር መጣላችሁ።

13. ያላወቀም ያርሳል ያወቀም ያለቅሳል

መሬቱን ተነጥቆ ሕልቁ ይታመሳል

አብጆው ነው እንጂ ወዬት ይደረሳል።

14. አዱኒያ ታልቅ እና ስትል ፈንደል ፈንደል

አንድ ላይ ይቀራል ቁርአን እና ፊደል።

15. አዱኒያ ታልቅ እና ስቀጥን እንደ ድር

ካህናቱ ሁሉ ይላል ምድር ምድር።

16. ስደድ ስደድ ብለሽ የሰደድሽው አልጋ

የማያስኮረትም የማያዘረጋ።

17. በርሃ ማዶ ሆኖ ቢነፋ ዋሽንት

አንድ ላይ ደለቀች ያበሻሴት

አይደለም ሌላ እንኮ እያለች መብት(2)

18- እኔን የቸገረኝ የሸዋ መሬት

ከአስር ሴት እመቤት አንድ ሴት ማጣት።

19. የእረኛ ደንቆሮ

ግልገልዋን ሰጠች ለቀበሮ።

20. ደገኛ ሞኝ ነው ይማታል በድግር

ትተሸው ነይ እና ቅጣውን ይጋግር።

21. በሀይለስላሴ ወልጀ ወልጀ

በደርግማ ጊዜ ዋልጀ ዋልጀ።

22. የዘንድሮ ሰወ የለውም እቃ

ባነጋግረው ሰውም አልነቃ።

23. አቤት አቤት ማለት እመንግስት ደጃፍ

ለመንግስት ነዌ

መንግስተ እሌለበት ሌባ ሊገለኝ ነው።

24. አገሬ ታምሃል አልሆነከም ወይ በጎ

እዛው እደጃፍህ ተውጣልህ ሸንጎ

መሬትህን ነጥቆ አፍህን ሸብቦ

አስመሳይ አስመሳይ መስሎ ሆድ ብቦ።

25. ያያ ሽማግሌ ውሃ ነው ቀለቡ

እኔ በሰው ገንዘብ አይኔ መቅለብለቡ።

26. አዱኒያ ታልቅ እና ስትቀጥን እንደ ድር
ትንሹም ትልቁም ይላል ምድር ምድር
የዛን ጊዜ የለም ተኝቶ የሚያድር።

27. ስትገባ ይግባ ስትወጣ ይውጣ

ሹመትን እንዴያገኝ ሹም ሽሩ ሲመጣ።

28. እጎራው ላይ ሆኘ ፋጨቴን ብለቀው

መብቴ ነው ብላ መጣች ከነ ሊጥዋ ሳትለቃለቀው።

29.በሮቻችን ሞተው ፈርጠው እንደ እንባይ

አሁን ብንታረቅ እርቅ ይሆናል ወይ።

30. ሎሚ ኮል ኮል የልጆች ጨዋታ

ጠዋት የተናገሩት አይገኝ ቆይታ።

31.አውላቸው ንጉስ አውላቸው አጼ

አገሩ ይገዛል በአንዳንድ ወጠጢ።

32-ወንድም ሊቀመንበር የተሸመላችሁ

ካማች ፍርድ ሸንጎ ጋብቻ ያላችሁ

ማሣውን እረሡት በሠፌው ይዛችሁ

እኔም ዘንግቸ ነው ሳላውቅ ቀርቼ

የሊቀመንበሩ አማች መሆን ትቸ።

33. በሮቹ ተጠምደው የታለማረሻው

ድፍንፍን ያለ ቀን እስከ መጨረሻው።

34. አትውረድ ቢሉት ወርዶ በያድ

አቆላለፈው እንደ በግ ቀንድ።

35. እንደ ጎበዞች አረፍያ ወርዶና

እምየ ያል ጀመር እዳር ቀመና።

36. የፈሪ እናቱ አትጨነቂ

ልጅሽ ቁራ ነው ነፍሱን ጠባቂ።

37. ፈሪ ለነቱ ያገለገላል

ምጣዱን ሥትይዝ ሞህድ ያቀብላል።

38.ያን ማዶ ጎራ ቢንዱት ምን ይላል

ፈሪ ቁጠማ ነው ይሸሸግበታል

የጊንባን ሜዳ ማን ይዘልቀዋል

ፊሪ ሰንጋ ነው ይጨልጠዋል።

39- ለሲቀመንበሩ አጎርሰው አጥቼ

ለሄድነው በስደት ካገሬ ወጥቼ።

40-ከኮሚቴዎቹ እጅ አልሠጥም ብዬ

እርስቴን አጣሁኝ ቀረሁ ተነቅዬ።

41-መሬት ታወረ አሉ አይኑ ተሰወረ
አሁን አሁንማ በሊቀመንበሩ ይመራ ጀመረ።

42 በሮቹ ተጠምደው ዘሩ ተቆጥሮ

ልትሰድበኝ ነው ወይ እንዳመናው ዘንድሮ።

## ማንነትን የሚገልፁ የቃል ግጥሞች

43 - ጊንባ ያደገው አባ ቦሌ አገር

ውሽቴን እንደሁ ይችት ኩራቴ ለምዴ ትናገር

በጎቼን ሳግድ ለምዴን ለብሼ

በከርጭቴ ቆለየን ይገባ።

44- እስኪ ላንጎራጉር በጎቼን አግጄ

ለምዴን አጥልቂያለሁ በሁለቱም እጄ

ከላይኛው ጌታ በተሰጠኝ ፀጋ

ሁሉን እነግራለሁ ትንሽ ሳልዘነጋ።

45- ምንሽሬን ይገባ ልበል ዘወር ዘወር

ትንሽ ይበቃል እሳትና ነገር

አልጠናም እንጂ ክንዴ ቢጠና

ይበታትናል እንደ አውሮፕና

ዘሬ ከጥንትም መብረቅ ነውና።

46 - ሁለት አፊ ለምለም ሶስት አፊ ከፍታ

ከኛ ይጫወታል እኛን የመሰለ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
I.E.S LIBRARY

ሚስጥርን ሲነግሩት ሲያስሩት ያልተፈታ፡፡

47 - ገና በይ ገና በይ ገና ለወደፊቱ
እሳት ይነዳል ከፊት ለፊቱ
አያት ብትሬ ታስታውቃለች
እንደ አዘንተኛ ፊትዋን ነጭታለች
ጠላትዋን እማ ታስራዋለች፡፡

48 -ያባቴን መሬት ማነው ያረሰው
በትላም ዱላ ደም ሳላለብሰው
አያቀኝ እንደሁ ይስማ ንገሩት
የጀግና ዘር ነኝ የነ ተራሩት፡፡

49- ሁለት አፈ ለምለም ሃምሌ እና ነሃሴ
ሶስት አፈ ከፍታ የሹሞች ሱሪ ነው
ይህንን ከፈታሁ ብጫወትሽ ምነው፡፡

50- ቀጭቀጭ እንደ በሮዶ
በልጆ እነቱ በርሃ ለምዶ፡፡

51- ሀይ ዘራፍየ ዘራፍ ተፈሪ
በረገርም በረት ቅልጥም ሰባሪ፡፡

52- ዘራፍ ተነስቶ ዘራፍ ሲታጠቅ
ልቡ አይሸበር ቀልቡ አይደነግጥ፡፡

53- አይመጡም እንጂ የመጡ እንደሆን
ሳይደነግጡ ከልብ መሆን፡፡

54- የቅርጫት ስጋ ዝንብ የወረረው
እንቢ አለ ልቤ ክልብሽ እያለ፡፡

55- ደጋ ለደጋ ይዘራል ገብስ
አፈር አልብሸው አፈር ልልበስ፡፡

55-ለከርሞም ና በለው ለዛሬም ና በለው

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

እስ ምን ጊዜም ድሉ የኛ ነው፡፡

56-ወንዜንስ ማን ደፍሮት

ሚዳየን ማን ደፍሮት

የያዝኩት ጀራፍ ሳተረሆን ብላሽ፡፡

57-የኛማ ልጆች ቀጫጭኖቹ

ይናደፋሉ እንደ ንቦቹ፡፡

58- በጥቁር ጭራ ብለምጠው

አሬራው ወጣ የቀላወጠው፡፡

59- ደሞ ለጭራ ለሚበነው

በራር ጥይት ተሙቶ ይድናል ሰው፡፡

60- እንበለህ እና እሆነ ድረስ

ያገኘም ያግኝ ያጣም ይመለስ፡፡

61- እንበለውና ጉልበት ጉልበቱን

እያነከሰ ይውጣው ዳግቱን፡፡

62- እንበለውና በበዳ ሰፊ

እንደ ወለደች እናቱ ትለፍ፡፡

63. ገና በይ ገና በይ ገና ለወደፊቱ

እሳት ይነዳል ከፊት ከፊቱ

ከየት ነህ ብሎ ቢጠይቀው

እኔ ነኝ አለ ከተራራው፡፡

64- ይንጡ ይጠራቀሙ

ለሁላችንም እንደ ጠቀሙ፡፡

65- እህል ሳይበላ ውሃ ሳይጠጣ

ሌሊት ተጉዞ ገሎ የሚመጣ

ከምድር ደባልቆ ከዛፍ ሲወጣ

መብረቅ ይመስላል ከላይ የመጣ፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

66-. ሁለት አፈ ለምለም ሶስት አፈ ከፍታ

ሃምሌ እና ነሃሴ

ከኛ ይጫወታል ይህንን የፈታ።

67- ትስጠኝ እንደሁ ስጠኝ ጠመንጃ

አልቀበልም ኮሳሳ ጥጃ።

68- በኔ ቤት በላይ በዋጀለቱ

ባንተ ቤት በላይ በዋጀለቱ

አዙሮ እሚጥል በጭንቅላቱ

እሽመርሃባ እስኪል መሬቱ።

69- በዚያ ሻሻታ በዚያ ቁልቁለት

በአንድ እጅ ብትር በአንድ ቁርቂት።

70-. አንድ ነው ብለው ናቅ አርገውታል

እንዲህም ሲሉ ያስፈሉጉታል።

71- ከወዲያ ወዲያ ቢያወደውዱ

ኑርየ ምን አሻው ባርንዛ ሆዱ

የተራራ ዘር አይቀመስም

ኑርየም ያው ነው አይቀመስም።

72 - እያት ብትርይ ታስታውቃለች

እንዳዘንተኛ ፌትዋን ነጭታለች።

73. ሃይ ገና ሃይ ገና

አካኪ ዘራፍ ልበ ወንበዴ

እሱ የሚመኝው ሰው በጎራዴ።

74- አምናም አርግኸ ነው ዘንድሮም ወልጄ

ቆይ አሳይሃለሁ ይደግማ ልጅ ።

75- የጋሸየ ልጅ የባላባቱ

የየሽዩ ልጅ የወይዘሮይቱ

ጥይት ፈልቃቄ በአምስት ጣቱ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አባቱ ነበር ማሽላ ዘሪ

ልጅ ደረሰ ጥይት መንዛሪ።

76- ደጋ ለደጋ ይዘራል ገብስ

አፈር አልበሸው አፈር ልልበስ።

77-ጀግናው ከበደ አሊ አለ ከሃላየ

ጀግናው ሰይድ አሊ አለ ከሃላየ

ማን ይነካኝ ብሎ ይፈራል ገላየ።

78. እንበላቸው ባይ እንደብድባቸው

አገሩ የኛ ቤቱ የሳቸው።

79. ውርድ እንውረድ ተባባሉ እና

አስደበደበው ከዳር ቆመና።

80- አጣድፎ ገዳይ እንደ መጋኛ

ብትሩ ከፋ ክንዱ ሀይለኛ

መከራ ሰርጉ የጦር አርበኛ።

81- -እጥፍጥፍ እንደመጫኛ

ካባቱ በቀር የለውም ዳኛ

አሴ አንድነቱ አስታጥቆኝ እና እንብርቴ ድረስ

አናት አናቱን ብዬው ልመለስ።

82- ሲያዩት ይመስላል ላይን ኮሳሳ
ሲቆጣ ነብር ሲገል አንበሳ
ጠላት አጥቅቶ እጅ የሚያስነሳ
የተነፈሰው በቃይ ነው ገሳ።

83- አርሳሱ ጥቁር በረዶ ነጭ

አፈሰሰበት እንደ ቁጫጭ።

84- ጥንት ልምድ ያለው ካያት ከአባቱ
አይወላውልም ሃይሌ አንድነቱ።

85- የለጋምቦ ልጆች ምን ቢቀጣጥኑ

ደፋር ነው ልባቸው ማንንም አይፈሩ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

86- ንርየ ጋሻው የአንበሣው ጋማ

በዱር አፈና ነብስ የሚቀማ

ምቀኞች በዝተው ቢነጋገሩ

ኑርየ አይሠንፍም ለውድ ሃገሩ።

87- ድብ ዱብ ባይ እንደ በረዶ

በልጅነቱ በረሃ ለምዶ

የሚቅበጠበጥ እንደ ቀን ዘንዶ።

88- እጥፍ እጥፍጥፍ እንደኩታ ልብስ

አስተራረሱ አንጀት የሚያርስ።

89- የሰማይ ኮከብ ሆኖ ጠላቱ

አይሠጋላትም ትንሽ ለሞቱ።

90- ሽሜማ ሽሜ የልጅ ወጉ ነው

ክንዴ እንኳ ሳይጠና በደል ምንድነው።

## ትንቢታዊ የቃል ግጥሞች

91- አህያ መጣች ተጭና ሻሽ

ኃይለ ስላሴ አጥብቀህ ሽሽ።

92-አህያ መጣች ተጭና ኳሳ

እንግዲህ ደርጉ ኳዝህን አንሳ።

93-አህያ መጣች ተጭና ለምድ

አንድ ትልም አርሶ ሁለት ጉድጓድ።

94-አህያ መጣች ተጭና ቅጠል

ቆርቆሮ ሰርቶ በርሀብ መቃጠል።

95-አህያ መጣች ተጭና ገንቦ

በልግ ረከሰ ወደለጋንቦ።

96- አህያ መጣች ተጭና ለበቅ

በርበሬ ጠፋታል ሳማህን ስበቅ።

97 -አህያ መጣች ተጭና ሞሰብ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

እህል ይረክሳል ለጤነህ እሰብ፡፡

98-አህያ መጣች ተጭና ጋን

የዘመኑን ሰው አለማመን፡፡

99-አህያ መጣች ተጭና ዱላ

አይመለስም ጊንባ ለዱላ፡፡

100-አህያ መጣች ተጭና ካራ

ትንሽ ትልቁ ቆርቆሮ ሰራ፡፡

101- አህያ መጣች ተጭና ገሳ

የባላባት ልጅ ወድቆ ተነሳ፡፡

102-አህያ መጣች እንጢጥ እያለች

የዘንድሮ ሴት እንቁላል ጣለች፡፡

103-አህያ መጣች ተጭና በሬ

አልሰማህም ወይ የርዳታ ወሬ፡፡

104-አህያ መጣች ተጭና ቀንበር

ከእንግዲህ ወዲያ ችግር ይቀበር፡፡

105-አህያ መጣች ተጭና ቀለም

የሚመጣውን የሚያውቀው የለም፡፡

106-አህያ መጣች ተጭና ወንፊት

ጥሩ ቀን መጣ አሁን ወደፊት፡፡

107- አህያ መጣች ተጭና ሞፈር

ቅቤ እንደጭቃ እህል እንዳፈር፡፡

108- አህያ መጣች ተጭና ላዳ

ችግር ይወርዳል ወደ ይላዳ፡፡

109- አህያ መጣች ተጭና ሜዳ

ችግር ይወርዳል ወደ ገራዶ፡፡

110-አህያ መጣች ተጭና ጣሳ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ወደ ልማቱ እንነሳሳ፡፡

111- አህያ መጣች ተጭና ጫማ

ሰማይ መሬቱ ሆነ ጨለማ፡፡

112-አህያ መጣች ተጭና ሳማ

ህግ እና ደንቡ በምን ተስማማ፡፡

113-አህያ መጣች ተጭና ቅማል

የዘንድሮ ቀን ጫት ያቃቅማል፡፡

114-አህያ መጣች ተጭና ጎታ

ያላሰ ሰው ሄደ ቡአገታ፡፡

115-አህያ መጣች ተጭና ለበቅ

በርበሬ የለም ሳማህን ስበቅ፡፡

116 -አህያ መጣች ተጭና ግልድም

መሬት የሸጠ እንዴት ይለድም፡፡

117-አህያ መጣች ተጭና ግልድም

በልግ ያልዘራ ሰው እንዴት ይለድም፡፡

118-አህያ መጣች ተጭና ቁልቁል

ጎይለ ስላሴ እዛታች ወድቁል

እንዳላነሳው አንጀቴ በሰሽቁል፡፡

119-አህያ መጣች ተጭና ዶሮ

ሃብታም ያገኛል የድሃ ኑሮ፡፡

120- አህያ መጣች ተጭና ዶማ

እየነገርነው ሰውም አልሰማ፡፡

121-አህያ መጣች ተጭና ላም

ከእንግዲህ ወዲያ ያለች አለም፡፡

122-. ገብስ እና ባቄላ ገብቶ ከሰው ጉያ

የዛሬ ዘመን ሰው ይላል ጉያ ጉያ፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

123-አህያ መጣች ተጭና ላዳ

ሰኞ ገበያ ፈረነረጅ ገባ።

124-አህያ መጣች ተጭና ጥፍጥፍ

ሴትአልተገኘም ቂጣህን ጠፍጥፍ።

125-አህያ መጣች ተጭና ጫት

ተማሪው ሁላ ሆነ እመጫት።

126- አህያ መጣች ተጭና ፎሌ

አድበህ ተኛ ባለ ብርሌ።

127- አህያ መጣች ተጭና ሞፈር

ከእንግዲህ ቀረ ትልቅ ሰው ማፈር።

128-አህያ መጣች ተጭና አልንጋ

ጨልሞ ነበር መልሶ ነጋ።

129-አህያ መጣች ተጭና እንስራ

ደርግ ሄደ አሉ አንድ ሳይሰራ።

130-አህያ መጣች ተጭና ድስት

አልተጣጣመም ዘር ከመሬት።

131- ጊዜ ለስተው ለዘገየ

የጊንባን ሜዳን ጢፍ ያየ።

132-አህያ መጣች ተጭና ሻኛ

መዳኒት የለውም ኤድስ እና ጉያ።

133 አህያ መጣች ተጭና ላም

ቱሉ አውልያ ላይ ያለች አለም።

134.አህያ መጣች ተጭና ቁልቁል

ራስ ግብረሂውት እዚያታች ወድቁአል

እንዳላነሳው አንጀቴ በሽቁአል።

135.-አህያ መጣች ተጭና ኮሶ

ጠጅ ሞተ አሉ እንሂድ ለቅሶ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

እናት አባቴን በዳ ለውሶ።

136-አህያ መጣች ተጭና ምስር
ባንዳ እረከሰ በየድንጋው ስር።

137- .እትየ ጣይቱ በሞተች በርጉዙዋ
ለድፍን ሃብሻ ይነዛ መርዙ።

138- ቤትዋን አስረታ እከተማው ስር
እባክህ ጠብቃት ስሚውል በሴር።

139-.እድሜ ለስጠው ለዘገየ
ቱሉ አውልያ እና ጊንባን ያየ።

140- እንዲህ በስተሰሜን በትግራይ መሬት
ድንገት ይመጣሉ ታህት የሚሉት
የሚይዙት እንኳ አጫጭር ብረት።

141-.ቱሉ አውልያ ላይ ያለች አለም
ይንድ ቀን እንኳ አይደለች የዘላለም።

142-. ቱሉ አውልያ ላይ የሚሰራው ቤት
ከቁመቱ መርዘም የወርዱ መስፋት
አይገኝም እንጂ የሚገባበት።

## ምክር ለጋሽ የቃል ግጥሞች

143 - ማረስ ነው እንጂ ገልበጥበጥ እርጎ እዲቡ ድረስ
የመጣ እንግዳ በልቶ ጠጥቶ ጠግቦ እንዲመለስ።

144- እርሻ ነው ማረስ "ዲብ"አዘልሎ
ቀይ ሴት አይቶ አይሆንም ኑሮ።

145 - ፍየል ቅጠል እንጂ አይበላም ገለባ
ምንድነው ስደቱ ወደ አዲስ አበባ
በራስ ሀገር ሰርቶ መሆን ነው ደርባባ።

146 - ያያ ሽማግሌ ውሃ ነው ቀለቡ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ምነው ባረብ አገር አይኖችህ አይኖችሽ ባይቅለበለቡ።

147-ድህነት እብድ አይደል ዘሎ አይጨመድድ

ግን ስነፍ ካገኘ ካሰረም አይሰድ።

148- አረ ምን ቢሆን ነው አረ መርዙ

እሱ ያመጣውን እሱ እስኪመልሰው

ምነው ባገሩ ላይ በቆማጣ ፈረስ አርሶ አይበላም ወይ ሰው።

149-ተይ በኋት ያችን ሳም ከስደቱ ላይ

ተው በሉን ያን በሬ ከስደቱ ላይ

ተው በሉን ያን በሬ ከገደሉ ላይ

እሱ ሳሩን እንጂ አሳሩን አያይ።

150 ከማንም ከማን ያው ዘመድ ይሻላል

ባዳ ና ወረርሽኝ ቀን አይቶ ይጥላል።

151- ወንድም የሌለው ሰው የለው አባሪ

እክንዱ ላይ ይቀራል የዱላ ስባሪ።

152-እናት እናት አልውት ስሙአን አሳንሰው

ሰማይ እና ምድር የምታክልው ሰው።

153- እማ እምየ እማ እናቴ

የለች አይሆንም ሂወቴ።

154-. የሽንኮራ አገዳ የለውም አበባ

እየወለዱ አዲስ አበባ።

155-. የፍየል አሮጊት አትሂድም በጫማ

ሂጅ ብሎ ሰዶ በሃላ ለዳማ።

156- ነይ እሪያ ፍሌ ነብር ይብላሻል

አሁን ላንች ብሎ ማን ይመጣልሻል።

157- ፍየል በተረተር ይመስላል ሰርገኛ

አስታራቂም የለን እንታረቅ እኛ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

158 - ቤታችን ተቃጥሎ አስተኝቶት ባመድ

አሁን ብንታረቅ ልንሆን ወይ ዘመድ።

159- ጠፍጣፋ ድንጋይ መቀመጫ ነው

ወገን የሌለው ማላገጫነው።

160- ተው በሉት ያንን ሰው ከገደሉ ላይ

እሱ ሳሩን እንጅ አሳሩን አያይ።

162-. እኔስ መች ተወለድኩ

እናቴስ መች ወለደችኝ

እጠላቶች ጋር አብሬ አየዶለትኩ።

163- .ደኑ የደኑ በሬ
የሚሽቆጠቁጥ እንዳ ደመኔ።
165- አምልጡልኝ በሮቼን አርጀ ልብላቸው

አምልጡልኝ ላሞቼን አርጀ ልብላቸው

ሳይደክም ጉልበቴ ሌባ ሳይነዳቸው።

167- ተው በለው ተው በለው ተው በለው ይሞታል

ጀግናው ሲወረወር አገዳ መስሎታል።

168-ተው አንተሠው ተው ተመክር
እርሻህን እረስ እሱ ነው ደም ስር።

## ሥድባዊ የቃል ግጥሞች

169- አራ ጎራው አረ መርዙ

አራ ጎራው አረ መርዙ

ወንድ ልጅ ተወልከዶ ካልተባለ አጅሬ

ከዳገት አቃኑት ሳር ይብላ እንደ በሬ፡

170-የቀስታ መኪና ማረፊያው ደሴ ነው

የፀጉርሽ ቆሻሻ አይኔን ሊያጠፋው ነው።

171- የፍቅርን ነገር ከቶ የት አወቅሽው

ከምጣዱ ቂጣ አይንህን ተክለሽው

ጎረምሳው ወዳጄ ውቃቢ የሸሸው

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ቂጣውን ጨረሰው ተልባውን አስካሸው
ዘጠኝ ቂጣ በልቶ አንድ ሲቀረው
አይ ጤና ማጣት ብሎ አስቀመጠው፡፡

17 - ከበጎቹ ሁሉ ሆሊት ትበልጣለች
ከንፈርዋን ከሳምዋት ሴት ልጅ ትቀብጣለች፡፡

173 - ያህል ልጅ ፈሳም የጅብ ልጅ ደንደሳም
ሴትን ለስራ እንጂ ማን አለ ለዙፋን፡፡

174- በፊት ነበር እንጂ እኔ የምወድሽ
ያቅማዳ ማሰርያ ሳይመስሉ ጡቶችሽ፡፡

175 - አምጃ ለምጃ ይገፋል ውተት
ከቁምትህ ማጠር የመልክህ መክፋት፡፡

176 -እንደ ጆሮ ትልቅ እንደ አይን ትንሽ
አሁን አንችን ነው ወይ ቆንጆ ነሽ ያሉሽ፡፡

177-ሰውየው ዙጣ ሞፎሩ ዙጣ
ያንእያረሰ ይቆምጣል ቂጣ፡፡

178 - እወድሽ ነበረ አሁን ጠላሁሽ
እንደሰፌድ ቆሎ ሁሉም ዘገነሽ፡፡

179- እንደሰፌድ ሁሉ ቢዘግነኝ
ተወደድኩኝ እንጂ መች ተጠላሁኝ፡፡

180-. የበጎች እረኛ ችግ ይላል በግዜ
ማርያ ይታጠቃል ያ ቡልሃ ፈንዜ፡፡

181-ባላገር ሞኝ ነው ይማታል በኮሎ
የበጎቹን ጅለት አይኑን ተኮኩሎ፡፡

185- እርስዋን አግድም ቅማል አረሰው
ጉፍጉፍ አለ የጊንባ ሰው፡፡

186- ፀጉሩ ልማልሞ ነው የሴቲት አንበሣ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አይረባም ወንድ ልጅ በደሉን ከረሣ::

187-መቸም አይቀር ብሎ ሞትና ኩነኔ

ያረጅም ቀውላላ ተጫወተ በኔ::

188-አገልግል ሰፍቼ መለጎሚያው ጭራ

ጉድ አይቼ መጣሁ አጭር ሰው ሲኮራ::

189- ከሴት ወንድ ይሻላል ብዬ ባገባው

እሱ ያመረተው አንድ ቁና ነው::

190- አሮጊት አግብቸ ጎኗ የደቀቀ

ሳንጓጓት አድራለሁ ቆዳ እንደሰረቀ::

191-ማሽላ ጠባቂ ይውላል ከማማ

ያገባሽ ይሆናል ጉድሽን ያልሰማ::

192- አረጀሽ መሰለኝ ውቃቢ ራቀሽ

አንች ከእህል በቀር ሰው አይናፍቅሽ::

194- እቴ አንቺ ጉደኛ የጉድ አውድማ ነሽ

አስወቀጥሽኝ እንጂ እስከኔው ጨምረሽ::

195- የሁሉ ነሽ አሉ የሰደቃ እህል

እኛም እንቅመስሽ የሰው ያህል::

197- እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ምንድነው ፉክክር

እንዲህ አውድማው ላይ ምረቱ ሲመሰክር::

198-ያንችማ ወዳጅ ጎፈሬው ሽሽ

ሲሽሽ አየነው ጎሽ ለጎሽ::

199-ያም ለኔ ያም ለኔ ያምለኔ ይልሻል

ያረንዛው የሰዳ አንቺ አምሮብሻል::

200-ለሴ;: ለይምሰል ደብድበው ቢሮጡ

ያዳልጥ የለም ወይ ሳሩ ሰንበሌጡ::

204- ያማዶ ጎራ ይብለጨለጫል

የዚያ አገር ውሪ ቅዘን ይረጫል::

ADDIS ABABA

205- የዛ አገር ልጆች ወዳድሎቹ

አር ይገምጣሉ እንደ አህዮቹ።

206-አምና የቡሄ እለት የበላው በርበሬ

እቂጡ ላይ በቅሎ የለቀማል ዛሬ።

207-አምና የቡሄ እለት የበላው ስናፍጭ

አላስሮጠው አለ እያለ ፍጭፍጭ።

208- ወንድ መሳይ ጎፍሬዋሽ

ሲሸሽ አየነው ጌሽ ለጌሽ።

209- ወንድ መሳይ ጎፈነው እንቅብ

ስሸሽ አየነው ቅብቅብ ለቅብቅብ።

210 -ያ ማዶ ጎራ ይብለጨለጫል

የዚያ ሃገር ውሪ ቅዘን ይረጫል።

211- የዚያ ሀገር ልጆች ወዳድሎቹ

አርይገጥሉ እንደ አህዮቹ

212- እሩጠህ እሩጠህ በማጠህው ቆሎ

እሩጠህ እሩጠህ በማጠህው ጣጣ

ወዴት ትሸሻለህ አንታራም ቆማጣ።

## ማሞገሻ የቃል ግጥሞች

213- ዘራፍ ዘራፍ

እጥፍጥፍ ጉጥፍጥፍ እንደ ኩታ ልብስ

አስተራረሴ አንጀት የሚያርስ።

214- ቀጭ ቀጭ እንደ በቆሎ ዕቃ

የተናገረው አንዱ የሚበቃ

እሱ ነው ዓሉ የወደፊቱ ያገር አለቃ።

215- ጊንባ ደጉ ወሎ ደጉ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARY

ድርቅ እንካ ቢመጣ

ወላጅ አልባ ልጆች ያላባት አደጉ።

216- አቆልቁለው ሲያዩት ፈርስና በጉ

ቀና ብለው ሲያዩት መህርና በልጉ።

217- የበጎች እረኛ ችግ ይላል በጊዜ

የሚያረገርገው ወገብታ እንደመንዜ።

218- ጊንባ ደጉ ወሎ ደጉ

መህሩ ሲበላ የሚደርሰው በልጉ

ወዲን በልጉ ወዲህ በጉ።

219 - ጊንባ ወሎ ያገር አለቃ

ፍየሉ በጉ ታርዶ አያበቃ።

220 - ጊንባ ሜዳ ወጥታ ትግጣለች በግ

ሽንጥዋ የሚመስለው የተማሪ ዘንግ።

221 -ጉችጉች ያለነው ጡቱ እንደ ፓፓየ

ስጠብቅ አደርኩኝ ይፈነዳል ብየ።

222-.እመጫኛው ሃገር ወሎ ተወልጀ

በነጋ በመሸ ይታሰራል እጀ።

223. የበጎች እረኛ ይላል ትሪትሪ

ወገብዋ ይመስላል ያልጋ ትርታሪ።

224- .በደርጉ ይጠታል እርጎው

ይበላል ስጋው

በድርጉ ደርጉ እናት አባቴ ደርጉ።

225 .ቆላ ተኩሶ ደጋ እሚምታ

ባንድ እጁ ብረት ባንድ እጁ ካርታ።

226. ድብ እና ድቡን አደ ባላቂ

የተኮረፈ ሰው አስታራቂ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

227. ሰባ እና ሰማኒያ ተደጋጋፊ ነው

በሽብር ራሱን ብትይልኝ ምን ነው፡፡

229- ወንዙ ምን አለ መልካው ምን አለ

ጀግናው አለልኝ የለም ብሎ አለ፡፡

230- አይዞሽ እናቴ አትስጊ ለእኔ

ጀግናው ሙሄ አስን አለ ከጎኔ፡፡

231 -ያን ማዶ ዞሮ ያ ማዶ ማን ነው

የጀግኖች ሀገር ከዚያ ወድያ ነው፡፡

232- አሻቅቤ ልሩጥ አግድሜ ልጣሰው

የወርቅነሽ ጠላ የማይቀመሰው፡፡

233- ወሽኔ ግሬራ ወሽኔ ማጠንት

የወርቅነሽ ላሞች የታለቡበትን፡፡

234- እንዴት ያለች ሴት ናት ሙያ የሌላት

ዶሮዋን ስትሰራ ከፈለች ካራት

የዶሮዋን ራስ ከእነ አይኗ አየኋት፡፡

235- ጥንስሥ ስጠነስስ ማጠቢያው እምቧጮ

የአለሚቱ ጠላ እንዴት ነህ አርፋጮ፡፡

236- አምናም አርግኸና ነው ዘንድሮም ወልጀ

ቆይ አንተ ቆማጣ ይደግማ ልጀ፡፡

237-የጀግና ሰው ሁሉ የለውም ትንሽ

እንጀራን ጋገረ ተልባውን እስካሽው፡፡

238- ይሁን ብለህ አይደል የሸሽህ እኔን

እስቲ ሄደህ እየው መበጣጠሱን፡፡

240- ያንን የጋራ ስር አይበላው ላም የለም

እኔን እንደ አንባዛ ያስገኛል ለምለም፡፡

241- ያች ቀበሮ ሔደች ስደት አይለቃትም

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሃገሩ እየከዳት ትደፋለች የትም።

242- መልኳማ ጥሩ ነው የሰለሞን ስራ

የአንገቷ ሸንተረር በተስኪያን አሰራ።

243 ከቤቴ አጠገብ ያለች ዋንዛ

በልታ አትጠረቃ ተቀብታ አትወዛ።

244- አትዋል ይዋሉ አትምከር ይምከሩ

ከማሱት ጉድጓድ ሳይገቡም አይቀሩ

በመልካም ግብርህ ከቤት አይቀሩ።

245- እኔ አንተን አይደለሁ ወዳጁን አላማ

በላይ ካልዘነበ በታች ውሃ አይሞላ።

246- እኔ የምወደው አንጥረኛውን

በቆርቆሮ ብቻ የሰራት ልጁን።

247- ይኸኛው በጋ አልፎ የሚመጣው በጋ

ልጆችህ በዙፋን ሚስትህ በወረወቅ አልጋ።

## የፍቅር መግለጫ ቃል ግጥሞች

248- እኔ አንተን አይደለሁ በፍቅር አለግም

ታምሜ ከርሜ መጣሁኝ ሳዘግም።

249 - እኔ አንችን አይደለሁ በፍቅር አልኮራ

ታምሜ ከርሜ  መጣሁ "በከዘራ"።

250- እናትና አባትሽ አይወዱም እንግዳ

ሳሚኝና ልሂድ በሳንቃው ቀዳዳ።

251-ምን ያሽብርሃል ለቤተኛ ሰው

የመጣውን  ዕዳ እኔ ልችለው።

252- ታምሜ ታምሜ በጎ መሆኔ ነው

የከንግዲሁ መምጣ "ግርሻ" ለመሆን ነው።

253- የበጎች እረኛ ችግ ይላል በጊዜ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አንችን ይስጡኝ እና ይቅርብኝ ደምወዜ።

267- ፍየሊቱ አበባ በጊቱ አሰለፈ

ልቤን ወሰደችው እያስለፈለፈች።

268-እንጨኴት እሰብራለሁ ብየ ስነግርህ

ጨፈቃ እቆርጣለሁ አለማለትህ

ውሃልቀዳነው ብየ ስነግርህ

ከብቶች አጠጣለሁ አለማለትህ።

269-ከሰላሳው ጥርስዋ አንዱ ተመቋል

ፍቅረዋ ጥሩ ነበር ግን አገርዋ እርቋል።

270- አልበላሽ አለኝ እንጀራው ለልኩ

እያሰለሰለ እያማረ መልኩ።

271- ቤትህ እና ቤቱ አግድመት ላግድመት

አንገቱ እረዘመ ስጋ እንዳ ድመት።

272 -የፋፋቴ ውሃ ፈረስ የረገጠው

እባክህ አንተ ልጅ ጥርስህን ግለጠው።

273- ቆለኛ በሬውን ያጠጣል በገንዳ

እቅፍ አርገኝ እና ያበጠው ይፈንዳ።

274- -ልብስሽን አውልቀሽ ነይልኝ ትግያ

አንች የጣልሽ እንደሁ እኔ ነኝ አህያ

እኔ የጣልኩ እንደሁ አየ ፈንጠዝያ።

275- ሣይሉኝ ወድጀ የጎረቤት ልጀ

ራቱን ሳልበላ ልቤ ወደደጀ።

276-እኔ መችአልኩ እና የጌታ ልጀ ወዳጀ

አልኩ እንጀ እኩያየን ሲያመኝ እሳት አንዳጀ።

277- አርጓጼ ለብሶ ይደንሳል እሳ

ሰውስ ጉድ አይልም ወይ እኔ አንችን ብረሳ።

278- ያህያ ሰባራ ያቀጥላል ባመት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ምርት የለው ግርድ የለው ፍቅር የለቀለት።

279-አስታማኝ አስታማኝ ሲጠናብኝ አይታ

ፍቅሬ ወዴት ሄደች ሳትታመን ቀርታ።

280-የበጎች እረኛ የነጆላሊት

ቀን አይመቸኝም ልምጣ ወይ ለሊት።

281-በሰባራ ፎሌ ውሃ አይጠለቅም

እኔ እወድሽአለሁ ያንችን ግን አላውቅም።

282-ባልሽ ነጋዴ ነው ነግዶ ያብላሽ

ለሳቅ ለጨዋታው እኔ አለሁልሽ።

283- አምጃ ላምጃ ይሄዳል ቀበሮ

እኔገና ልጅ ነኝ አላውቅም ቀጠሮ።

284- እጎራው ላይ ሆኘ ባነጥስ ባነጥስ

ወይ አንች ብቅ አትይ ወይ ጥጃው አይበጥስ።

285- ጊንባ በጉ እረባ እረኛው ቢገኝ

ሽጌ ደህና ሰንብች እስክንገናኝ።

286. አለቅሳለሁ በአይኔ እጮሃለሁ በጀ

የበጎች እረኛ እረቆኝ ከደጀ።

287-ሀኪም ቤት አልሔደች ያለችው እቤት
እንዴት ላርጋት እኔ ያችል ልጅ አሟት።

288-ላሊበላ ልሂድ በዚያው ልመንን
ነፍሴ በዛች ሸጋ ይማር እንደሆን።

289- መጣች ያገሬ ልጅ እንደ አረግ ተመዛ

ሳይቀምሱት አጥጋቢ ጨዋታዋን ይዛ።

290- ምነው ባደረገኝ የጊንባን ገለባ

እንድትረጋግጠኝ ስትወጣ ስትገባ።

291- ምነው ባደረገኝ ያባትህ መናሽ

ዘወትር እንዳይህ እህል ስሰጥህ።

292- ወገብና ዳሌ ያምላክ ስራ ነው

እኔን የገረመኝ አካሄዷ ነው።

293- ተደጋጋፊ ነው እርጎየና ደዬ

ሽንጧ የሚመስለው በሰይፍ የተለየ።

294- አስራ ሁለት በጎች ከደጃሽ አስረሽ

ስጋ ብዬ ስሔድ ምነዋ ጨከንሽ።

295- አንተም የሰው ግዙ እኔም የሰው ገዙ

ቁጭ በል እናውራ ይቅርብን ደመወዙ።

296- አገሬ ጉራንጉር ያለሁት በለምድ

ስንቱን ጎራ ዞሬ አንችን አላለምድ።

297- አጋሙን ግራሩን ያበቀልከው ጌታ

ያችል ልጅ ፊለካት አርጋት ጋለሞታ።

298- ጉድ አለ ይላዳ ጉድ አለ ገነት

አጥንት የሌላት ልጅ እንደ ቀይ ሽንኩርት።

299- የሰማዩን ኮከብ አንድ ብለሽ ቆጥረሽ

የምድሩን አሸዋ አንድ ብለሽ ቆጥረሽ

የዚያን ያህሉ ነው እኔ የምወድሽ።

300- ካንተ ጋር አድሬ ሲነጋ ልሙት

ላፈር አይደለም ወይ የተፈጠርኩት።

እሪኩም በሉላት ያስወጣላት
እሪኩም በሉላት ይለይላት
እሪኩም በሉላት ያስወጣላት
እሪኩም መጋላ ሰንደል ገላ።

## አባሪ 2:- ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. በእረኝነት ስፍራ የምትለበሷቸው የተለየ አልባሳት አላችሁ? ወደእረኝነት ስትመጡ ምንምን ነገሮችን ይዛችሁ ትመጣላችሁ?
2. በእረኝነት ስፍራ ቃል ግጥሞችን እንዴት ነው የሚትገጥሙት? በምን ስአት እና ጊዜ?
3. ቃልግጥሞቹን ስትገጥሙ ለብቻችሁ ነው ወይስ እንዴት ነው?ፈጥራችሁ ነው ወይስ ሌላ ሰው ሲል የሰማችሁትን እንዴት ተማራችሁ?
4. ከብቶችን ስትጠብቁ ምን ምን አይነት ቃል ግጥሞችን ትገጥማላችሁ? በምን አይነት መንገድ?
5. በምትናገሩአቸው የቃል ግጥሞች ማህበረሰቡ በናንተ ላይ ምን አመለካከት አለው? ምን ይላችሃል?
6. በእረኝነት ስፍራ የምትግባቡበት የተለየ ቋንቋ አላችሁ? ይህ ቋንቋ ምንድን ነው? መቼ ትጠቀሙበታላችሁ? ለምን ያገለግላል ?
7. የእረኝነት ሙያ ሁሉንም ጾታዎች ያካትታል? ሙያውን እንዴት ትገልጸዋለህ(ሽ) ?


# አባሪ 4፡- የፎቶ መግለጫ



ፎቶ 1፡- በለጋምቦ ወረዳ ጊምባ ሜዳ



ፎቶ2፡- አጥኚዋ ከእረኛ ኢብራሂም ሃሰን ጋር



ፎቶ3፡- እረኛ ኑርዮ ጋሻው በቱሉ አውልያ



ፎቶ4፡- እረኞች በፉከራ ቃል ግጥም



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ፎቶ 5፡- የይላዳ ባህላዊ የትግል ስነ-ስረዓት



ፎቶ 6፡- አጥኚዋ በቃለ መጠይቅ ላይ



ፎቶ7፡- የእረኞች አልባሳት



ፎቶ 8፡- እረኞች በጊምባ ሜዳ ላይ



ፎቶ9፡- እረኞች በዘፈን ግጥሞች ክዋኔ



ፎቶ 10፡-እረኛ ኢብራሂም ሃሰን



ፎቶ 11፡- እረኞች ከብት የሚያጠጡበት ወንዝ(ጊምባ)

እኔ አልማዝ ዘውዱ በአ.አ.ዩ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ተማሪ ያቀረብኩት ጥናት የራሴ መሆኑን የተጠቀመበኩባቸው ተዛማጅ ጽሑፎች በአግባቡ የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ______________________________

ፊርማ ______________________________

ቀን ______________________________

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY